# የቤንች ህገረሰባዊ ትውን ጥበባት ክዋኔ

በ

ምንታምር ልንገርህ

ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ከሚጠበቁ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ

ጥናታዊ ጽሑፍ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

የሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ
የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት
የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ-ግብር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ሰኔ 2003 ዓ.ም

# የቤንች ህገረሰባዊ ትውን ጥበባት ክዋኔ

በ

ምንታምር ልንገርህ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አማካሪ

አብርሃም አለሙ

ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ከሚጠበቁ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ

ጥናታዊ ጽሑፍ

የሰብአዊ ሳይንሶች ፋኩልቲ

የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የኢትዮጵያ ስነ-ፅሑፍና ፎክሎር ድህረ ምረቃ መርሀ-ግብር

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2003 ዓ.ም

# የቤንች ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት ክዋኔ

በምንታምር ልንገርህ አያሌው

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰብአዊ ሣይንሶች ፋኩልቲ

ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ድኅረ ምረቃ ፕሮግራም

ለኤም.ኤ ዲግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| [illegible] | [illegible] | 18/07/11 |
| አማካሪ | | |
| [illegible] | [illegible] | 10/11/2003 |
| ፈታኝ | | |

# ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ ካርታዊ መግለጫ




ምንጭ፣ የሚዛን ፋይናንስ ቢሮ

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

## ምስጋና

ካደረጉልኝ አንፃር የቃላት ምስጋና የሚያንሳቸው ቢሆንም አማካሪዬ አቶ አብርሃም አለሙን በመጀመሪያ አመሰግናለሁ፡፡ ከአማካሪዬ በመቀጠል እኔ ለራሴ ከማስበውና ከምጨነቀው በላይ ስለኔ የሚጨነቁልኝንና የሚያስቡልኝን ቤተሰቦቼንና ውድ ጓደኛዬ መብራቱ በላቸውን ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡ እንዲሁም ጥዋት ማታ ከጎኔ በመሆን ብርታት ለሆኑኝ ጓደኞቼ ለባንችአምላክ በቀለና ለአመለወርቅ ወርቅነህ ልባዊ ምስጋናዬ ይደረሳቸው፡፡

የጥናቱን አርትኦት በመስተካከል እና የሀሳብ ድጋፍ በማድረግ የተባበሩኝን የዚህ ክፍል ተማሪ የሆኑትን አቶ ዋልተንጉስ መኮነን እና ስለሽ አባተን እንዲሁም ሰለሞን ታደለንና እና መልካም ጋሻዬን ለማመስገን እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻ በየቀኑ ለጥናቱ የሚያግዙ የቤተ መጽሐፍት መረጃዎችን ለመጠቀም ስፈልግ ደከመኝና ሰለቸኝ ሳይሉ ያስተናገዱኝን የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ቤተ-መጽሐፍት ሰራተኞች በሙሉ አመሰግናሉ፡፡ እንዲሁም በመስክ ቆይታዬ የቪዲዮ ካሜራ ባለሙያ በመሆን አብሮኝ ከቦታ ቦታ በመዘዋወርና የሚቀረፁ መረጃዎችን በመቅረፅ የተባበረኝን ደረጀ በላይን፣ የደቡብ ቤንች ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሰራተኞችንና ለዚህ ጥናት መሳካት በተለያየ መልኩ እገዛ ያደረጉልኝ ሰዎች በሙሉ አመሰግናቸዋለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ሲዘጋጅ የቤንች ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት የሚከወኑት መቼ፣ በማን እና ለምን እንደሆነ መመርመር፤ ትውን ጥበባቱ በማህበረሠቡ ውስጥ የሚፈጥሩትን ማህበራዊ ትስስር መግለጽ፤ ማህበረሰቡ ታሪኩን፣ እምነቱንና እሴቱን በሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እንዴት እንደሚገልፀው ማሳየት የጥናቱ ዋና አላማ ነው፡፡ ይህንን አላማ ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ውስጥ ትውን ጥበባቱ መቼ? በማን? እንዴትና ለምን? ይከወናሉ? የሚሉ ጥያቄዎች ተመልሰዋል፡፡

በጥናቱ አላማ መሰረት መስክ በመውጣት በምልከታና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በምዕራፍ ሁለት ከተገለፁት የምሁራን ትውሮች አንፃር ተተንትነዋል፡፡

በጥናቱ የማህበረሰቡ አባላት የእኔ ናቸው ብለው ያመኑባቸውና ይገልፁታል ተብለው በቀጥታ ገለጻ የተደረጉባቸው በማህበረ-ባህላዊ እና በሃይማኖታዊ አውዶች የሚከወኑባቸውን ትውን ጥበባት እና በትውን ጥበባቱ ወቅት የሚጠቀሙባቸውን የመከወኛ ቁሶች ናቸው፡፡ የማህበረሰቡ ትውን ጥበባት የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎች መሰረት በማድረግ ማህበረ-ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ አውዶች ተብለው ተመድበዋል፡፡ እነዚህ አውዶች በማህበረሰቡ አገላለጽ መሰረት ማህበረ-ባህላዊ አውድ ስር የወርደት፣ የየብ እና የቃይጥ ተብለው በመመደብ ገለፃ ተደርጎባቸዋል፡፡ እንዲሁም በሃይማኖታዊ አውድ ስር የባለቃልቻ ዱቦችና ዶሮች ተብለዉ በመከፋፈል ተገልፀዋል፡፡

በማህበረሰቡ ዘንድ በወርደት፣ በየብና በቃይጥ የሚከወኑት ትውን ጥበባት በማህበረሰቡ ቋንቋ ዶርና ዱብ ሲሆኑ እነዚህ ትውን ጥበባት በሚከወኑባቸው ወቅቶች የማህበረሰቡ አባላት ስሜታቸውን፣ እምነታቸውን፣ ፍላጎታቸውንና አመለካከታቸውን እንደሚገልፁባቸው ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ እንዲሁም እነዚህ ትውን ጥበባት መከወናቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የትስስር መንፈስን በመፍጠር በኩል ሰፊ ድርሻ እንዳላቸው ጥናቱ ያስረዳል፡፡ ለምሳሌ፡- በወርዶት ወቅት ዶር መከወኑ በማህበረሰቡ ዘንድ የትዳር አጋር ማግኛ በመሆን ያገለግላል፡፡ በየብ ወቅት በሚከወኑ ዶሮች ማህበረሰቡ ሀዘኑን ይረሳበታል፣ የሙት መንፈስ ይረጋጋበታል፡፡ በቃልቻ ክብረ በዓል በሚከወኑ ዶሮች አማካይነት ደግሞ የእምነቱ ተከታዮች አምልኮታቸውን እንደሚፈፅሙበት እና በቃይጥ ወቅት በሚዜሙ ዱቦች ደግሞ የማህበረሰቡ አባላት የአንድነት መንፈሳቸውን እንደሚያጠናክሩበት በጥናቱ ተገኝቷል፡፡

ዱቦችና ዱሮች ሲከወኑ የሚጠቀሙባቸው የመከወኛ ቁሶች ክዋኔውን ከማድመቅ ባለፈ የማህበረሰቡ እምነት፣ ታሪክ እና አመለካከት በመግለፅ በኩል ሰፊ ድረሻ እንዳለቸው በጥናቱ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገፅ


ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ካርታዊመግለፃ....................I

ምስጋና....................II

አጠቃሎ....................III

1. መግቢያ....................1

1.1 የጥናቱ ዳራ ....................1

1.2 የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት....................2

1.3. የጥናቱ ዓላማ ....................3

1.4 የምርምር ጥያቄዎች....................3

1.5. የጥናቱ ወሰን ....................3

1.6. የጥናቱ አስፈላጊነት....................4

1.7. የመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴ....................4

1.7.1 ምልከታ....................5

1.7.2. ቃለ መጠይቅ....................6

1.8. የጥናቱ አቀራረብ ....................7

1.9. የመስክ ቆይታ....................7

1.10. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች....................9

1.11. የጥናቱ አደረጃጀት....................12

2. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት....................13

2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ....................13

2.1.1. የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ምንነት....................13

2.1.1.1 ሀገረሰባዊ ሙዚቃ....................14

2.1.1.2 ሀገረሰባዊ ዳንስ....................15

2.1.1.3 ሀገረሰባዊ ድራማ....................16

2.2. ጥናቱ የሚከተላቸው ንድፈ-ሀሳቦች ....................16

2.2.1. ክዋኔ ተኮር ቲወሪ....................17

2.2.1.1 የመከወኛ አጋጣሚ ....................19

2.2.1.2 ከዋኝ ........................................ 19

2.2.1.3 ታዳሚ ........................................ 20

2.2.1.4. አውዳዊ ቲወሪ ........................................ 21

2.2.1.5 የክዋኔ ጠቋሚዎች ........................................ 23

2.2.1.6. የመከወኛ ቁሶች ........................................ 23

2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................................ 24

2.3.1. ሀገረሰባዊ ዳንስን ያጠኑ ........................................ 24

2.3.2. ባህላዊ ሙዚቃን ብቻ ያጠኑ ........................................ 27

2.3.3. የማህበረሰቡን አኗኗር ከሙዚቃቸው ጋር አያይዘው ያጠኑ ........................................ 28

2.3.4. በአጠቃላይ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን ያጠኑ ........................................ 29

3. ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ........................................ 31

3.1. ዞናዊ ገጽታ ........................................ 31

3.2 መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ንብረት ........................................ 32

3.3 የቤንች ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር ........................................ 32

3.4 የቤንች ማህበረሰብ ቋንቋ ........................................ 33

3.5. ባህላዊ አስተዳደር ........................................ 34

3.6. ኢኮኖሚያዊ ተግባራት ........................................ 36

3.7. መሰረተ ልማት ........................................ 36

3.8. ማህበረ-ባህላዊ እሴቶች ........................................ 37

3.8.1. የጋብቻ ስርዓት ........................................ 37

3.8.2. የለቅሶ ስርዓት ........................................ 40

3.9 ባህላዊ እምነት ........................................ 41

3.9.1 የሚያንጌ እምነት ........................................ 42

3.9.2 የቃልቻ እምነት ........................................ 43

4. የቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት አውዳዊ ክዋኔ ገለፃ ........................................ 45

4.1 የቤንች ሀገረሰባዊ ሙዚቃ (ዱብ) ........................................ 46

4.1.1 ማህበረ- ባህላዊ አውድ ........................................ 47

4.1.1.1 የወርደት ዱብ (የሰርግ ሙዚቃ) ........................................ 47

4.1.1.2 የየብ ዱብ (የለቅሶ ሙዚቃ) ........................................ 52

4.1.1.3 የቃይጥ ዱብ (የስራ ሙዚቃ) ....................................................55
4.1.2 ሃይማኖታዊ አውድ....................................................................57
4.1.2.1 የቃልቻ ዱብ (የቃልቻ ሙዚቃ).................................................57
4.2 የቤንች ህገረሰባዊ ዳንስ (ዶር)..............................................................58
4.2.1 ማህበረ- ባህላዊ አውድ..................................................................59
4.2.1.1 የወርደት ዶር (የሰርግ ዳንስ) ....................................................59
4.2.1.2 የየብ ዶር (የለቅሶ ዳንስ) ..........................................................65
4.2.2.ሃይማኖታዊ አውድ.....................................................................70
4.2.2.1 የቃልቻ ዶር (የቃልቻ ዳንስ)...................................................70
4.3 የቤንች ህገረሰባዊ ትውን ጥበባት የመከወኛ ቁሶች......................................73
4.3.1 የዱብ መሣሪያ (የሙዚቃ መሳሪያ)........................................................74
4.3.1.1 የእጅ የዱብ መሳሪያ.............................................................75
4.3.1.2 የትንፋሽ የዱብ መሳሪያ.........................................................78
4.3.1.3 የእግር የዱብ መሳሪያ ..........................................................81
4.3.2. ለማድመቂያነት የሚውሉ ቁሶች ...................................................82
4.3.3 አልባሳት.......................................................................................86
5. ማጠቃለያ..........................................................................................90
ጥቅስማ (Reference)
አባሪዎች
አባሪ አንድ
አባሪ ሁለት

# የምስል ማውጫ


ርዕስ | ገፅ

ምስል 4.1. ዳሶዬ ሲጨፍሩ ....61

ምስል 4.2 ባባ ሲጨፍሩ ....62

ምስል 4.3 ናሪ ሲጨፍሩ ....63

ምስል 4.4 ቶናስ ሲጨፍሩ ....64

ምስል 4.5 የሮ (ይሀ) ሲጨፍሩ ....67

ምስል 4.6 ሲሶ ሲጨፍሩ ....68

ምስል 4.7 አስ ሲጨፍሩ ....70

ምስል 4.8 ለባለአባት ሲጨፍሩ ....72

ምስል 4.9 ክራር የዱብ መሳሪያ ....76

ምስል 4.10 ሶስቱ ቲያርቦች ....78

ምስል 4.11 ቶህ ሲነፉ ....79

ምስል 4.12 ፊርግን ....80

ምስል 4.13 ቶሪ (ቃጭል) ....82

ምስል 4.14 ጃስ ....85

ምስል 4.15 ማይትና ማይዱሽ ....87

ምስል 4.16 እጨጭና የአሞራ ክንፍ ....88

# 1. መግቢያ

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት የአንድ ማህበረሰብ አባላት በተለያዩ ወቅቶች፣ ለተለያዩ ዓላማዎች የሚከውኗቸው እንደ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ሀገረሰባዊ ዳንስ እና ሀገረሰባዊ ድራማ የመሳሰሉትን የፎክሎር ዘውጎች የሚካተቱ ክፍሎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት፣ የመምጣታቸውን ስለምን የሚወስኑ፣ የመከወኛ አጋጣሚዎች ያሏቸው፣ በተወሰኑ ጊዜያትና ቦታዎች፣ ለተወሰነ ማህበራዊ እና ሀይማኖታዊ ፋይዳ የሚከወኑ ጥበባዊ ሃብቶች ናቸው፡፡ በነዚህ አጋጣሚዎች በሚከሰቱ ሁነቶች አማካይነት ማህበረሰቡ ደስታውን፣ ሀዘኑንና ስሜቱን ይገልፅባቸዋል፡፡ የታመቀና የታፈነ ስሜቱን አውጥቶ ማንነቱን ያደላድልባቸዋል፡፡ ማህበራዊ ሰላሙንና እሴቱን በየትውልዱ ልቦና ውስጥ አትሞ ያስቀምጥባቸዋል፡፡

ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ የደስታና የሀዘን ጊዜያትን ያጅባሉ፡፡ አጀቡም በጭፈራ ፣ በሙዚቃ፣ በእንጉርጉሮ እና በስርዓቱ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የሚከወን ሊሆን ይችላል፡፡ ስርዓቶችም የትውን ጥበባቱ ባለቤት ማንነት የሚገልፁ ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህ ሃገረሰባዊ ጥበብ የሚባል ቅርፅ ፎክሎር ትኩረት ሰጥቶ ከሚያጠናቸው የአንድ ማህበረሰብ ማንነት መገለጫ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የፎክሎር ጥናት የአንድን ማህበረሰብ መንፈሣዊና ቁሣዊ ጥበባት፣ ስለህይወት፣ ስለተፈጥሮ፣ ስለዓለማት ወዘተ…ያለውን አስተሳሰብ፣ እምነትና ፍልስፍና ይገለፃል፡፡ በነዚህና በሌሎች ፈርጀ ብዙ ምክንያቶች የተነሣ የፎክሎርን ልዩ ልዩ ቅርፃች (genres) ሳይንሣዊ በሆነ መንገድ ሰብስቦ በወጉ ማጥናትና ሰንዶ ማስቀመጥ አስፈላጊ ነው (ፈቃደ፣ 1991)፡፡ የአንድ ማህበረሰብ የማንነት መገለጫ የሆነውን ሀገረሠባዊ ትውን ጥበባት ማጥናት ማህበረሰቡ ታሪኩን፣ እምነቱንና እሴቱን በቁሳዊና በትውን ጥበባቱ እንዴት እንደሚፈጥርና እንደሚገልፅ፤ ስለ ህይወት ያለው ፍልስፍና ምን እንደሚመስል ለማወቅ ያስችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ክዋኔው የሰውን ተራክቦ (ግንኙነት) ማጥኛ ከሆኑት መሠረታዊ መንገዶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ

ተራክቦ ማህበረሰቡን የሚያገለግል የጋራ ሀብት ስለሆነ ለማህበራዊ ተግባቦት ወሣኝነት አለው፡፡

የአንድ ክዋኔ ህልውና የሚያርፈው በተግባቦታዊ ነገሮች፣ በግለሰቦች ብቃት፣ በተሣታፊዎች ሚና እና በወቅቱ በሚከሰቱ አውዳዊ ነገሮች ላይ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ትውን ጥበባቱ ለመከወን የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ ገቢሮች፣ ክስተቶችና የአከዋወን ደንቦች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው የአከዋወን ስርዓቶች ናቸው" (Bauman, 1991፡15)፡፡ እነዚህ ህዝባዊ ሀብቶች በሚከወኑበት ወቅት የማህበረሠቡን ማንነት፣ ያለፈ ታሪክ እና አመለካከት በመግለጽ በኩል የሚሠጡት የራሳቸው የሆኑ ተግባራት አሏቸው፡፡

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት የአንድን ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ፣ እድገት፣ ማንነት፣ ባህል እና እምነት፤ እንዲሁም ከሌላው ማህበረሰብ ጋር የሚመሣሠልባቸውን እና የሚለያዩባቸውን ገፅታዎች ለመረዳት ያስችላል፡፡ በመሆኑም የቤንች ሀገረሠባዊ ትውን ጥበባት ከሀገረሰባዊ ሙዚቃና ከሀገረሠባዊ ዳንስ አንጻር መጠናታቸው የማህበረሰቡን ማንነት፣ የህይወት ፍልስፍና እና ታሪካዊ አመጣጥ ለመረዳትና ለማወቅ ይረዳሉ፡፡ ከዚህ ሀሣብ በመነሣት የማህበረሰቡ ሀገረሠባዊ ትውን ጥበባት መቼ፣ በማን፣ እንዴትና ለምን ተግባር እንደሚከወኑ ይህ ጥናት ትኩረት ሠጥቶ ይመረምራል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

የቤንች ማህበረሰብ እንደሌሎች ማህበረሰቦች የራሳቸው የሆኑ በርካታ ቁሳዊና መንፈሳዊ እሴቶች አሏቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ ቁሳዊና መንፈሳዊ እሴቶች ተገቢ የሆነ ትኩረት አግኝተውና በባለሙያዎች በበቂ ሁኔታ ተመርምረው፣ የተያዙና ለተተኪው ትውልድ ሊተላለፉ በሚችሉበት መንገድ ተቀርሰው የተያዙ ነገሮች እንደሌሉ አረጋግጫለሁ፡፡ ይህንም ያልሁት ለዚህ ጥናት ርዕስ ለመምረጥ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ቤተ መፅሐፍት ሳነብ ምንም ያገኘሁት መረጃ ስለሌለ ነው፡፡ በመሆኑም የማህበረሠቡ መገለጫ የሆኑትን እነዚህን ትውን ጥበባት ማጥናትና ወደ አካዳሚያዊ ጉዳይ ለውይይት ማምጣት የዚህ ጥናት ዋነኛው አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡ ከአሁን በፊት በቤንች ማህበረሰቦች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ቢኖሩም፣ በትውን ጥበባት ላይ ግን ሙሉ በሙሉ

ሆነ በክፊል የተካሄዱ ምርምሮች ስለሌሉ ያንን ክፍተት ለመሙላት ማሰቤ ሌላው ምክንያቴ ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የቤንች ማህበረሰብ ትውን ጥበባቱን የህይወት መልኩ አድርጎ ይዟቸው እንዲዘልቅ ያደረገውን ምክንያት ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በዚህ ዋና ዓላማ ላይ ተመስርቶ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች በውስጡ ይዟል፡-

- ➢ ትውን ጥበባቱ የሚከወኑባቸውን አጋጣሚዎች ማሳየት፣
- ➢ የከዋኞችንና የታዳሚዎች ሚናና ማንነት መግለጽ፤
- ➢ ትውን ጥበባቱ በማህበረሠቡ ህይወት ውስጥ ያላቸውን ተግባርና ፋይዳ መመርመር፤
- ➢ ማህበረሰቡ ታሪኩን፣ እምነቱንና እሴቱን በእነዚህ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እንዴት እንደሚገልፀው ማሳየት፡፡

## 1.4 የምርምር ጥያቄዎች

ከላይ የተዘረዘሩትን አላማዎች ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

- የማህበረሰቡ ትውን ጥበባት መቼ፣ እንዴት እና በማን ይከወናሉ?
- ትውን ጥበባቱ በመከወናቸው ለቤንች ማህበረሠብ ያላቸው ተግባር ምንድን ነው?
- ትውን ጥበባቱ የማህበረሰቡን ታሪክ፣ እምነት፣ እሴት እና ማህበራዊ ደረጃ በመግለጽ በኩል ያላቸው ተግባር ምንድን ነው?

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ኢትዮጵያ የብዙ ማህበረሰብ አገር ናት፡፡ አብዛኞዎቹ ማህበረሰቦች ደግሞ በደቡብ የሀገሪቱ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፤ ከነዚህ መካከል አንዱ የቤንች ማህበረሰብ ነው፡፡ የዚህ ማህበረሰብ አባላት በቤንች ማጅ ዞን ውስጥ በሚገኙ ሶስት ወረዳዎች (ደቡብ

ቤንች፣ ሰሜን ቤንች እና ሺ ቤንች) ላይ ተበታትነው እና ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር ተቀላቅለው የሚኖሩ ሲሆን በአብዛኛው ግን ሰፍረው የሚገኙት በደቡብ ቤንች ወረዳ ነው፡፡ እኔም ካለኝ የጊዜ እና የኢኮኖሚ ውስንነት አንፃር ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ የመስክ መረጃዎች የተሰበሰብሁት የማህበረሰቡ አባላት በብዛት ሰፍረው ከሚገኙበት ደቡብ ቤንች ወረዳ (ኮብ፣ ደብረወርቅ፣ ሚያህ፣ አማን፣ አዲስ አለም፣ ጊሊት እና ቂጤ ቀበሌ) ነው፡፡ ስለዚህ የጥናቱ ተተኳሪም ይኸው ወረዳ ብቻ ነው፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ በዋናነት የሚያተኩረው የቤንች ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ከሆኑት መካከል የሀገረሰባዊ ዳንስ (Folk dance) እና የሀገረሰባዊ ሙዚቃ (Folk music) አውዳዊ ክዋኔ በመግለፅ ላይ ነው፡፡

## 1.6. የጥናቱ አስፈላጊነት

ኢትዮጵያ የብዙ ማህበረሰብ አገር እንደመሆኗ መጠን የተለያዩ የህዝብ ታሪኮችን፣ ቅርሶችን እና ትውን ጥበባት (ጭፈራዎችን፣ ውዝዋዜዎችንና ዘፈኖችን) በውስጧ አካታ ይዛለች፡፡ እነዚህ ትውን ጥበባት በየዘርፍ በየዘርፉ ተከፋፍለው መጠናታቸው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ጥበባዊ ተግባር በመግለጽ በኩል ሰፊ የሆኑ ጠቀሜታዎች አሏቸው፡፡ በመሆኑም የቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት መጠናታቸው የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይሰጣሉ፡፡

- የቤንች ማህበረሰብ ትውን ጥበባት በማን፣ መቼ፣ እንዴት እና ለምን እንደሚከወኑ ለሌሎች ማህበረሰቦች ለማሳወቅ ይጠቅማል፡፡
- የቤንች ሀገረሠባዊ ትውን ጥበባት የማህበረሰቡን ታሪክ እንዴት እንደሚገለፁ ለሌሎች ሰዎች ያስተዋወቃል፡፡

## 1.7. የመረጃ መሠብሠቢያ ዘዴ

ይህ ጥናት ሲካሄድ ከመስክ በፊትና በኋላ ጥናቱ ስለሚደረግበት አካባቢና ማህበረሰብ ታሪካዊ፣ መልካዓምድራዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራዎች ተጽፈው ከተገኙ ፅሁፎችና በአካባቢው ጥናት ካደረጉ ግለሰቦች መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ የጥናቱን ርዕሰ ጉዳይ መሠረት በማድረግ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቤተ-መፅሐፍት

የተገኙ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ጥናቶች እንዲሁም በታዋቂ ጆርናሎች ላይ የወጡ አርቲክሎች ተዳሰው የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ተደርጓል፡፡

በፎክሎር ጥናት የመረጃ መሠብሠብያ ዘዴውን የሚወስነው የጥናቱ ርዕስና የጥናቱ ዓላማ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ እኔም ጥናቱን ለማካሄድ መረጃዎችን የሰበሰብኳቸው ቀጥሎ የቀረቡትን ዘዴዎች ተጠቅሜ ነው፡፡ አንዱና ዋነኛው የምልከታ ዘዴ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የቃለ መጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ በመጀመሪያ ግን በትልመ ጥናቱ ላይ እንደገለጽሁት መረጃውን ለመሰብሰብ ያሰብሁት ከላይ ከተገለፁት በተጨማሪ የቡድን ውይይት የመረጃ መሠብሠብያ ዘዴን ጭምር በመጠቀም ነበር፡፡ ነገር ግን የቡድን ውይይት ለማድረግ ባህሉ የማይፈቅዳቸው የተለያዩ ምክንያቶች ስላሉ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ ለምሳሌ፡- አንዱ ባለቃልቻ ከሌላው ባለቃልቻ ጋር ከተገናኘ እንሞታለን ብለው የማመንና የመሳሰሉት ችግሮች ስላሉ በዚህ ምክንያት መስክ በወጣሁበት ወቅት ቃለ መጠይቅና ምልከታ በመጠቀም የባህል አዋቂ ከሆኑት ሰዎች ከሚያዝያ 11 እስከ ግንቦት 6 ቀን መረጃዎችን ሰብስቤአለሁ፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም ከምሁራን ንድፈ ሀሳብ አንፃር ገለጻና ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡ እያንዳንዱ የመረጃ መሠብሠብያ ዘዴ ከዚህ በታች በሰፊው ተብራርቷል፡፡

### 1.7.1 ምልከታ

ይህ ክፍል መረጃው ሲሰበሰብ ምልከታው በምን መልኩ እንደተተገበረና በጥናቱ ይበልጥ ትኩረት የተሰጠባቸው የትውን ጥበባት ዓይነቶች እንዴት እንደተመረጡ ይገልፃል፡፡

በቤንች ማህበረሰብ ዘንድ የሚከወኑ ትውን ጥበባት ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በተፈጥሮአዊ መቼትና በተፈጥሮዊ ቅንብር መቼት ከእነክዋኔያቸው ምልከታ ተደርጎባቸዋል፡፡ ይህም ማለት የተሰበሰቡት መረጃዎች በተፈጥሮአዊ መቼትና በተፈጥሮዊ ቅንብር መቼት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ተፈጥሮአዊ በሆነ መቼት የተሰበሰቡት መረጃዎች በሠርግ ጊዜ እና በለቅሶ ጊዜ የሚከወኑት ትውን ጥበባት ሲሆኑ በተፈጥሮዊ ቅንብር መቼት የተሰበሰቡት ደግሞ ለቃልቻ ክብረ በዓል የሚከወኑት ትውን ጥበባት ናቸው፡ በምልከታው ወቅት የተሰበሰቡት መረጃዎች በፎቶ ግራፍ (በአንድ በባለ ሰባት መቶ ኤም ቢ ዲስክ)፣ በቪዲዮ (በአንድ በባለ 4.7 ጂፒ የዲቪዲ

ዲስክ) እና በምልከታው ወቅት በተያዙ የፅሁፍ ማስታወሻዎች በመታገዝ ተሰብስበዋል፡፡

### 1.7.2. ቃለ መጠይቅ

ይህን ጥናት ለማጥናት ከተጠቀምሁባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንዱ ቃለ መጠይቅ ሲሆን ቃለ መጠይቅ የማደርግላቸውን መረጃ ሰጪዎች ስመርጥ ሁለት መንገዶችን ተጠቅሜያለሁ፡፡ የመጀመሪያው መንገድ ከወረዳው ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊዎች ጋር በመገናኘት ባህሉን በደንብ ያውቃሉና መረጃ ይሰጣሉ የተባሉ ሰዎችን በመምረጥ ሲሆን ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ምልከታ ለማድረግ በየቀበሌው በምዘዋወርበት ወቅት ባህል አዋቂ ሰዎችን ከአካባቢው ሰው በመጠየቅ ነው፡፡ የተመረጡትን ሰዎች ቀጠሮ በማስያዝና ቀጠሮ ሳላስይዝ ባገኘሁበት አጋጣሚ ቃለ መጠይቅ በማድረግ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡ በቀጠሮ ዕለት ቃለ መጠይቅ ያደረግሁላቸው ከባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሀላፊዎች ጋር በመሆን ለተመረጡት ሰዎች ሲሆን በድንገት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ደግሞ ለምልከታ ወደ መከወኛ ቦታዎች በሄድኩበት ወቅት ያገኘኋቸውን ሰዎች ነው፡፡ ቃለ መጠይቁ የተደረገው ዝግጅት በተደረገባቸው እና ዝግጅት ባልተደረገባቸው ጥያቄዎች አማካይነት ነው፡፡ ዝግጅት የተደረገባቸው ማለት ቀድሜ መረጃ አቀባዮችን ከማግኘቴ በፊት የተዘጋጀሁባቸውን ማለት ሲሆን ዝግጅት ያልተደረገባቸው ማለት ደግሞ ከመረጃ ሰጪዎች ጋር ቃለመጠይቅ ላይ በነበርኩበት ወቅት መረጃ አቀባዮች ሲናገሩ ድንገት የሚከሰቱ ጥያቄዎች ማለት ነው፡፡.

ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በመጠቀም ስለቤንች ታሪክ፣ ስለትውን ጥበባት ባህላዊ እሳቤዎች እና ትርጓሜዎች፣ ትውን ጥበባቱ መቼ? የትና በማን እንደሚከወኑ፣ ስለማህበረሰቡ ቋንቋና በትውን ጥበባቱ ወቅት የሚጠቀሙባቸው የመከወኛ ቁሶች እና ተግባራታቸውን የሚያመለክቱ መረጃዎች ሰብስቤአለሁ፡፡ ቃለ መጠይቆች የተካሄዱትም በቢሮዎች ውስጥ፣ በካፍቴሪያዎች እና በመረጃ አቀባዮች ቤት ውስጥ ሲሆን በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መቅረፀ ድምፅ በመጠቀም (አስር ካሴት) እና የፅሁፍ ማስታወሻዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

## 1.8. የጥናቱ አቀራረብ

ይህ ጥናት የቀረበው ገላጭ በሆነ መንገድ ነው። ይህ አቀራረብ የተመረጠበት ምክንያት የተሠበሠበውን መረጃ መግለፅ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ ሁኖ ስለተገኘ ነው። በዚህ አቀራረብ በመጠቀም የቤንች ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ዳንስ እና ሙዚቃ በሚከወኑበት ወቅት፣ የሚያከናውኗቸው ድርጊቶች እና የሚጠቀሙባቸው ቁሶች (የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ የማድመቂያ ቁሶች እና አልባሣት) ተገልጸዋል። እንዲሁም በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ የሚከውኑት ትውን ጥበባት እንደሚከወኑበት አጋጣሚ ገለፃ ተደርጎባቸዋል። በአጠቃላይ ማህበረ-ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ክዋኔዎች የትና በማን እንዲሁም ለምን አላማ እንደሚከወኑ በመግለፅ ጥናቱ አሳይቷል።

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ የጥናቱ ትኩረት የሆነው የቤንች ማህበረሰብ ትውን ጥበባት ክዋኔ፣ የመከወኛ አጋጣሚ፣ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ አውድ እንዲሁም በክዋኔው ወቅት የሚጠቀሙባቸው የመከወኛ ቁሶች እና የመሣሠሉት ከዚህ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ አንፃር ተገልጸዋል።

## 1.9. የመስክ ቆይታ

ለጥናቱ የመረጥሁትን አካባቢ ቀደም ብዬ ለተወሰነ ቀናት የማውቀው ቢሆንም በጥናት መልክ ግን ትኩረት ሰጥቼ አላየሁትም ነበር። ነገር ግን ወደ አካባቢው ከመሰማራቴ በፊት በአካባቢው ጥናት ያደረጉ ሰዎችን በማነጋገር ስለመረጃ ሰጪዎች እና ስለአንዳንድ ጉዳዮች ቀድሜ ለመዘጋጀት ችያለሁ።

በመሆኑም ወደ መስክ በምወጣበት ወቅት ከትምህርት ክፍሉ የትብብር ደብዳቤ በማፃፍ ሚያዝያ 8 ቀን 2003 ዓ.ም ከጥዋቱ 12:00 ከአዲስ አበባ ተነስቼ ወደ መስክ አመራሁ። ከዚያም ከሁለት ቀን ጉዞ በኋላ የዞኑ ዋና ከተማ ከሆነችው ሚዛን ከቀኑ 11:30 ገባሁ። በመቀጠል ሚያዚያ 10 ቀን 2003 ዓ.ም ከትምህርት ክፍሉ ያፃፍሁትን ደብዳቤ ለዞኑ አስተዳደር ልዩ አማካሪ ለአቶ ካሣሁን ከበደ ሰጠኋቸውና እሳቸው ጉዳዩን ተረድተው ወደ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የትብብር ደብዳቤ ፃፉልኝ። ያንን ደብዳቤ ይዤ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ስሄድ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊው በትክክል የቤንች ማህበረሰብ ባህል በሚገኝበት ደቡብ ቤንች ወረዳ አድርሶኝ የሚመጣ አንድ ሰው እና ለወረዳው አስተዳደር

የትብብር ደብዳቤ ፅፈው ላኩኝ፡፡ የተመደበልኝ ባለሙያም የማህበረሰቡ ትክክለኛ ባህል ይገኝበታል ከተባለው የደቡብ ቤንች ወረዳ አደረሰኝ፡፡ ከዚያ መረጃውን በቀላሉ ለመሰብሰብ የማህበረሰቡን ተወካይ ማግኘት ነበረብኝ፡፡ በዚህ የተነሳ አብሮኝ የሄደው ሰው ከወረዳው አስተዳደር ጋር አስተዋወቀኝና የሄድሁበትን አላማ አስረድቶልኝ ተመለሰ፡፡ እኔም በተደረገልኝ ትውውቅና በተፃፈልኝ የትብብር ደብዳቤ መሠረት የወረዳው አስተዳደር የሆነውን አቶ ካማ አዲስን አንዳንድ ትብብሮች እንዲያደርግልኝ ማለትም ቪዲዮና የቪዲዮ ካሜራ ባለሙያ፣ ተፈጥሮዊ ቅንብር መቼት የሚያዘጋጁልኝ እና መረጃ የሚሰጡኝ ሰዎች የት እንደማገኛቸውና ከሱም የትብበር ደብዳቤ ለመረጃ ሰጭዎች እንዲጽፍልኝ ጠየቅሁት፡፡ አቶ ካማም ጉዳዩን ተረድቶ ሁለት ባለሞያዎች ከአንድ ቪዲዮ ካሜራው ጋር እና ተፈጥሮዊ ቅንብር መቼት የሚያዘጋጁልኝ አስር ሰዎች ለሦስት ቀን ያህል መደበልኝ፡፡ እንዲሁም ለመረጃ ሰጪዎች በየስማቸው በምፈልግበት ሰዓት እንደሚፅፍልኝ ፍቃደኛነቱን ገለጸልኝ፡፡

በእነዚህ በተፈቀዱልኝ ሦስት ቀናት ተጠቅሜ በጥናቱ ዘዴ ላይ እንደተገለፀው የሠርጉንና የለቅሶውን ትውን ጥበባት በተፈጥሮአዊ መቼታቸው የቃልቻውን ክብረ በዓል ትውን ጥበባት ደግሞ በተመደቡልኝ ሰዎች አማካይነት በተፈጥሮዊ ቅንብር መቼት በየቀበሌው (ኮብ፣ ሚያህና ጊሊት) እየተዘዋወርኩ በቪድዮ ቀርጬና ተመልክቼ ጨረስሁ፡፡ ከዚያ ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ወደ ቃለ መጠይቁ ገባሁ፡፡ ቃለ መጠይቅ ሳደርግ የአማርኛ ቋንቋ መናገር የማይችሉትን በአስተርጓሚ በመጠቀም በቤንቸኛ ቋንቋ አማርኛ ቋንቋ መናገር የሚችሉትን ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ በመጠቀም መረጃዎችን ሰበሰብሁ፡፡ ከነዚህ መካከል ሚያህ ቀበሌ የሠርጉን ትውን ጥበባት በተፈጥሮአዊ መቼታቸው ልቀርፅ በሄድኩበት ወቅት በአጋጣሚ ሠርጉ ቦታ ላይ ሦስት የባህል አዋቂ ሠዎችን (አበሽ ቱዩ፣ በላይ አዲሱ እና ቦጁ ቶዩ) በማህበረሰቡ ጥቆማ አገኘሁና በአስተርጓሚ ከድር ሸባ አማካይነት ተግባብተን የምፈልገውን መረጃ እየመረጥኩ ሰበሰብሁኝ፡፡ ከመስክ አስራ አምስት ቀን ቆይታ በኋላ ደግሞ ወደ ዞኑ የባሕልና ማስታወቂያ ቢሮ በመመለስ መረጃ የሚሰጡኝን ሠዎች እንዲጠቁሙኝ አደረግሁ፡፡ ይህን ያደረግሁበት ምክንያት ቀን የሰበሰብሁትን መረጃ ማታ በማዳምጥበትና በማነብበት ወቅት የምፈልገው መረጃ የተሟላ ሆኖ ስላላገኘሁት ነው፡፡ ከዚያ የባሕል አዋቂ የተባሉን ሠዎች አቶ ሻንቆ ጋኪናስንና አቶ ኩንዲሳ ፈርኪን ጠቆሙኝ፡፡ እነዚህ ሠዎች

ባሉበት ቦታ ድረስ ሄጄ ቃለ መጠይቅ አድርጌ ስጨርስ ሌላ መረጃ የሚሰጠኝ ሰው እንዲጠቁሙኝ ባናገርኳቸው መሠረት ሌሎች ሠዎችን (ሰለሞን ፈጠነን፣ አዳሙ ሀንቲያብን እና ሀብታሙ ኮምትኬትን) ጠቆሙኝ፡፡ የተነገሩኝን ሠዎችም አድራሻቸውንና ስማቸውን መዝግቤ በመያዝና ያሉበት ቦታ ድረስ በመሄድ በቀጠሮና በአጋጣሚ ቃለ መጠይቅ እያደረግሁ ይሆናሉ ያልኳቸውን መረጃዎች መርጬ ሰበሰብሁ፡፡

አማርኛ ቋንቋ መናገር የማይችሉትን ሰዎች ቃለ መጠይቅ በማደርግበት ወቅት በቦታው በመገኘት ከመረጃ ሰጭዎች ጋር ከቤንችኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ ከአማርኛ ወደ ቤንቸኛ ቋንቋ እየተረጎመ ያግባባን የማህበረሰቡ ተወላጅ የሆነው ወጣት ከድር ሸባ ነው፡፡ ይህ ወጣት የደቡብ ቤንች ወረዳ በባህል እና ማስታወቂያ ቢሮ ምክትል ጸሐፊ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የአገር ውስጥ እና የውጭ አገር ሰዎች ለጉብኝት ሲሄዱ በተርጓሚነት ይሰራል፡፡ የማህበረሰቡ አባላት ሀገረሰባዊ ሙዚቃዎችን በሚያቀርቡበት ወቅት የሚጠቀሙባቸውን ግጥሞች በመተርጎም የተባበሩኝ ደግሞ አዳሙ ሀንቲያ እና ሀብታሙ ኮምትኬት የሚባሉ ሁለት የአካባቢው ተወላጅ የሆኑና የአማርኛ ቋንቋ የሚችሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ሰዎች በዋናነት ተቀጥረው የሚሰሩት በዞኑ መገናኛ ብዙሀን ቢሮ በቋንቋ ተርጓሚነት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተገለፀው መልኩ እስከ ግንቦት 6 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ መረጃዎችን ከሰበሰብሁ በኋላ ግንቦት 8 ቀን 2003 ዓ.ም ከጥናቱ ቦታ ተነስቼ ግንቦት 10 ቀን 2003 ዓ.ም አዲስ አበባ ገባሁ፡፡ ከዚያም በቴፕ ካሴት የተቀረፁትን ቃለ መጠይቆች ወደ ፅሁፍ ቀየርሁ፡፡

## 1.10. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

ይህን ጥናት በማጠናበት ወቅት በመስክ ቆይታዬ የተለያዩ ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡ ከገጠሙኝ ችግሮች መካከል፡-

1. ስለ ማህበረሰቡ ባህል በቂ እውቀት ያላቸው መረጃ አቀባዮችን እንደተፈለገው እና እንደታቀደው አለማግኘት፡፡ ታሪክ አዋቂዎች በአብዛኛው ባለአባት (ባለቃልቻ[1]) ስለሆኑ ቀርቦ ማነጋገር አለመቻል፡፡ ይህም የሆነው ቃልቻው የማይፈልገውን ምግብ (ጎመን፣ በግና የጤፍ እንጀራ) በልተሻል የሚል ጥርጣሬ ሥላለባቸው መንፈሳችን ይረክሳል ብሎ ማመን ነበር፡፡ ይህንን ችግር ለመቀነስ የባለቃልቻውን የቅርብ አገልጋዮች (ወይዘሶች) የሄድሁበትን አላማ በግልፅ በማስረዳት እነሱ ጠይቀውና ተረድተው እንዲያነጋግሩኝ ማድረግ ነበር፡፡

2. የመረጃ ሠጪዎች በቀጠሮአቸው ስዓትና ቦታ አለመገኘትና ከተገኙ በኋላም ነገ ይላሉ፤ ነገ ስጠይቃቸው ከነገ በኋላ እያሉ ቢያንስ አንድ ሠው ለማግኘት የሦስት እና የአራት ቀን ቀጠሮ ማስያዝ፡፡ በመጨረሻ በቀጠሮአቸው ሣይገኙ መጥፋት ነበር፡፡ ይህን ችግር ለማቃለልም መረጃ ሰጭዎች ይገኙበታል የተባለው ቦታ ድረስ ያለ ምንም ቀጠሮ ከወረዳው የትብብር ደብዳቤ ይዤ በመሄድ በአጋጣሚ ጠይቄአለሁ፡፡ ለምሳሌ፡- ገዛኸኝ አባተ ለተባለ መረጃ አቀባይ ያለቀጠሮ ከቢሮው ድረስ በመሄድ ቃለመጠይቅ አድርጌለታለሁ፡፡

3. ቃልቻ በሚነግስበት ጊዜ የሚደረገውን የጭፈራ ሥርዓት በተፈጥሮዊ መቼቱ ማግኘት ስላልቻልሁ ተፈጥሮዊ ቅንብር መቼት ለማዘጋጀት ሥጠይቃቸው ፍቃደኛ አለመሆን፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ ዘንድ ቃልቻ የሚነግሠው የበፊቱ ባለቃልቻ ከሞተ ከሦስተኛው ቀን ጀምሮ ስለሆነ ይህ ሚርት ነው ባለው ባለቃልቻ ላይ ስለዚህ አይቻልም ነበር ያሉኝ፡፡ ይህን ችግር ለማቃለል የወሠድሁት የመፍትሔ ስለሥርዓቱና ስለክዋኔው አስመልክቶ ያውቃሉ የተባሉ የተለያዩ የባህልና የታሪክ አዋቂ ሰዎችን በመጠየቅ ክፍተቱን ሞልቻለሁ፡፡

4. አንዳንድ በቃልቻ ጭፈራ ወቅት የሚጠቀሙባቸውን የሙዚቃ መሳሪያዎች ለማየትም ሆነ ፎቶ ግራፍ ለማንሳት ባለቤቶች አለመፍቀድ ነበር፡፡ ይህን ችግር ለማቃለል ስለቁሱ ያውቃሉ የተባሉ ሰዎችን ቃለመጠይቅ በማደረግ ክፍተቱን መሙላት ተችሏል፡፡

---

[1] "ባለአባት" ማለት በማህበረሰቡ ቋንቋ "ባለቃልቻ" ማለት ስለሆነ በጥናቱ ውስጥም "ባለቃልቻ" የሚለውን ቃል ተጠቅሜያለሁ፡፡

5. ቃለ መጠይቅ የሚደረግላቸው መረጃ ሠጪዎች ድምፃችን ከተቀረፀን መናገር አንችልም ብሎ በማሠብ ለመቀረፅ ፍቃደኛ አለመሆን። ለዚህ ችግርም የተወሰደው መፍትሔ ሁለት ነገሮች ነበሩ። አንደኛው የራሴን ድምፅ በፊታቸው ቀርጬ በማሰማት ምንም አይነት የንግግር ችግር እንዳልገጠመኝ በማሳመን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በተቻለ መጠን ማስታወሻዎችን በመያዝ ችግሩን አቃልያለሁ። ከዚህ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅ የሚደረግላቸው መረጃ ሰጭዎች ፎቶ ግራፍ ለመነሣት አለመፍቀድ ነበር። በዚህ ጊዜ ፎቶ ግራፍ መነሳታቸው ምንም ችግር እንደሌለው ደጋግሜ ለማሳመን ብሞክርም ፈቃደኛ ሊሆኑ ስላልቻሉ ማንሳት አልቻልሁም። ምክንያቱም አንድን መረጃ አቀባይ ያለፈቃዱ ምንም ዓይነት መረጃ መውሰድ የጥናቱ ህግ ስለማይፈቅድ ጭምር ነው።

6. ለባህሉና ለቋንቋው እንግዳ በመሆኔ በቀላሉ መግባባት አለመቻል። ማለትም በአስተርጓሚዎች ሥጠይቃቸው በትክክል አላማውን አለመረዳት እና ግልጽ ሆኖ መረጃውን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ነበር። በዚህ ጊዜ እኔና እነሱን የሚለየን የእኔ የተለያየ ቋንቋ መናገራችን እንጂ እኔም እንደ እነሱ የራሴ ባህል እና እምነት ስላለኝ በእነሱ ባህል ለመቀለድ እንዳልሄድሁ በአስተርጓሚዎች አማካይነት በግልፅ በማስረዳት መረጃውን ለማግኘት ችያለሁ።

7. ጥናቱ የተካሄደበትን አካባቢያዊ ዳራ ለመግለፅ የሚያስችሉ በቂ የሆኑ የጽሑፍ መረጃዎችን አለማግኘት ነበር። ምክንያቱም ይህ ጉዳይ የሚመለከታቸው የዞኑ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ለምሳሌ፡- የዞኑ የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ የህዝብ ቆጠራ ቢሮና የዞኑ አስተዳደር ዋና ጽህፈት ቤት ለጥናቱ የሚያገለግል ሙሉ በሙሉ አስተማማኝ የሆነ መረጃ የሌላቸው መሆኑ ነው። በተወሰነ ደረጃ ከዞኑ የህዝብ ቆጠራ የተገኙ መረጃዎች ቢኖሩ እንኳ በግምት ከ1999 ሰነድ ላይ በመነሳት የተቀመጡ መሆናቸው። እንዲሁም ሴት መረጃ አቀባዮችን ማግኘት አለመቻል ነበር። የዚህ ምክንያት አስተርጓሚዎቼ ወንድ ስለሆኑ በባህሉ ደግሞ ወንድ ልጅ አንድ ያገባችን ሴት ቀርቦ ማነጋገር አይችልም።

## 1.11. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአምስት ምዕራፎች የተደራጀ ነው፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ መግቢያ ሲሆን በውስጡ የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አነሣሽ ምክንያት፣ የጥናቱን ዓላማ፣ የጥናቱን ወሰን፣ የጥናቱን ውጤት ጠቀሜታ፣ የመረጃ መሠብሠብያ ዘዴ፣ የመረጃ አተናተን ዘዴ፣ የመስክ ቆይታ፣ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ተካተዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ተደርጓል፡፡ በምዕራፍ ሦስት ጥናቱ የተካሔደበት አካባቢያዊ ዳራ ተገልጿል፡፡ በምዕራፍ አራት የቤንች ማህበረሰብ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚከወኗቸው ሀገረሰባዊ ዳንስና ሀገረሰባዊ ሙዚቃ አውዳዊ ክዋኔ ገለፃ ተደርጓል፡፡ በምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ እና ይሁንታ ቀርቧል፡፡ በመጨረሻም አባሪዎች ተያይዘዋል፡፡

# 2. ንድፈ ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

## 2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ

### 2.1.1. የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ምንነት

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚከወኑ ክዋኔዎች ሲሆኑ በተለይ ድራማ፣ ዳንስ እና ጭፈራ ላይ ያተኩራሉ" በማለት Encarta የተባለው መዝገበ ቃላት ገልጾታል። ይህ ሀሳብ ከተለያዩ ምሁራን ብያኔ ጋር ይመሳሰላል። ከነዚህ መካከል ፈቃደ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሚል "የጥቅል ስም የምንጠራው ሀገረሰባዊውን ሙዚቃ፣ ሀገረሰባዊውን ዳንስ እና ሀገረሰባዊውን ድራማ የሚያጠናውን ሞያ እና የሚጠኑትን ነገሮች ነው" ሲሉ (ፈቃደ፣1991፡12) ገልፀውታል።

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ማለት በውስጡ ዳንስን፣ ዝማሬን (ሙዚቃን)፣ የማስመሰል ትወናን፣ የድራማ እንቅስቃሴዎችን እና የተለያዩ መሳሪያዎች በመጠቀም የሚጫወቱትን ጨዋታዎች አካቶ የያዘ ነው ሲሉ Bruno ያትታሉ።

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ የአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ እና ሥርዓት መግለጫ ሲሆን በውስጡ ብዙ ነገሮችን አካቶ ይዟል። ይህም ማለት ከላይ እንደተገለፀው አንድን ማህበረሰብ ሊገልፅ የሚችለውን ሀገረሰባዊውን ሙዚቃ፣ ሀገረሰባዊውን ዳንስ እና ሀገረሰባዊውን ድራማ የሚይዝ ነው ሲሉ (Dorson,1972: 2-3፣1975፡ 144) ገልፀውታል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ዓይነቶች የእያንዳንዳቸው የሆኑ መገለጫ ባህሪ ቢኖሯቸውም እንኳ አንዱን ከአንዱ ነጥሎ ማጥናት (ማየት) ግን አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም አንዱ ሲነካ ሌላው ብቅ ማለቱ የማይቀር ጉዳይ ስለሆነ። ለምሳሌ፡- ሀገረሰባዊ ዳንስ ሲነሳ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ አብሮ መምጣቱ የማይቀር ነው። አንድ ዳንስ የሚደነሰው በሙዚቃና በሙዚቃ መሳሪያ ታጅቦ ሲሆን አንድ ሙዚቃ ሲቀርብም የግድ በተለያዩ እንቅስቃሴዎች ስለሚታጀብ ነው።

### 2.1.1.1 ሀገረሰባዊ ሙዚቃ

ሀገረሰባዊ ሙዚቃ አንድ ማህበረሰብ ባህላዊ ልብስ ለብሶ እና በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ታጅቦ በተለያየ አጋጥሚ ለተለያየ አላማ በራሱ መንገድ የሚከወነው ነው። ይህ ሙዚቃ የሚከወንበት የራሱ የሆነ የመከወኛ አጋጣሚ ያለው ሲሆን እንደሚከወንበት አጋጣሚም አከዋወኑ የተለያየ ነው ሲሉ (Larey,1990፣ 96-97) ገልፀውታል። ማህበረሰቡ ሙዚቃውን የሚከውነው ከመዝናኛነት በተጨማሪ የእራሱን ስሜት፣ ፍላጎት፣ ደስታ፣ ሀዘን እና ማንነት ለሌላው ማህበረሰብ ለማካፈል ወይም ለማንፀባረቅ ነው ሲሉ (እዝራ አባተ 1996፣ 1-5) ገልፀውታል።

ሀገረሰባዊ ሙዚቃ የአንድን ሀገር ህዝብ ወይም ብሔር ከሌላኛው ለመለየት የሚያስችል ነው። ይህ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ የሚከወነው በአብዛኛው በማህበራዊና ኢኮኖሚ ደረጃቸው አነስተኛ በሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ሲሆን በተለይ በገጠር አካባቢዎች ሲዘወተር ይስተዋላል። ነገር ግን እነዚህ ከዋኞች በማህበረሰቡ ውስጥ ታዋቂ ከመሆናቸው ባሻገር የሙዚቃ ሙያ ባይኖራቸውም የሚያዜሙት ሙዚቃ ከዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው (ለምሳሌ:- ከክብረ በዓላቸው፣ ከስራቸው፣ ከእምነታቸው፣ ከልጅ አስተዳደጋቸው . . . ወዘተ) ጋር በቀጥታ የተገናኘ ነው።

ሀገረሰባዊ ሙዚቃ ዜማ ባለው ስልት የሚከወን ሲሆን የማህበራዊ ማንነትን ማጠናከሪያና መገንቢያ ነው። ይህ ሙዚቃ እንደ ዘመናዊው ሙዚቃ በፅሁፍ የሚሸጋገር ሳይሆን ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የሚተላለፍ በመሆኑ የተለዋዋጭነት ባህሪ ይታይበታል። በፅሁፍ መልክ ከእነግጥማቸው ተያይዘው የሚከወኑትን ሳይሆን በቃል የሚከወኑትን ሙዚቃዎችና ዝማሬዎች ነው። በዚህ ምክንያት የሙዚቃው ቅርፅና ሥርዓት ከጊዜ ወደ ጊዜ በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ሊኖረው ይችላል። እ.ኤ.አ. በ1954 ዓ.ም በወጣው የዓለም አቀፍ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ ካውንስል (International Folk Music Council (IFMC)) "የሀገረሰባዊ ሙዚቃን በቃላት ሥርዓትና አቀማመጥ ላይ ብቻ ትኩረት ሰጥቶ ይበይነዋል። እንደካውንስሉ ብያኔ 'ሀገረሰባዊ ሙዚቃ በልማዳዊ መንገድ ተፈጥሮ በቃል የሚተላለፍና በሂደት የሚለወጥ ነው'" ሲሉ ይገልፁታል Rosenberg (1996፡ 340)።

ሀገረሰባዊ ሙዚቃ ከሌሎች ታዋቂና ዘመናዊ ሙዚቃ የሚወርሳቸው ባህርያት እንዳሉ ሁኖ ሙዚቃውን ለመለየት የሚያስችል መስፈርት ማዘጋጀት ወይም ድንበር ማበጀት ግን አዳጋች ሲሆን ይታያል። ነገር ግን አንድ አንድ ምሁራን ሀገረሰባዊ ሙዚቃን ከዘመናዊ ሙዚቃ በተለያየ መልኩ ይለዩታል። ከነዚህም መካከል Bruno "ሀገረሰባዊ ሙዚቃ የሚከወነው ምንም እንኳን ተሰጥኦ ባላቸው ሰዎች ቢሆንም በባህሪው ግን ቀላልና አጭር የስልት ጥበብን መከተሉ ከዘመናዊው የሙዚቃ አይነት ይለያል" ሲሉ Bruno (2008፡13) ገልፀውታል። በአጠቃላይ ሲታይ ግን ሀገረሰባዊ ሙዚቃ በቃል እንደ መቅረቡ መጠን ይሄ ነው የሚባል አንድ ባለቤት የለውም።

### 2.1.1.2. ሀገረሰባዊ ዳንስ

ሀገረሰባዊ ዳንስ በአንድ ክልል ወይም ሀገር የሚኖሩ እና ተመሳሳይ ቋንቋ የሚናገሩ ህዝቦች በአንድ ላይ ተሰባስበው ባህላዊ ጥበብ በተሞላበት መልኩ የሚከውኑት ዳንስ ነው። ይህ ሀገረሰባዊ ዳንስ በዋናነት በገጠር በሚኖረው ማህበረሰብ ዘንድ የተለያዩ በዓላት በሚከበሩበትና የተለያዩ ዝግጅቶች በሚዘጋጁበት ወቅት በተወሰኑ ሙዚቃዎች እና ሰዎች ታጅቦ የሚከወን ዳንስ ነው። ይህን ሀሳብ አስመልክተው የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔ የሰጡ ሲሆን ከእነዚህ መካከል Suzanne የተባሉ ምሁር "ሀገረሰባዊ ዳንስ በግብርና ስራ ላይ ተሰማርተው በገጠር የሚኖሩ ሰዎች በተለያዩ አጋጣሚዎች በጋራ የሚጨፍሩት ክዋኔ ሀገረሰባዊ ዳንስ ተብሎ ይበየናል" ሲሉ ገልፀውታል Suzanne (2008፡ 1)።

ከላይ ካለው ሀሳብ እንደምንረዳው ይህ የዳንስ አይነት በተለያዩ አጋጣሚዎች በልደት፣ በዓመታዊ ክብረ በዓላት፣ በእምነት ቦታዎች፣ በግላዊ የህይወት ኡደት (በውልደት፣ በግዝረት፣ በሰርግ እና በሞት)፣ በስራ ቦታ፣ በተለያዩ የመዝናኛና የዝግጅት ቦታዎች በአንድ በተወሰነ የማህበረሰብ አባላት የሚከወን ነው።

ሀገረሰባዊ ዳንሶች በባህላዊ ክብረ በዓላት፣ በእምነት ቦታዎች፣ በደስታና በሀዘን ጊዜ እንዲሁም በግብርና ስራዎች ላይ የሚጨፈሩበት ዋነኛ ተግባራቸው ለማዝናናት እና በማህበረሰቡ አባላት መካከል የትብብር መንፈስ ለመፍጠርና ለማዳበር ነው። እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላት ዳንሱን በሚከውኑበት ወቅት ስሜታቸውን፣ እምነታቸውን፣ አመለካከታቸውን እና ፍላጎታቸውን ለመግለጫነት ይጠቀሙበታል ሲሉ Matthews

(1990፡ 102) ገልጸውታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ግን በአሁኑ ሰዓት እነዚህ ዳንሶች ለአንድ ማህበረሰብ መገለጫና አንዱን ማህበረሰብ ከሌላኛው መለያ በመሆን ጉልህ ሚና እየሰጡ ይገኛሉ:: እያንዳንዱ የዳንስ እንቅስቃሴ የራሱ የሆነ ትዕምርታዊ ውክልና አለው ሲሉ (Suzanne 2008,4፣ በክላንድ፣1983፡) ገልፀውታል፡፡

ሀገረሰባዊ ዳንስ ከሌሎች የዳንስ አይነቶች የሚለይበት የራሱ የሆነ ባህሪ አለው:: ከእነዚህ ባህርያት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡ አንደኛ በአንድ ተመሳሳይ የኢኮኖሚ ደረጃ እና የመኖሪያ አካባቢ በሚገኙ ሰዎች የሚከወን መሆኑ፤ ሁለተኛ ማንኛውም የማህበረሰብ ክፍል አባላት እንዲሳተፍ ማስቻሉ እና ሶስተኛ ከትውልድ ወደ ትውልድ በዳንስ ባለሙያ ሳይሆን በልምድ መተላለፉ ነው::

### 2.1.1.3 ሀገረሰባዊ ድራማ

ሀገረሰባዊ ድራማ አንድ ማህበረሰብ ባህላዊ ልብስ ለብሶ በተለያዩ አጋጥሚዎች ለተለያየ አላማ በራሱ መንገድ የሚከውነው የድራማ ዓይነት ነው፡፡ ይህ ድራማ አንድ ነገር ሲከወን የሚታዩ እንቅስቃሴዎችን ትኩረት ሰጥተን እንድንመለከታቸው የሚያደርግ ጥበብ ነው ሲሉ (Turner and McArthur,1990፡ 85) ገልጸውታል፡፡

ከዚህ በላይ በተደረገው የንድፈ ሀሳብ ቅኝት ላይ ሶስቱ የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ዓይነቶች ቅኝት ይደረግባቸው እንጂ ጥናቱ ግን ካለው ጊዜና አቅም አንፃር ትኩረት ሰጥቶ የሚመረምረው ሀገረሰባዊ ዳንስንና ሀገረሰባዊ ሙዚቃን ነው።

## 2.2. ጥናቱ የሚከተላቸው ንድፈ-ሀሳቦች (Theoretical Frame works)

ይህ ጥናት Performance, Contextual እና Functional ንድፈ-ሀሳቦችን እንደ አመችነታቸው አጣምሮ ወይም ለየብቻቸው የሚጠቀም ሲሆን በዋናነት ግን የPerformance Centered እና Contextual Approach የጥናት ዘዴዎችን ይከተላል፡፡

እነዚህ ንድፈ-ሀሳቦች የተመረጡበት ምክንያት ጥናቱ በዋናነት የሚመለከታቸው ከሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት መካከል ሀገረሰባዊ ሙዚቃን እና ሀገረሰባዊ ዳንስን ነው፡፡ እነዚህ ትውን ጥበባት ለምን? በማን? እንዴት? የት? እና መቼ? እንደሚከወኑ ትኩረት

ሰጥቶ ስለሚመረምር ነው። ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ከሚጠናባቸው አንፃሮች መካከል 1ኛ. ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን እንደ አንድ የፎክሎር ዘርፍ በመገኛ ቦታቸው በመገኘት መመልከት እና መሰብሰብ፤ 2ኛ. ለተሰበሰቡት ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ከባህሉ ባለቤቶች አንጻር ገለፃ መስጠት፤ 3ኛ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በጋራ መሰራትን፣ መግባባትን እና መከወንን የሚጠይቁ በመሆናቸው ማህበራዊ ተግባራቸውን ማየት፤ 4ኛ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ የአንድን ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ እንዴት እንደሚገለፁት በመዳሰስ ከምሁራን ንድፈ-ሃሳብ አንፃር መግለፅ ነው።

## 2.2.1. ክዋኔ ተኮር ቲወሪ

በአሁኑ ዘመን ክዋኔ ተኮር ቲወሪ ለመስክ ጥናት እና ምርምር በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን (ለምሳሌ፡- Bauman, Sims and Stephens) የገለፁት ሲሆን በተለይ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ለማጥናት ከመስክ መረጃውን የሚሰበስቡ አጥኝዎች መጠቀም እንዳለባቸው ያትታሉ።

የክዋኔ ተኮር ቲወሪ በዋነኛነት በመስክ ጥናት እና ምርምር ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ስለተጠኝው ማህበረሰብ ወይም ቡድን ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ዝርዝር መረጃ ከእነነባራዊ ሁኔታቸው (ከእነክዋኔያቸው) ለመሰብሰብና ለመገንዘብ ይረዳናል:: እንደዚህ ንድፈ-ሀሳብ አገላለፅ የአንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ማጥናት ካስፈለገ ቢያንስ ክዋኔ፣ የሚከወኑበት አጋጣሚ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ የክዋኔ ቦታዊና ማህበራዊ አውድ ወዘተ... ያካተተ መሆን እንዳለበት የመስኩ ምሁራን ያትታሉ (Bauman 1977፣ vansina1985፣ Sims and Stephens 2005)። ከዚህ ጋር ተያይዞ Performance Theory የአንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በተከታታይ ምዘና እና አስታያየት በዘወትር የማህበራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴዎች የዳበሩ፣ በጋራ የሚፈጠሩ፣ ከከዋኞች እና ከታዳሚዎች ጋር የሚያግባቡ መንገዶች እንደሆኑ ተገልጿል (Sims and Stephens, 2005፡128-133)::

በመሆኑም የክዋኔው ውጤታማነትና ግብ መችነት የሚወሰነው በከዋኞችና በታዳሚዎች ብቃት፣ እድሜ፣ ፆታ፣ ባህሪና ሚና ነው። እነዚህ ነገሮች በወቅቱ በሚከሰቱ ወይም ባሉ ዓውዳዊ ነገሮች ላይ የተመሰረቱ እንደሆኑ ምሁራኑ ያስረዳሉ ፣ (Sims and Stephens, 2005፡ 132)::

ስለዚህ የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት አጥኚዎች ትኩረት መስጠት ያለባቸው ዋናው ጉዳይ በከዋኞች አጠቃላይ እንቅስቃሴ፣ የከዋኞችን ሥነ-ጥበባዊ ግንኙነት እንዲሁም ከዋኞች እርስ በእርሳቸው መቼ? የት? ከማን ጋር? እንዴት? እና ለምን? መስተጋብር እንደሚመሰርቱ መሆን አለበት ሲሉ የPerformance theory አቀንቃኝ የሆኑት (Sims and Stephens, 2005:134) ይጠቁማሉ:: "Folklorists pay attention to the performed act of expressive, artistic communication, the when, where, with whom, how, and why people communicate with each other." ይህ ሀሳብ አንድ የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት አጥኚ ከመልዕክቱ (text) በተጨማሪ የመልዕክቶችን ስብጥር ወይም ውህደት (texture) እና ከዋኞች ከአውዱ (context) ጋር ካላቸው ግንኙነት አንፃር መመልከት እንዳለበት ያስረዳል:: ከዚህ አኳያ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት የሚያጠነጥኑት በክዋኔው ላይ ስለሆነ አንድ የፎክሎር አጥኚም ከዋኞች ያላቸውን ማህበራዊና ባህላዊ እሴት ሳይሆን መመርመር ያለበት ከዋኞች በተግባር የሚፈጽሙትን ማህበራዊና ባህላዊ እንቅስቃሴ በትኩረትና በቅርበት ማየት ነው ሲሉ የፎክሎር ተመራማሪዎቹ ( Sims and Stephens, 2005:134) ያሳስባሉ:: "... it is important to keep in mind that folklore is something we do,not just something we possess. Performance study foregrounds this perspective on the active sharing of contemporary folklore."

በአጠቃላይ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት የማህበረሰቡን እሴት፣ መስተጋብር፣ ልማት፣ አስተዳደር፣ ባህል እና ስነ-ልቦና የሚጠነሰሱባቸው እና የሚተገበሩባቸው መድረኮች ናቸው:: ይህ በመሆኑ አንድ ክዋኔ ለመከወን የግድ የሚከወንበት መድረክና የተሳታፊዎች ማለትም የከዋኝና የታዳሚ ግንኙነት መኖር አለበት:: "In order for a performance to "happen," a recognized setting must exist (we have to know a performance is taking place) and participants (performers and audience) must be present" (Sims and Stephens, 2005, 128):: በተለይ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱ በቡድን በሚከወኑበት ወቅት የከዋኝና የታዳሚ ቁርኝት እንዲኖር ያስፈልጋል። ይህን ሀሳብ Bawman እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል።

> The term performance was employed there, as it was by several of contributors to the collection, because it conveyed a dual sense of artistic action- the doing of folklore-and artistic event- the

performance situatiion, involving performer, art form,audience, and setting-both of which are centeral to the developing performance approch to folklore. (Bawman,1977፡ 209)

ከዚህ አንጻር የአንድ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት አጥኝ እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ሀሳቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት ክዋኔውን ከእነ አከዋወኑ በቅርበትና በጥልቀት ማጤን አለበት:: ይህን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ጥናቱ በሚያተኩርበት አካባቢ የሚከወኑት የሀገረሰባዊ ሙዚቃ እና የሀገረሰባዊ ዳንስ ክዋኔ ምን እንደሚመስል በጥናቱ አራተኛ ክፍል ተገልጿል፡፡

### 2.2.1.1 የመከወኛ አጋጣሚ

አንድ የሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ ቅርጽ ለመከወን የራሱ የሆነ የመከወኛ አጋጣሚ ይፈልጋል፡፡ ይህም ማለት ለመከወን የራሱ ሆነ ምክንያት ይኖረዋል እንጂ በዘፈቀደ የትም ቦታና ጊዜ አይዘፈንም ወይም አይደነስም ማለት ነው፡፡ ይህን ሀሳብ አስመልክተው Vansina እንዲህ ሲሉ ገልፀውታል፡፡ Performances are not produced at random times. The occasions for performances are limited and can be observed in the Field (Vansina, 1985፡ 39). ከዚህ ሃሳብ እንደምንረዳው ሰርግ ሣይኖር አይጨፈርም፤ ስራ ሣይኖር የስራ ዘፈን አይዘፈንም፣ የእምነት ክብረ በዓል ሳይኖር የእምነት መዝሙር አይዘመርም፣ የአምልኮ ቦታ ሳይኖር አይመለክም ማለት ነው፡፡

በመሆኑም ማንኛውም የትውን ጥበባት አይነት ለመከወን የግድ የራሱ የሆነ አነሳሽ ምክንያት ሊኖረው ይገባል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ሀሳብ ሁሉ ጥናቱ በሚያተኩርበት አካባቢ የሚከወነው ሀገረሰባዊ ሙዚቃም ሆነ ሀገረሰባዊ ዳንስ ለመከወን በማህበረሰቡ ዘንድ የሚፈጠር የራሱ ሆነ አጋጣሚ አለው፡፡

### 2.2.1.2 ከዋኝ

የአንድ ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ከሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮች መካከል የከዋኞች መኖር አንዱ ነው፡፡ እነዚህ ከዋኞች ግን እንደሚኖሩበት ማህበረሰብ የተለያየ ማህበራዊ ደረጃ ያላቸው ናቸው፡፡ እንደ ሩት

ፊነጋን አገላለፅ እነዚህ ከዋኞች ሙያዊ ስልጠና በመውሰድ በክዋኔ ሙያ ብቻ የሚተዳደሩ፣ ከሙያቸው በተጓዳኝ የሚሰሩ ተብለው የሚመደቡ ናቸው (Finnegan,1970:171-215)። እንዲሁም ከዋኞች በሙያው የሰለጠኑ ወይም ያልሰለጠኑ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህን ሀሳብ ቫንሲና እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል። "Performers could be specialists or not." (Vansina, 1985፡ 36).

እንደ ማህበረሰቡ ባህል እና እንደሚከወኑበት አጋጣሚ የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ከዋኞች በእድሜ፣ በፆታ እና በመሳሰሉት ነገሮች ሊከፋፈሉ ይችላሉ። ይህን ሀሳብ በተመለከተ ፊነጋን እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል። "Performers are also of certain ages, gender, social position, training, reputation, and competence all needing investigation" (Finnegan,1992: 90).

ጥናቱ በሚያተኩርበት ማህበረሰብ ውስጥ የሀገረሰባዊ ሙዚቃና የሀገረሰባዊ ዳንስ ከዋኞች እንደሚከወኑበት አጋጣሚ በጾታና በእድሜ የተከፋፈሉ ናቸው። እነዚህ ከዋኞች ሙያውን የሚያገኙት ከተወለዱበት ማህበረሰብ በልምድ ነው።

### 2.2.1.3 ታዳሚ

እንደ ማህበረሰቡ ባህልና እምነት የተለያየ ቢሆንም ማንኛውም ትውን ጥባባት በሚከወኑበት ወቅት የራሳቸው የሆኑ ከዋኞች እንዳሏቸው ሁሉ የራሳቸው የሆኑ ታዳሚዎች አሏቸው። ምክንያቱም ታዳሚዎች በክዋኔ ወቅት የሚተገብሯቸው የራሳቸው የሆኑ ሚናዎች አሏቸው። ይህ ማለት በክዋኔ ወቅት ክዋኔውን ለመመልከት፣ ለማዳመጥ፣ ለማድመቅ፣ ከዋኞችን ለማበረታታት እና ሲሰሳቱ ለማረም የሚመጡ ናቸው።

> ...an audience is involved some times the audience is really paret of the performance it selfe, as in songs for cheral singing or is to at times, as when alead singer performs partly as soloist, paretly as leader in a joint singing with the audience (Finnegan, 1977; 216).

### 2.2.1.4. አውዳዊ ቲወሪ

አውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ተከታታይ ጥናትና ምርምር የሚጠይቅ በመሆኑ በቤተ-መጽሐፍት የተወሰነውን የጥናት አቅጣጫ የቀየረ ሰፊ የጥናት ዘርፍ ያለው ንድፈ-ሀሳብ ነው:: ይህም ከረጅም ጊዜ በፊት በቤተ-መጽሐፍት ብቻ ተገድበው ሲጠኑ የነበሩ የፎክሎር ጥናቶች የተጠኙዎችን የክውኔ አውድ (performance context) ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ ወይም "ዶሮን ከእንቁላሏ ለይቶ" እንደ ማጥናት አይነት ስለነበር የጥናቶች ግኝቶች በከፊል ውጤታማ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የተቀየሰ ወይም የተፈጠረ ንድፈ-ሀሳብ ነው::

የክዋኔ አውድ የሚፈጠረው ወይም የሚኖረው ከዋኞች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን የሚከውኑባቸው ቦታዎች፣ ማህበራዊ ሁኔታዎች እንዲሁም በተመልካቾችና በከዋኞች መካከል መስተጋብር ሲፈጠር ወይም ሲኖር እንደሆነ (Sims and Stephens, 2005፡ 134) ይገልጻሉ:: ከዚህ ጋር በተያያዘ እነዚህ ታዋቂ የፎክሎር ምሁራን አውድ (context) ማለት ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሚከወኑበት ዙሪያ ያለ ማንኛውንም መልዕክትና ክዋኔ እንደሆነ ያስረዳሉ::

> The physical settings and social situations in which members of folk groups share folklore, as well as the relationships among audience members and performers, make up the context of the performance. ... Context refers to anything and everything that surrounds a text and performance (Sims and Stephens, 2005, 135).

ይሁንና የተለያዩ ምሁራን አውድ (context) የሚለውን ንድፈ-ሀሳብ በተለያየ መልኩ ሲበይኑት ይስተዋላል:: ከነዚህ መካከል Dundes የተባሉ ተመራማሪ አውድ ማለት አንድ ክዋኔ ሲካሄድ የሚታይበት ቦታ ነው ሲሉ ይገልፁታል:: Sims and Stephensን ደግሞ Hymes የተባለው ፎክሎሪስት ጠቅሰው አውድ ማለት የመግባቢያ ቦታ ነው ይላሉ:: እንዲሁም በአውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ ግንባር ቀደም የሆኑት ተመራማሪ Ben-Amos ደግሞ አውዶችን "ባህላዊ" አውድ (context of culture)ና "የሁኔታ" አውድ (context of situation) በማለት በሁለት ከፍለው እንደሚከተለው በይነዋቸዋል::

> The context of culture comprises the reference to, and the representation of, the shared knowledge of speakers, their conventions

> of conduct, belief systems, language metaphors and speech genres, their historical awareness, and ethical and judicial principles. Context of culture is the broadest framework for the perception and interpretation of folklore. In contrast, the situation is the narrowest, most direct context for speaking folklore. (Ben-Amos, 1993፡ 215-216).

ከላይ ካለው ሀሳብ እንደምንረዳው አንድ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ በሚጠናበት ጊዜ የትውን ጥበቡን መልዕክትና ለአንድ የማህበረሰብ ክፍል ያለውን ተግባር ከሚገኝበት አውድ ለይቶ በመገንዘብ ብቻ ሳይሆን የትውን ጥበቡን መልዕክትና ጠቀሜታ ከሚገኝበት ሰፊ የባህላዊ አውድ ጭምር አዋህዶ መሆን እንዳለበት ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት መልዕክቶች የአውዱ አንድ አካል እንደመሆናቸው መጠን የፎክሎር ተመራማሪዎች የጥናታቸውን መረጃና ውጤት ሲገልፁና ሲተነትኑ የክዋኔውን አውድ ተላብሰው ወይም በውስጣቸው አስርጸው መሆን አለበት:: ያለበለዚያ ደግሞ የክዋኔው ባለቤቶች የሚሰጡትን ትርጉም እንዳለ በመውሰድ (ያለምንም ግምገማ) ወይም መልዕክቱ በሚተላለፍበት አውድ ውስጥ ሆነው ከዋኞች ከሚያዩበት መነፀር አኳያ መሆን እንዳለበት የንድፈ ሃሳቡ አቀንቃኞች ያስገነዝባሉ::

> In studying a certain folk text we cannot simply lift it from the context and begin to understand its importance to a particular group accurately. It must be seen within a larger context, as part of a cultural system. In addition, ... as the text is an element of a group's folklore, the members of the group are the experts on what those items or practices mean, so the folklorist can't just walk away from the culture with an interpretation in good conscience or good scholarship and consider her work complete (Sims and Stephens, 2005፡137).

በአጠቃላይ አውዳዊ ንድፈ-ሀሳብ የሚያተኩረው የአንድ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብን መልዕክትና ፋይዳ ማወቅ የሚቻለው ትውን ጥበቡ የቀረበበትን ቦታዊ አውድ እና ማህበራዊ አውድ ጭምር በማጠቃለል ነው:: ለምሳሌ:- አንድ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ ሲከወን የሚከወንበትን አውድ፣ ጊዜ፣ ሁኔታ እና የከዋኞችንና የተመልካቾችን ስሜት ከባህላዊው ዳራው አኳያ መመልከት ያስፈልጋል:: ስለዚህ እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ሀሳቦች ከግምት ውስጥ በማስገባት ክዋኔውን ከእነሚከወንበት አውድ በቅርበትና በጥልቀት ማጤን ያስፈልጋል።

### 2.2.1.5 የክዋኔ ጠቋሚዎች

እያንዳንዱ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብ የራሱ የሆኑ የክዋኔ አጀማመርና አጨራረስ ሂደትን የሚያሳዩ ጠቋሚዎች አሉት፡፡ ይህ የሚሆነው ትውን ጥበባቱ በሚከወኑበት ወቅት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚታወቁ የክዋኔ ስርዓቶች ስላሏቸው ነው፡፡ ከነዚህ የማህበረሰብ ደንብ እና ስርዓት ሀገረሰባዊ ሙዚቃውም ሆነ ሀገረሰባዊ ዳንሱ ሊወጣ አይችልም፡፡ ይህን ሀሳብ Sims and Stephens እንዲህ ሲሉ ገልፀውታል፡፡ frequently, performances have clear settings and recognizable structures that indicate to participants that the performance is taking place. (Sims and Stephens, 2005፡128)

### 2.2.1.6. የመከወኛ ቁሶች

እንደ ማህበረሰቡ ባህልና እምነት የተለያዩ ይሁን እንጂ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሚከወኑበት ወቅት ለክዋኔዎች ማጀቢያነት (ማድመቂያነት) የሚውሉ አንዳንድ ቁሶች አሉ፡፡ እነዚህ ቁሶች ተራርቆ የሰፈረውን ማህበረሰብ በማግባባት በኩል ሰፊ የሆነ ድርሻ እንዳላቸው የመስኩ ምሁራን ያትታሉ (Finnegan, 1970፣ Vansina, 1985)፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ቁሶች ማህበረሰቡ የሚከተለውን እምነት፣ ያንጸባርቃሉ፤ ጀግንነት ይገልጻሉ፤ ከጥንት ጀምሮ የእሱነቱ መገለፃ የሆነውን የአለባበስ ስልት ያሳሉ፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ Vansina እንዲህ ሲሉ ይገልፁታል፡፡

> Objects as proof of a certain event or as mementos of a past happening are quite common. In the Hopi case mentioned earlier, we see the Hopi produce a feather shrine (tiponi) in 1938 as proof of an earlier agreement about the boundary between Navaho and Hopi. Wampum was used in the eastern United States in similar ways as proofs of treaties and clues of memory. Similarly a firebrand kept by an Anyi (Ivory Coast) family substantiated their ancient royal status. (Vansina, 1985፡ 44)

ጥናቱ በሚያተኩርበት አካባቢ በትውን ጥበባቱ ወቅት የሚጠቀሙባቸው ቁሶች አሉ፡፡ በእነዚህ ቁሶች ማህበረሰቡ ለአገሩ ያለውን ፍቅር፣ ለጠላቱ ያለውን ጀግንነት እና

አይበገሬነት በእጁ ጠብመንጃ፣ ጋሻና ጦር ይዞ በአገኛቸው አጋጣሚዎች ሁሉ በመከወን ስሜቱን ይገልፅባቸዋል።

በአጠቃላይ እስከ አሁን በተደረገው ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት መሰረት ማንኛውም ትውን ጥበብ በአንድ ማህበረሰብ ዘንድ ለመከወን የራሱ የሆነ ክዋኔ፣ ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ የመከወኛ አጋጣሚ እና የመከወኛ ቁስ ያስፈልገዋል። እንጂ ዝም ብሎ በማንኛውም ቦታ እና ጊዜ አይከወንም። በዚህ መሰረት በጥናቱ ውስጥ የቤንች ሀገረሰባዊ ዳንሶች እና ሙዚቃዎች እንደሚከወኑበት አጋጣሚ ተከፋፍለው በክፍል አራት ላይ ገለፃ ተደርጎባቸዋል።

## 2.3 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የሀገረሠባዊ ትውን ጥበባት ማለትም ዳንስን፣ ሙዚቃንና ድራማን አስመልክቶ ለሁለተኛ ዲግሪ የቀረበ ጥናት የተገኘው አንድ ብቻ ሲሆን ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች፣ በተለያዩ ጆርናሎች ላይ የወጡ ጽሑፎች እና በተለያዩ ሴሚናሮች ላይ የቀረቡ ሥራዎች ግን የተወሰኑ ተገኝተዋል።

ሁሉንም ጥናቶች በመጀመሪያ በሚያነሱት ርዕሠ ጉዳይ ተመሣሣይነት ለቅኝት አመቺ በሆነ መንገድ ለመመደብ ሞክሪያለሁ። በዚህ መሠረት ባህላዊ ሙዚቃን ያጠኑ፣ ባህላዊ ዳንስን ያጠኑ፣ አኗኗራቸውን ከባህላዊ ሙዚቃቸው ጋር አያይዘው ያጠኑ እና ሀገረሠባዊ ትውን ጥበባትን ያጠኑ ተብለው ተመድበው ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል። በአንድ ዓመተ ምህረት (በተመሳሳይ ዘመን) ከተጠኑት ጥናቶች በስተቀር አቀራረባቸው በተጠኑበት ዘመን ቅደም ተከተል መሠረት ነው።

### 2.3.1. ሀገረሰባዊ ዳንስን ያጠኑ

ሀገረሰባዊ ዳንስን አስመልክተው የተሠሩ ሥራዎችን ስቃኝ ለመጀመሪያም ሆነ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተጠኑ ጥናቶች አላገኘሁም። ነገር ግን በጆርናል ላይ ታትመው የወጡ ስራዎችና ያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት አንድ ያልታተመ ስራ አግኝቻለሁ። በዚህ ስራ የመጀመሪያው ሰው ሊሆን የሚችለው Martin (1968) “Dance type in Ethiopia” በሚል ርዕስ በJournal of the international Folk Music council. ውስጥ ያሳተመው

ስራ ነው። ይህ አጥኝ ትኩረት ያደረገው በኢትዮጵያ ያሉ የዳንስ አይነቶች ምን ያህል ተመሣሣይነት እንዳላቸው መግለፅ ላይ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ያለው አጥኝ ደግሞ Vadasy ሲሆን ሀገረሰባዊ ዳንስን አስመልክቶ ሶስት ተከታታይ ጥናቶችን በኢትዮጵያ ጥናት መፅሔት (Journal of Ethiopia Studies) ውስጥ አሣትሟል።

እነዚህ ስራዎች በታተሙበት ቅደም ተከተል መሠረት እንደሚከተለው ቀርበዋል። "Ethiopian Folk Dance" (1970) በሚል ርዕስ ባሣተመው ሥራ የተለያዩ የኢትዮጵያ ዳንሶችን ለማጥናት የተጀመረው በ1964 እ.ኤ.አ በሁለት ሀንጋሪያን ፎክሎሪስቶች ሲሆን እነዚህ ፎክሎሪስቶች በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ባህላዊ ዳንስና ባህላዊ ሙዚቃዎች እንደሠበሠቡ ገልጿል። ነገር ግን ቫዳሲ በኢትዮጵያ የሚገኙ የዳንስ አይነቶችን ምትና ሪትም በማነፃፀር ከፋፍሎ መግለፅና ክዋኔውን ማሣየት ነው። ይህን ሲያደርግ ከአማራ ክልል የጐጃምን፣ የጐንደርንና የምንጃርን ዳንስ በማንሣት መቼ፣ የትና እንዴት እንደሚከወኑ ካሣየ በኋላ ይህን ልዩነት ያመጣው የባህሉ መለያየት እንደሆነ ጠቁሟል። በእነዚህ አካባቢዎች በሚደነሱ ዳንሶች እነማን እንደሚሣተፉና የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሣሪያ ምን እንደሆነ ከእነአጠቃቀሙ አብራርቶታል። እንዲሁም የእያንዳንዱን ዳንስ እንቅስቃሴ ከሙዚቃ አላባውያን (ምት፣ ቢትና ሞቲቭ) አንፃር ገልጸውታል።

በሁለተኛ ደረጃ "Ethiopian Folk Dance II Tigre and Gurage" (1971) በሚል ርዕስ ባሣተመው ሥራ ውስጥ የትግሬን ዳንስ ሲገልፁ የትግሪዎች ዳንስ ከምንጃር ዳንስ ጋር እንዴት እንደሚመሣሠል ጠቁመዋል። እንዲሁም የትግሬና የጉራጌን ዳንስ ደግሞ እንደ አካባቢያቸው እና እንደመከወኛ አጋጣሚያቸው ልዩነት የተለያየ ስም እና እንቅስቃሴ እንዳላቸው አብራርተውታል።

እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ(1973) ደግሞ የወሎንና የኦሮሞን ማህበረሰብ የዳንስ አይነትና አደናነሳቸውን በሰፊው ገልፀውታል። ይህን ሲገልፁ የወሎ ዳንስ በህዝብ አመት በዓላት ወቅት ወንዶች በቡድን ሆነው የሚደንሱት የዳንስ አይነት "ሆታ" እየተባለ የሚጠራ ሲሆን ሴቶች ጭምር የሚሣተፉበት ዳንስ ደግሞ "የፍቅር ዳንስ" እየተባለ ይጠራል ሲሉ ጠቁመዋል።

የኦሮሞን ማህበረሰብ ዳንስ ሲገልፅ ደግሞ ሁለት አይነት ናቸው ይላል፡፡ እነሱም ደቼሣና ረገዳ የሚባሉ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው የራሣቸው የሆነ ከዋኝ እና የመከወኛ አጋጣሚ አላቸው፡፡ ለምሣሌ ደቼሣ በወንዶች ብቻ የሚከወን የዳንስ አይነት ሲሆን የሚከወነው በጥምቀት፣ በመስቀልና በአጠቃላይ የማህበረሰቡ በዓል ቀን ሲሆን ነው እንጂ በማንኛውም ሰዓት የሚከወን አይደለም፡፡ ረገዳ ደግሞ ወንዶችና ሴቶች በመስመር ተሠልፈው የሚከውኑት የዳንስ አይነት ሲሆን ከደቼሣ ቀጥሎ የሚመጣና በጣም ለአጭር ጊዜ የሚደነስ ዳንስ ነው በማለት አብራርተውታል፡፡

በአጠቃላይ ቴቮር የኢትዮጵያን ሀገረሰባዊ ዳንስ ሲያጠና መረጃውን የሰበሰበው በአብዛኛው ከተማሪዎች፣ ከኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና ከብሔራዊ ትያትር እንደሆነ ገልፀውታል፡፡ እነዚህ ሀገረሰባዊ የዳንስ አይነቶች የሚለያዩት እንደ አካባቢው ባህልና የአኗኗር ሥርዓት ነው ይላል፡፡ ቴቮር እነዚህን የኢትዮጵያ ሀገረሰባዊ ዳንሶች ሲያጠና ማህበረሰቡ ሀገረሰባዊ ዳንሱን በሚከውኑበት ወቅት የሚጠቀሙባቸውን የመከወኛ ቁሶች ለማህበረሰቡ ከሚሰጡት ተግባር አንፃር አልተመለከተም፡፡

ነፃነት ሙሉጌታ (1994) "የአማራ ባህላዊ ውዝዋዜዎች ጥንትና ዛሬ" በሚል ርዕስ ጥናት አጥንቷል፡፡ ይህ አጥኚ ዋና ትኩረቱ የአማራ ክልል ባህላዊ ውዝዋዜ አይነቶችን ልዩነት በማሣየት ላይ ነው፡፡ ይህን ሲያጠና የአማራ ክልልን አራት ባህላዊ የውዝዋዜ አይነቶች (የጐጃም እንቅጥቅጥ፣ የጐንደር እስክስታ፣ የወሎ ዋንጫ ልቅለቃ እና የምንጃርን ውዝዋዜ) በማንሣት ለማነፃፀር ሞክሯል፡፡ እነዚህ ውዝዋዜዎች እንደ መልከዓ ምድር አቀማመጣቸውና እንደ ባህሉ ባለቤት አለባበስና አጊያጌጥ የሚለያዩ መሆናቸውን ጠቁሟል፡፡

ነፃነት ይህን ጥናት ለማጥናት የተነሣው የአማራ ባህላዊ ውዝዋዜ የጥንቱንና የዛሬውን ያለውን ልዩነት ለማሣየት ነበር፡፡ ነገር ግን እሱ ትኩረት ያደረገው ከላይ እንደተገለፀው አራት የአማራ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን በመውሠድ ልዩነቱ ከባህሉ ባለቤት የመነጨ መሆኑን በማሣየት ላይ ነው፡፡ ይህ ጥናት በአጠቃላይ የርዕስና የአላማ አለመጣጣም በሠፊው ይታይበታል፡፡ ይህ ደግሞ ጥናቱን ክፍተት እንዲኖረው አድርጎታል፡፡

### 2.3.2. ባህላዊ ሙዚቃን ብቻ ያጠኑ

ጴጥሮስ መላኩ (1991) "በወለጋ ኦሮሞኛና በሸዋ ኦሮሞኛ ዘፈን መካከል ያለው የአዘፋፈን አንድነትና ልዩነት" በሚል ርዕስ ጥናት አጥንቷል፡፡ ይህ አጥኝ የወለጋና የሸዋ ኦሮሞ ባህል መገለጫ የሆነውን የአዘፋፈን ስልት አንድነትና ልዩነት በማሣየት ላይ ነው፡፡ በጥናቱም የሸዋና የወለጋ ማህበረሰብ ከሚኖሩበት የአኗኗር ዘየ የተነሣ የአዘፋፈን ልዩነት እንደሌላቸው ጠቁሟል፡፡ አንድነቱ የመነጨው ቋንቋቸው አንድ ስለሆነ ነው ይላል፡፡ የእነዚህ ሁለት የዘፈን ግጥሞች የኦሮሞ ማህበረሰብ እርስ በእርስ ባላቸው መዋደድና መፈቃቀር ላይ የተመሠረተ ነው ሲል ገልጾታል፡፡ እንዲሁም የሁለቱ ማህበረሰቦች ውዝዋዜ ረገዳና ደቼሣ እንደሚባሉ ጠቁሟል፡፡

ጴጥሮስ በጭፈራው ወቅት የባህሉ ባለቤቶች የሚለብሱትን ልብስና የሚጠቀሙበትን ቁስ ከእነክዋኔው በመግለፅ በኩል ጥሩ የሚባል ሥራ ሠርቷል፡፡ ነገር ግን መረጃውን እንዴትና ከየት እንደሠበሠበው አልገለጸውም፡፡

ማቴዎስ ከበደ (1994) "የሸዋ ኦሮሞ ጥቂት የባህል ሙዚቃና የሙዚቃ መሣሪያዎቻቸው" በሚል ርዕስ ጥናት አጥንቷል፡፡ ይህ አጥኝ የሸዋ ኦሮሞ የአዘፋፈን ስልት ከምትና ሪትም ጋር በማያያዝ ገልጾታል፡፡ ይህን ሲገልፅ የሸዋ ኦሮሞ ዘፈን አይነቶች ረገዳና ደቼሣ ሲሆኑ እነዚህ ዘፈኖች መቼና የት እንደሚካሄዱ በሠፊው አብራርቶታል፡፡ የዚህ አጥኝ ዋና ትኩረት የሙዚቃውን ሪትምና ቢት በማሣየት ላይ ስለሆነ ክዋኔውን ትኩረት ሰጥቶ አላተመለከተም፡፡

ሳሮን ጌትየ (1994) "'ጌይ ኡሱዕ' የአደሬ ባህላዊ ሙዚቃ" በሚል ርዕስ ጥናት አጥንታለች፡፡ ሳሮን ጥናቱን ስታጠና ትኩረት ያደረገችው የአደሬ ማህበረሰብ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ላይ ሲሆን የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሣሪያ ከምን እንደተሠራና ለምን አገልግሎት እንደሚውል ገልፃለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአደሬ ሙዚቃ የማህበረሰቡን ሃይማኖት ማሞገስ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ጠቁሟለች፡፡ ይህን ከመጠቆም ባለፈ ግን ለምን? እንዴት? እና መቼ? እንደሚከውኑ ትኩረት ሰጥታ አላየችውም፡፡

ትምክህት ተፈራ (2009) “Control, Influence and Violence through Music: the Role of Political Songs during the Ethiopian Revoltion (1974-1993)” በሚል ርዕስ ሙዚቃ ለባህላዊ ለውጥና ለፖለቲካዊ ንቅናቄ ያለው ሚና ምን እንደሆነ አብራርታለች፡፡

በ2005 “Music, making Music and Dancing: Ethnmusicological Observations in Meqelle/Tegray” በሚል ርዕስ ለሠባተኛው አለም አቀፍ ኮንፍረንስ የቀረበው ጥናት የትግሬ ሙዚቃ እንዴት የትግሬን ባህል እንደሚገልፅ፣ በክዋኔው ወቅት ከዋኞች የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሣሪያ ከምን እንደተሠራና ለምን አገልግሎት እንደሚውል አብራርቶታል፡፡

## 2.3.3. የማህበረሰቡን አኗኗር ከሙዚቃቸው ጋር አያይዘው ያጠኑ

ይርጋሸዋ ደብሬ (1994) “የአላባ ብሔረሰብ ባህላዊ አኗኗራቸውና ሙዚቃቸው” በሚል ርዕስ ጥናት አጥንቷል፡፡ ይህ አጥኝ ያተኮረው የአላባ ማህበረሰብ አኗኗራቸውና ሙዚቃቸው ምን ያህል ግንኙነት እንዳለው ነው፡፡ በዚህ ጥናት የአላባ ማህበረሰብ የአኗኗር ሥርዓታቸውን፣ የሚጠቀሙበትን የሙዚቃ መሣሪያና ሙዚቃዎቻቸው የሚከወኑበትን ወቅት በእርሻ፣ በሰርግ እና እንግዳ ሲቀበሉ በማለት ከፋፍሎ ገልፆታል፡፡

አሸናፊ ሙሉጌታ በ(1994) በጅጅጋ አካባቢ በሚኖሩ የሱማሌ ማህበረሰቦች ባህላዊ አኗኗርና ሙዚቃቸው ምን ግንኙነት እንዳለው ጥናት አካሄዷል፡፡ የዚህ አጥኝ ዋና ትኩረት የሱማሌን ማህበረሰብ ባህላዊ ሙዚቃቸው ምን ያህል እንደሚገልፃቸው ማሣየት ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ የሱማሌ ማህበረሰብ የመኖርያ ቤት አሰራር፣ የአለባበስ፣ የአመጋገብና የአኗኗር ስርዓታቸው በባህላዊ ሙዚቃቸው እንዴት እንደሚገለፅ አብራርቶታል፡፡ እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላት ሙዚቃ በአንዳንድ የበዓላት ቀን በዓሉን ለማክበርና በአዘቦት ቀን ለመዝናናት እንደሚዜም ጠቁሟል፡፡ የዚህን ባህላዊ ሙዚቃ ከዋኞችም ወንዶችና ሴቶች እንደሆኑ ገልጿል፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ጥናቶች አንድ ባህላዊ ሙዚቃ ከማህበረሰቡ አኗኗር ጋር ያለውን አንድነትና ማህበረሰቡን ምን ያህል እንደሚገልፁት በማሣየት ላይ ያተኮሩ ሥራዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህ አጥኝዎች የመከወኛ ቁሶችና አልባሳት ያላቸውን ትዕምርታዊ ውክልና መግለፅ ላይ ትኩረት አላደረጉም፡፡

## 2.3.4. በአጠቃላይ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን ያጠኑ

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሚል ርዕስ እስከ አሁን ያገኘሁት አንድ ጥናት ብቻ ነው፡፡ ይህም ገዛኸኝ አሰፋ (1999) "የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍል ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ከሚጠበቁ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት ያጠናው ነው፡፡ አጥኚው ይህን ጥናት ሲያጠና ዋና አላማው የከምባታን ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት መሰብሰብ፣ መመርመር እና ሰንዶ ለተተኪው ትውልድ እንዲተላለፍ ማቆየት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ያተኮረው የከምባታን ሀገረሰባዊ ዳንስ፣ ሀገረሰባዊ ዘፈንና ሀገረሰባዊ ድራማ ክዋኔ በማሣየት ላይ ነው፡፡

ገዛኸኝ መረጃውን የሠበሠበው በቦታው በመገኘት በምልከታና በቃለ መጠይቅ ነው፡፡ የጥናቱ ስልት አካሄድ ደግሞ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበብን እንደ ታሪክ ቅሪት በመቁጠር ሰብስቦ ገለፃና ትንታኔ መስጠት ነው፡፡ ይህን ገለፃና ትንታኔ ሲያደርግ ሀገረሠባዊ ትውን ጥበባቱ መቼ? በማንና እንዴት? እንደሚከወኑ በሠፊው ገልጿል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ብዙ ክፍተቶች ይታዩበታል፡፡ ለምሳሌ፡- ሀገረሠባዊ ትውን ጥበባት ሲከወኑ የባህሉ ባለቤቶች ባህላዊ ልብሶችን ለብሰውና በባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች ታጅበው በልዩ ልዩ ስርዓቶች ላይ የሚከውኗቸው የህዝብ ባህላዊ ሀብቶች ጠቁሞ ከማለፍ ውጭ በማህበረሠቡ ውስጥ ያለውን አንድምታ ትርጓሜ (ትዕምርታዊ ውክል) አልገለፅም፡፡ እንዲሁም ክዋኔውን ሲያሣይ ለምሣሌ፡- በዳንስ ጊዜ ክብ ሠርተው እንደሚደንሱ ከመግለፅ ባሻገር ለምን ክብ ሠርተው እንደሚደንሱ ማብራሪያ አልሠጠም፡፡ በተጨማሪ እነዚህ ትውን ጥበባት ለማህበረሰቡ የሚሠጡትን ተግባራት አልገለፀም፡፡ ነገር ግን ሁለታችንን የሚያመሣስለን ነገር በሙዚቃውም ሆነ በዳንሱ ውስጥ ባለው ምት ላይ አለማተኮራችን ነው፡፡ እኔ የማተኩረው ሀገረሠባዊ ትውን ጥበባቱ መቼ እንደሚከወኑ ክዋኔውን በማሣየት ላይ ነው፡፡ ይህን ስገልፅ ክዋኔውን፣ በክዋኔውን ወቅት

የሚጠቀሙበትን የመከወኛ ቁሶች ያላቸውን ተግባራት ትኩረት ሠጥቼ ስለምመለከት የእኔና የገዛኸኝ ጥናቶ በዚህ ይለያያሉ፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ ቅኝት በተደረገባቸው ጥናቶች ውስጥ ድርጊቱ መቼ፣ በማንና የት እንደሚካሄድ ከእነክዋኔው መግለፃቸው አጥኝዎቹን የሚያስመሰግናቸው ቢሆንም በጥናቱ ውስጥ ግን ጉልተው የሚታዩ ክፍተቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ክፍተት ሁሉም አጥኚዎች ክዋኔውን በማሣየት ላይ እንጂ ድርጊቱ ለምን እንደሚደረግ እና ከምን የመነጨ እንደሆነ ትኩረት አለማድረግ፡፡

ሌላው ክፍተት ደግሞ አንድ ማህበረሰብ አንድን ባህላዊ ሙዚቃ፣ ባህላዊ ዳንስና ባህላዊ ውዝዋዜ ሲያካሄድ የራሱ የሆነ የአለባበስና የአጊያጌጥ ሥርዓት አለው፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ግን የውዝዋዜውን ክዋኔ በማሣየት ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ስለዚህ አንድ አጥኝ ክዋኔን ሲያጠና እያንዳንዱ ድርጊት ለምን እንደሚደረግና የመከወኛ ቁሶች በአግባቡ ካልተገለፁ ጥናቱን ያልተሟላ ያደርጉታል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ይህ ጥናት ከላይ ከተዘረዘሩት ቀደምት ጥናቶች ጋር የሚመሣሳሰልባቸው ክዋኔው በማን፣ መቼና የት እንደሚከወን ማሳየት ነው፡፡ ተመሳሳይነት ይኑረው እንጂ በአንፃሩ ግን ጥናቱ ከቀደምት ጥናቶት ጋር ሰፊ ልዩነቶች አሉት፡፡ ማለትም ጥናቱ የቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ከሆኑት መካከል ሀገረሰባዊ ሙዚቃና ሀገረሰባዊ ዳንስ በሚከወኑበት ወቅት ከፋፍሎ ማየቱ ልዩ ያደርገዋል፡፡ እንዲሁም የሚጠቀሙበትን የመከወኛ ቁሶች ለምሣሌ:- አልባሳቱን፣ የሙዚቃ መሣሪያውን እና የመሳሰሉትን ነገሮች ጨምሮ ይገልፃል፡፡

# 3. ማህበረ-ባህላዊ ዳራ

## 3.1. ዞናዊ ገጽታ

የቤንች ማጂ ዞን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከሚገኙት 13 ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች አንዱ ሲሆን በኢትዮጵያ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ ከአዲስ አበባ 561 ኪሎ ሜትር እና ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ከሀዋሳ 836 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ በ2001 የተዘጋጀው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ፕሮፋይል እንደሚያመለክተው ዞኑ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ ከከፋ ዞን፣ በሰሜን ምዕራብ ከሸካ ዞን፣ በደቡብ ምስራቅ ከደቡብ ኦሞ ዞን፣ በደቡብ ምዕራብ ከጋምቤላ ክልል እና በደቡብ ከሱዳን ሪፐብሊክ ጋር ይዋሰናል፡፡

ዞኑ የተመሰረተው የደርግ ስርዓት ውድቀትን ተከትሎ ከ1983 ዓ.ም መግቢያ እስከ 1985 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በተፈጠረው አዲስ ክልላዊና ዞናዊ አደረጃጀቶች መሰረት ነው፡፡ መጀመሪያ በሁለት ዞኖች ተከፍለው የቤንችና የማጂ ዞን በመባል ለሁለት አመት ተደራጅተው ለየብቻ ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ ነገር ግን በሁለቱ ዞኖች ውስጥ የሚገኙት ማህበረሰቦች ያላቸውን የባህልና የታሪክ ትስስር በመመልከት እና ከግምት ውስጥ በማስገባት በ1987 ዓ.ም መጨረሻ ሁለቱን ዞን አንድ ዞን በማድረግ “ቤንች ማጂ ዞን” በሚል ስያሜ እንዲጠራ ተደርጓል፡፡ ሲሉ አቶ ገዛኸኝ አባተ (ሚዛን፣ 26 ቀን 2003 ዓ.ም) ገልፀውልኛል፡፡

ዞኑ በዚህ መልኩ ይመስረት እንጅ የ2002 ሰነድ እንደሚያመለክተው በስሩ ባልተማከለ የአስተዳደር ስርዓት መሰረት አስር ወረዳዎች፣ አንድ ከተማ መስተዳደር እና 241 የገጠርና የከተማ ቀበሌዎችን አቅፎ ይገኛል፡፡ በዞኑ ስር ቤንች፣ ዲዚ፣ መኢኒት፣ ሸኮ፣ ሱርማና ዝልማሙ (ባሌ) የተባሉ ስድስት ማህበረሰቦች ይኖሩበታል፡፡ በ1999 ዓ.ም የተካሄደውን የህዝብ ቤቶች ቆጠራ ውጤት መሰረት በማድረግ በተደረገው ትንበያ ደግሞ በአሁኑ ሰዓት በዞኑ ውስጥ የሚኖረው የህዝብ ብዛት በአጠቃላይ 718,062 ሲሆን ከፆታ አንፃር ሲታይ 355,870 (49.56%) ወንዶች እና 362,192 (50.44%) ሴቶች እንደሆኑ የዞኑ ህዝብ ቆጠራ ያስረዳል፡፡

## 3.2 መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ንብረት

የቤንች ማህበረሰብ ሰፍሮ የሚገኝበት የመሬት አቀማመጥ ሜዳማ፣ ተራራማና ሸለቋማ ሲሆን ከባህር ወለል በታች እስከ 1000 ሜትር እና ከባህር ወለል በላይ 500-3000 ሜትር ከፍታ የሚደርስ መልክዓ ምድራዊ ገፅታ አለው፡፡ የአየር ንብረቱ ደግሞ ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላማ ስለሆነ ለተለያዩ የግብርና ስራዎች ምቹ ነው፡፡ አመታዊ የዝናብ መጠኑ በአማካይ ከ400-2000 ሚ.ሜ ሲሆን አመታዊ የሙቀት መጠኑ ደግሞ በአማካይ ከ15-27 ይደርሳል፡፡ ከስነ-ምህዳር ስብጥር አንፃር ሲታይ 52% ቆላማ፣ 43% ወይና ደጋ እና 5% ደጋ የአየር ንብረት እንዳለው በ2002 የተዘጋጀው የዞኑ ሰነድ ያመለክታል፡፡

## 3.3 የቤንች ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር

ከላይ እንደተገለፀው የቤንች ማህበረሰብ በቤንች ማጅ ዞን ውስጥ ከሚገኙት ስድስት ማህበረሰቦች መካከል አንዱ ነው፡፡ የዚህ ማህበረሰብ ታሪካዊ አመጣጥ በግልፅ ባይታወቅም የተለያዩ አፈ-ታሪኮች ግን በተለያየ መንገድ ስለአመጣጡ ለማስረዳት ይሞክራሉ፡፡ እንዲሁም ኩንዲሳ (1988) እና የደቡብ ህዝቦች ፕሮፋይል (2001፡ 85) የተለያዩ አፈ-ታሪኮችን በመጥቀስ የማህበረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ በሰፊው አብራርተውታል፡፡ እነዚህ አፈ-ታሪኮች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የመጀመሪያው አፈ-ታሪክ ከነገደ ኩሽ ከመሀል ኢትዮጵያ እየፈለሰ ወደ ደቡብ ምዕራብ የመጣ ነው፡፡ ምክንያቱም የካም (የሴም) ነገዶች ከሰሜን እየፈለሱ ወደ መሀል አገር ሲመጡ መሀል አገር ያለው ማህበረሰብ ደግሞ ወደ ደቡብ እየፈለሰ ስለመጣ ነው ይላል፡፡

ሁለተኛው አፈ-ታሪክ ስለማህበረሰቡ አመጣጥ ሲያስረዳ ጥንት ከአሁኑ ሸዋ ቤንች አካባቢ "ቤንችቲያት" በተባለ መሪ አማካኝነት "ወርጎ" ከተባለ ስፍራ ከጋቸብ ወንዝ ዳርቻ ሰፍሮ የአሁኑን የቤንች አካባቢ መያዙን ይናገራል፡፡

ሌላው አፈ-ታሪክ ደግሞ ከሁለተኛው ብዙ ልዩነት የሌለው ሲሆን ስለማህበረሰቡ አመጣጥ የሚከተለውን ይላል፡፡ በቀድሞ ጊዜ "ቤንችቲያት" የተባለ ሀብታም ባለአባት

ነበር የሱም የዘር ሀረጎች በመራባት አሁን ያለውን ማህበረሰብ ፈጠሩ በማለት ይተርካል። ይህ አፈ-ታሪክ ስለአመጣጡ የገለፀው ሀሳብ ትክክል መሆኑን በመስክ ቆይታየ ያገኘኋቸው መረጃ ሰጪ አቶ ኩንዲሳ ፈርኪ ስለማህበረሰቡ ታሪካዊ አመጣጥ እንዲህ ሲሉ ተርከውልኛል።

> የቤንች ማህበረሰብ የመጣው "ቤንችቲያት" ከተባለ ንጉስ ነው። ምክንያቱም "ቤንችቲያት" መጀመሪያ ከመሀል አገር ተነስቶ ከጋቸብ ወንዝ አካባቢ ሰፈረ። ከዚያም የመሪነት ስልጣን ሲያገኝ የአሁኑ ሸዋ ቤንች አካባቢ ሰፈረ። ከዚያም ሲራባ የአሁኑን ቤንች መሰረተ በዚህም መሰረት የአሁኑ የቤንች ማህበረሰብ መጣ። (ቂጤ፣ ሚያዝያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም)

ማህበረሰቡ ቤንች የሚለውን ስያሜ የወረሰው "ቤንችቲያት" ከተባለው ጥንታዊ መሪ እንደሆነ ይነገራል። "ታት" የሚለው ቃል "ጌታ" ማለት ሲሆን ለማህበረሰቡ እና ለቋንቋው መጠሪያ በመሆን ያገለግላል። ይህን ሀሳብ ኩንዲሳ (1988) በሰፊው አብራርተውታል። የቤንች ማህበረሰቦች በዋናነት በዞኑ ውስጥ በሚገኙ ደቡብ ቤንች፣ ሺ ቤንች እና ሰሜን ቤንች ወረዳዎች ሰፍረው ይገኛሉ። በተወሰነ መልኩ ደግሞ ከዞኑ ጋር ኩታገጠም በሆኑት በካፋ ዞን በጨና እና ደቻ ወረዳዎች፣ በሸካ ዞን በየካ ወረዳዎች እንዲሁም በአዲስ አበባ "ጊምራ" ሰፈር ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ ይገኛሉ። ማህበረሰቡ በሰሜን ምስራቅ የካፋ፣ በደቡብ እና በምዕራብ የሸኮ፣ በምስራቅና በደቡብ የመኢኒት ማህበረሰቦች ጋር ይዋሰናል። በ2002 የተዘጋጀው ሰነድ እንደሚያመለክተው የማህበረሰቡ አሰፋፈር 88.34% በገጠር እና 11.66% በከተማ የሚኖሩ ሲሆኑ የህዝብ ጥግግቱ ሲታይ ደግሞ በአንድ ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት መሬት 37 ሰዎች እንደሚኖሩ ይገመታል።

## 3.4 የቤንች ማህበረሰብ ቋንቋ

የማህበረሰቡ ቋንቋ "ቤንቸኛ" ሲሆን ከምዕራብ ኦሞአዊ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ ይመደባል። ቋንቋው ከድዋሮኛ፣ ከሸኮኛ፣ ከዲዚኛ እና ከካፊኖኖ ጋር ይመሳሰላል። ይህን ቋንቋ ከማህበረሰቡ ተወላጆች በተጨማሪ አብረው የሚኖሩት የሌላ ማህበረሰብ ተወላጆች የሆኑት የሸኮ፣ የመኢኒት እና የካፋ ማህበረሰብ አባላት ይናገሩታል። በአሁኑ ወቅት ቋንቋው ከንግግር በአለፈ በአንዳንድ ቦታዎች የላቲን ፊደል ተዘጋጅቶለት በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የሙከራ ትምህርት እየተሰጠበት እና በፕሮቴስታንት ሀይማኖት

ተከታዮች ዘንድ የወንጌል ትምህርት እየተማሩበት ይገኛል፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ካማ አዲሱ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡

> ቤንቸኛ ቋንቋ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የላቲን ፊደል ተዘጋጅቶለት ተማሪዎች በየትምህርት ቤቱ ለሙከራ ያህል እየተማሩበት ነው፡፡ ነገር ግን የፕሮቴስታንት ሀይማኖት ተከታዮች ወንጌል እያስተማሩበት ይሁን እንጅ በጽሑፍ አገልግሎት ላይ ሙሉ በሙሉ ውሏል ለማለት አያስደፍርም፡፡ (አማን፣ ሚያዝያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም)

በመስክ ቆይታየ ወቅት አንዳንድ የሀይማኖት አባቶች ሲናገሩ እንደሰማሁት በ1990 ዓ.ም የመካነየሱስ ቤተክርስትያን የሳባ ፊደላትን በመጠቀም ቋንቋውን የጽሑፍ ቋንቋ ለማድረግ ባካሔደችው ጥናት መሰረት መፅሐፍ ቅዱስን ከአማርኛ ወደ ቤንቸኛ ቋንቋ ተተርጉሞ አገልግሎት እንዲሰጥ አድርጋለች፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ በርናባስ በኮምታት እንዲህ ሲሉ አረጋግጠውልኛል፡፡

> የእኛ ቤተ-ክርስትያን በዘጠናዎቹ ዓመተ ምህረት ውስጥ መፅሐፍ ቅዱስን ከአማረኛ ወደ ቤንቸኛ ቋንቋ ለመተርጎም ሞክራለች፡፡ ይህ ሙከራ የተደረገበት ዋና አላማ የማህበረሰቡን ተወላጆች በራሳቸው ቋንቋ የሀይማኖት ትምህርት ለማስተማርና ወንጌል ለመስፋፋት ነው፡፡ (ሚዛን፣ ሚያዝያ 27 ቀን 2003 ዓ.ም)

በአጠቃላይ የቤንችን ማህበረሰብ ቋንቋ ከንግግር ቋንቋ ወደ ጽሁፍ ለመቀየር ከላይ እንደተገለጸው የተለያዩ ሙከራዎች ቢደረጉም በአሁኑ ሰዓት ግን ለቋንቋው እንዲመች ተደርጎ የተቀረጸው የላቲን ፊደል ነው፡፡ በመስክ ቆይታየ ወቅት እንዳረጋገጥሁት የማህበረሰቡ አባላት ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ አማርኛ፣ ካፊኖኖ እና ሸኮኛ ቋንቋዎችን ይናገራሉ እንጅ በብዛት የሚግባቡት ግን በራሳቸው ቋንቋ እንደሆነ መረጃ ተርጓሜዬ ከድር ሸባ ነግረውኛል፡፡

## 3.5. ባህላዊ አስተዳደር

የቤንች ማህበረሰብ ከ18ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ የራሱ የሆነ የአስተዳደር ስርዓት የነበረው መሆኑን እና መሪው "ቤንችቲያት" በሚል የማዕረግ ሥም እንደሚጠራ የደቡብ ሕዝቦች ፕሮፋይል (2001) ይጠቁማል፡፡ ይህን መሪ የሚመርጡት የ"ቃም" ጎሳዎች ሲሆኑ የሚመረጠው ደግሞ ኮምት ከሚባል የባላባት ዝርያ ካላው የጎሳ አባል የተወለደ ነው፡፡ ምክንያቱም የቤንች ማህበረሰብ በውስጡ በአራት ዋና ዋና ጎሳዎች

የተከፋፈለ እና እያንዳንዱ ጎሳ የራሱ የሆነ ማህበራዊ ደረጃ ያለው በመሆኑ ነው። እነዚህ ጎሳዎች የተከፋፈሉት የሚተዳደሩበትን የኢኮኖሚ ምንጭ መሰረት በማድረግ ነው። ኮምት የባለአባት ዝርያ ያላቸው እና የገዥው መደቦች ናቸው። ቃም ደግሞ በውትድርና፣ በሳር አጨዳ፣ በከብት ጥበቃ፣ በእርሻ፣ ንብ በማነብና ውሀ በመቅዳት የገዥውን መደብ (የኮምት) ነገስታትን የሚያገለግሉ ናቸው። ማንጃ (ባንድ) እንደ ዝቅተኛ ጎሣ የሚቆጠሩና በባህሉ የስራ ክፍፍል መሰረት ወንዶች በአደን ሴቶች ደግሞ በሸክላ ስራ የተሰማሩ ናቸው። ማኖ (ፋቂ) የሚባሉት ደግሞ ቆዳን በመፋቅና በማልፋት የሚተዳደሩ ናቸው። በዚህ ምክንያት ቃም፣ ማንጃ እና ማኖ የሚባሉት ሶስቱ ጎሣዎች በማህበረሰቡ ዘንድ ለመሪነት አይመረጡም። ስልጣኑ የሚተላለፈው ከኮምት ጎሣ በዘር ሀረግ ለሚገናኝ እና ንፁህ ቤንች ሆኖ ከቲያቶች ሚስት ለተወለደ የበኩር ልጅ ነው። ነገር ግን ቲያቱ (መሪው) ልጅ ሳይወልድ ከሞተ ስልጣኑን ወንድሙ ሊወርሰው ይችላል ሲሉ አቶ ሻንቆ ጋኪናስ አረጋግጠውልኛል (አማን፣ ሚያዝያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም)።

ከላይ እንደተገለፀው ማህበረሰቡ የራሱ የሆነ ባህላዊ አስተዳደርና የዳኝነት ስርዓት ያለው ሲሆን የስልጣን እርከኑና የስራ ሀላፊነቱ የሚወሰነው ደግሞ በእየርከኑ ባሉ የጎሣ መሪዎችና የአገር ሽማግሌዎች አማካይነት ነው። በማህበረሰቡ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው መሪ ኮምት ነው። ይህ መሪ ማንኛውንም ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች በበላይነት ይመራል።

በቤንች ማህበረሰብ ዘንድ ከባህላዊ መሪዎች በተጨማሪ መንፈሳዊ መሪዎች የሚገኙ ሲሆኑ የራሳቸው የሆነ መዋቅር እና ሚና አላቸው። ለምሳሌ፡- በግድያ፣ በድምበር፣ በግጦሽ መሬት፣ በጠለፋ ጋብቻ እና በመሳሰሉት ነገሮች የአካባቢው ሰዎች ሲጣሉ ባለቃልቻዎች በማስታረቅና ችግሩን በመፍታት ያገለግላሉ ሲል የደቡብ ህዝቦች ፕሮፋይል (2001) ያትታል።

ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ በማህበረሰቡ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ የተለያዩ የግጭት አፈታት ስልቶች ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፡- ግድያ ከተፈፀመ በአገር ሽማግሌዎች የወንጀሉ አፈፃፀም ከተጣራ በኋላ በሁለት ደመኞች ድንበር ላይ በሬ ታርዶ በደሙ በመታጠብ ይታረቃሉ። ልጅ አገረድ ከገዳይ ወገን በካሳ ትሰጣለች። ነገር ግን ችግሩ በዚህ መልኩ ካልተፈታ ገዳዩን ሰው ከሞት፣ በስቅላት፣ ገደል በመወርወር፣ ሁለት እጆቹን የፊጥኝ

ከዛፍ ጋር በማሰር የሚች ወገኖች በጦር ወጋግተውና አሰቃይተው እንዲገሉት በማድረግ ይቀጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኩንዲሳ(1988) በማህበረሰቡ ዘንድ መዋሸት፣ መስረቅ እና ዝሙት መፈፀም በጥብቅ የተከለከለ እንደሆነ በጥናታቸው ውስጥ ገልፀውታል፡፡ ይህ ዓይነቱን ድርጊቱን የፈፀመ ሰው ለባለቃልቻው ጊደር ወይም ወይፈን እንዲሰጥ ይደረጋል፤ ለተወሰኑ ወራት ለባለቃልቻው እንዲያርስ ይታዘዛል፤ ከአስር እስከ ሰላሳ ጅራፍ ይገረፋል፤ በእግረ ሙቅ ይታሰራል፡

## 3.6. ኢኮኖሚያዊ ተግባራት

የቤንች ማህበረሰቦች የሚገኙበት ዞን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት እና በውጭ ምንዛሪ ከፍተኛውን ቦታ ሸፍኖ የሚገኘውን ቡና በስፋት በማምረት የሚታወቅ ስለሆነ የማህበረሰቡ አባላት በአብዛኛው የሚተዳደሩት በቡና ምርት ነው፡፡ የማህበረሰቡ አባላት ከቡና ምርት በተጨማሪ የገቢ ምንጭ የሚያገኙት በወርቅ ማዕድን ቁፋሮ፣ ከብት በማርባት እና እርሻ በማረስ ነው፡፡

የዞን የቆዳ ስፋት 1,932,659 ሄክታር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 13.38% የታረሰ (የለማ)፣ 6.99% ሊለማ የሚችል፣ 4.1% ለግጦሽ የዋለ፣ 45.81% በደንና ቁጥቋጦ የተሸፈነ፣ 20.4% ሊለማ የማይችል እና 9.32% ለሌሎች አገልግሎቶች የዋሉ እንደሆኑ በዞኑ የተገኙት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

## 3.7. መሰረተ ልማት

ዞኑ እንደ ሌሎች ዞኖች የራሱ የሆነ የመሰረተ ልማት አውታሮች አሉት፡፡ እነሱም፡- ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ተቋማቶች (የሰውና የእንስሳት)፣ መንገድ የመሳሰሉትን ናቸው፡፡

የዞኑ የ2002 ዓ.ም ያልታተመ ሰነድ እንደሚያመለክተው የማህበራዊ አገለግሎት መስጫ ሽፋን ሲታይ በዞኑ ውስጥ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ 409 የትምህርት ተቋማት ይገኛሉ፡፡ የመንግስት ትምህርት ተቋማት በአጠቃላይ 401 ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል 51 አማራጭ መሰረተ ትምህርት የሚሰጥባቸው፣ 337 የመጀመሪያ ደረጃ (ከ1-8)፣ 10 የሁለተኛ ደረጃ (ከ9-12) ትምህርት ቤቶች፣ አንድ የቴክኒክና ሙያ ተቋም ፣

አንድ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና አንድ ዩንቨርስቲ ናቸው። መንግስታዊ ያልሆኑ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በአጠቃላይ ስምንት ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ሁለት ቅድመ መደበኛ (አፀደ-ህፃናት)፣ አምስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ1-8) እና አንድ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ ናቸው።

የ2001 ዓ.ም የጤና መምሪያ ሰነድ እንደሚያመለክተው በዞኑ ውስጥ ያለው የጤና ተቋም ሽፋን ሲታይ የመንግስት ጤና ተቋማት አንድ ሆስፒታል፣ 12 ጤና ጣቢያዎች፣ 22 ታዳጊ ጤና ጣቢያዎች እና 161 ጤና ኬላዎች የሚገኙ ሲሆኑ የግል ጤና ተቋማት ደግሞ አራት ታዳጊ ጤና ጣቢያዎች፣ ስድስት መካከለኛ ክሊኒኮች፣ 76 አነስተኛ ክሊኒኮች፣ ስምንት የመድሀኒት መደብሮች እና 12 የገጠር መድሀኒት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን በአጠቃላይ በዞኑ ውስጥ 302 ጤና ተቋማት ያሉ መሆኑን መረጃው ይጠቁማል።

የመንገድ ትራንስፖርት ቢሮ መሰረተ ልማት እንደሚያመለክተው ደግሞ የተለያየ ደረጃ ያላቸው የገጠር መንገዶች በዞኑ ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህ መንገዶች በሁለት ተከፍለው 2050 ኪ..ሜ የበጋ እና 733 ኪ..ሜ የክረምት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ።

### 3.8. ማህበረ-ባህላዊ እሴቶች

የቤንች ማህበረሰቦች እንደሌሎች ማህበረሰቦች የበርካታ ባህላዊ እሴቶች ባለቤት ናቸው። ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል። የጋብቻ ስርዓት፣ የለቅሶ እና የቀብር ስርዓት፣ እምነት እና የመሳሰሉት ባህላዊ እሴቶች ናቸው።

### 3.8.1. የጋብቻ ስርዓት

በማህበረሰቡ ጋብቻ የሚፈፀመው የጎሳን ክፍፍልን መሰረት በማድረግ እንደሆነ ማንያለው (1999) እና ኩንዲሳ (1988) ገልጸውታል። በዚህ መሰረት የማህበረሰቡ ጋብቻ የሚፈጸመው "ኮምት" የተሰኘው የጎሳ አባል ከ"ቃም" ጎሳ አባል ጋር ሲሆን "ማኖ" የተሰኘው የጎሳ አባል ደግሞ ከ"መንጃ" ጎሳ አባል ጋር ነው። እንጂ አራቱ ጎሳዎች እርስበርስ አይጋቡም። ምክንያቱም "ኮምት" እና "ቃም" የከፍተኛ ባላአባት የዘር ሀረግ ስለሆኑ በማህበረሰቡ ዘንድ የዝቅተኛ ጎሣ የዘር ሀረግ ናቸው ከሚባሉት ከ"ማኖ" እና ከ"መንጃ" ጋር ከተጋቡ ዘራችን ይረክሳል ብለው ያስባሉ።

የማህበረሰቡ የጋብቻ እድሜ የሚፈቀደው ሴቷ አስራ አምስት ዓመት ወንዱ ደግሞ ሀያ አመት ሲሞላቸው ነው። የማህበረሰቡ የጋብቻ ስርዓትቶ በአራት ዓይነት የተከፋፈሉ ናቸው። እነሱም ጌርስታ (በቤተሰብ ስምምነት የሚፈፀም ጋብቻ)፣ ጋሪስካ (በማባበል የሚፈፀም ጋብቻ)፣ ጉቻ (በጠለፋ የሚፈፀም ጋብቻ) እና ባረዝ (በውርስ የሚፈፀም ጋብቻ) ናቸው።

**ሀ. በቤተሰብ ስምምነት የሚፈፀም ጋብቻ (ጌርስታ)፡-** ይህ ጋብቻ የሚፈፀመው በቤተሰብ ስምምነት ሲሆን አግቢው ለሚያገባት ልጅ አገረድ ቤተሰቦች የከብት ጥሎሽ ይጥላል። የጥሎሹ መጠን ግን እንደየጎሳው አባል እና የስልጣን ደረጃ ይለያያል። ማለትም የታጨችዋ ልጅ የ"ኮምት" ጎሳ አባል ከሆነች ከአስራ አምስት እስከ ሀያ ከብት ይጣላል። የታጨችዋ ልጅ የዝቅተኛ ጎሣ አባል ልጅ ከሆነች ደግሞ ከሶስት እስከ ሰባት ከብት ይጣላል። ጥሎሹ ከተጣለ ከተወሰነ ቀን በኋላ በሁለቱም ቤተሰብ ዘንድ ሰርግ ይሰረጋል። በሰርጉ ሥነ-ስርዓት ከልጁ ቤተሰብ ቦርዴ ተጠምቆ፣ የበቆሎ ዳቦ ተደፍቶ፣ ወተትና ቅቤ ተዘጋጅቶ ወደ ልጅቷ ቤት ይወሰዳል። ሙሽሮች እና አጃቢዎች ይህን በልተውና ጠጥተው ከጠገቡ በኋላ በተረፈው ዳቦ ድብድብ ይጀምራሉ። ከዚያ ድብድቡ ሲያበቃ ተሰብስበው የተለያዩ ጭፈራዎችን ይጨፍራሉ። ይህ ሀሳብ አቶ ሻንቆ ጋኪናስ እና ሌሎች መረጃ ሰጭዎቼ አረጋግጠውልኛል።

**ለ. የጠለፋ ጋብቻ (ጉቻ)፡-** ይህ የጋብቻ ዓይነት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚፈፀመው በሁለት መልኩ ነው። አንደኛ አንድ ወንድ ሊያገባት የፈለጋትን ልጅ አገረድ አባብሎ ሊያገባት እንደሚፈልግ ይገልፅላታል። ነገር ግን ልጅቷ እሱን ማግባት እንደማትፈልግ ገልፃ እምቢ ካለችው በዚህ ጊዜ እሱ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ልጅቷን ማገዶ ለቀማ፣ ገበያ፣ ለቅሶ ወይም ሰርግ ቤት ስትሄድ ጠብቆ ይጠልፋታል። ሌላኛው ጠለፋ ደግሞ የሚደረገው አንድ ወንድ አንዷን ልጅ አገረድ ስታልፍ አይቶ ከወደዳት ልጅቷ ምንም ሳታወቅ ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ይጠልፋታል። ልጅቷን ከጓደኞቹ ጋር ሁኖ በሚጠልፍበት ጊዜ በመጀመሪያ ባሏ የሚሆነው አስቀድሞ እንደመጣች እጇን ይይዛታል። ከዚያ ጓደኞቹ ተሸክመው እምቢ ካለች እየደበደቡ ይዘዋት ይሄዳሉ። የሚያገባት ሰው አስቀድሞ እጇን የሚይዝበትን ምክንያት ታደሰ ከተማራሽ እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል። "በባህላችን በጠለፋ ጊዜ የሚያገባት ወንድ

አስቀድሞ እጇን የሚይዛት ልጅቷ አግቢዋ ማን እንደሆነ እንድትለይ በማለት ነው።" (ደብረወርቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም)

ከላይ በተገለፀው መልኩ ልጅቷን ከጠለፏት በኋላ የአግቢው ቤተሰብ ካሉበት ራቅ ብሎ አንድ ቤት ይነጠፍና ወደፊት የሚያገባት ልጅ ክብረ ንፅህናዋን እንዲወስደው ይደረጋል። ይህ የሚደረግበት ምክንያት በማህበረሰቡ ዘንድ አንድ ሴት ክብረ ንፅህና ከሌላት ጋለሞታ ስለምትሆን ለትዳር ጓደኛዋ አትመችም በማለት ሌላ ባል ስታገባ የሚከፈላት ጥሎሽ አነስተኛ ስለሚሆን ነው። በዚህ ምክንያት ልጅቷ እዚያው ለምዳ እንድትቀር በማሰብ ነው። ነገር ግን በማህበረሰቡ ዘንድ የጠለፋ ጋብቻው የፀና የሚሆነው ሽማግሌ በጉዳዩ ገብቶበት አስፈላጊው ካሳ ለእሷና ለቤተሰቦቿ ተከፍሎ ጥሎሽ ከተጣለና ሰርግ ከተሰረገ በኋላ ነው።

**ሐ. የማባበል ጋብቻ (ጋርስካ)፡-** ይህ ጋብቻ የሚካሄደው በሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት ሲሆን እነዚህ ወጣት ተጋቢዎች የሚመራረጡት በሁለት መልኩ ነው። አንደኛ በዘፈን ጊዜ፣ በሰርግ እና በለቅሶ ጭፈራ ወቅት ወጣቱ ልጅቷን ስትጨፍር አይቶ ከወደዳት አብራው ዳንስ (ዶር) እንድትደንስ በብትር በመንካት ይጠይቃታል። እሷም ወዳው ከሆነ እሺ ብላ አብራው ትደንሳለች በዚህ ጊዜ ትውውቁ እየሰፋ ይሄድልና ሁለቱ የአንገት ጨሌያቸውን ይቀያየራሉ። ከዚያ ከተወሰነ ቀን በኋላ አንድ ቦታ ይቀጣጠሩና መጥቶ ይወስዳታል። ሁለተኛው የማባበል ጋብቻ ደግሞ የሚፈፀመው ወጣቱ ልጅቷን በራሱ ወይም በራሷ ዘመዶች አባብሎ በማግባት ነው። ነገር ግን ይህ ጋብቻ የፀና የሚሆነው ልክ እንደ ጠለፋ ጋብቻ ለቤተሰቦቿ አስፈላጊውን ካሳ ተከፍሎና ጥሎሽ ተጥሎ ሰርግ ከተሰረገ በኋላ ነው።

**መ. የውርስ ጋብቻ (ባርዝ)፡-** ይህ የጋብቻ ዓይነት በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመደ ሲሆን ጋብቻው የሚፈፀመው አንድ ወንድ ሚስት አግብቶና ልጅ ወልዶ ከሞተ ሚስቱን ሌሎች ወንድሞቹ በመውረስ ነው። የሟቹን ሚስት በውርስ የሚያገባት ታላቅ ወንድም ካለው እሱ ታላቅ ከሌለው ታናሽ ወንድሙ ነው። ሟቹ ወንድም ከሌለው ግን የቅርብ ዘመድ ተፈልጎ ያገባታል። ይህ የውርስ ጋብቻ በማህበረሰቡ የሚደረግበት ምክንያት የሟቹን ሀብት ንብረቱን እና ልጆች ሌላ ባዳ እንዳይወርሳቸው በማለት ነው።

እነዚህ ከላይ የተገለፁት የጋብቻ ዓይነቶች በማህበረሰቡ ዘንድ የተለመዱ ሲሆኑ እያንዳንዳቸው ግን የየራሳቸው የሆነ ደንብ አላቸው። ለምሳሌ፡- በቤተሰብ የሚፈፀም ጋብቻ (ጌርስታ)፣ በጠለፋ የሚፈፀም ጋብቻ (ጉቻ) እና በማባበል የሚፈፀም ጋብቻ (ጋርስካ) ጊዜ በቤተሰብ አማካኝነት ከፍተኛ የሆነ ሰርግ ተሰርጎ እየተበላ እና እየተጠጣ ይጨፈራል። በውርስ ጋብቻ ጊዜ ግን በቤተሰብ አማካኝነት ምንም አይነት ዝግጅት አይደረግም። ምክንያቱም ጋብቻው የሚፈፀመው ትዳር ለመያዝ ታስቦ ሳይሆን ከላይ እንደተገለፀው የሟቹን ሀብት እና ንብረት ባዳ እንዳይወርሰው ስለተፈለገ ብቻ ነው።

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ የጋብቻ ስርዓት የሚፈፅመው ከላይ ከተገለፁት የጋብቻ ዓይነቶች በአንዱ ነው። ነገር ግን በማህበረሰቡ ዘንድ አንድ ወንድ ማስተዳደር ከቻለ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ይፈቀድለታል። በተለይ ባለቃልቻ ከሆነ እስከ አርባ ሚስቶች ማግባት የሚችል ሲሆን የመጀመሪዋ (አንጋፋዋ) ሚስት "ጌን" በመባል ትጠራለች። የደቡብ ህዝቦች ፕሮፋይል (2001፡86)

### 3.8.2. የለቅሶ ስርዓት

የቤንች ማህበረሰብ እንደ ማንኛውም ማህበረሰብ የራሱ የሆነ የለቅሶና የቀብር ሥርዓት አለው። ነገር ግን በማህበረሰቡ ዘንድ የለቅሶና የቀብር ሥርዓቶች የሚፈጸሙት ሟቾች በማህበረሰቡ ዘንድ ካላቸው ማህበራዊ ደረጃ አንፃር ሲሆን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ። እነሱም፦

1ኛ .ባለቃልቻ የለቅሶና የቀብር ሥርዓት

2ኛ. ሀብትና ንብረት ያላቸው ሰዎች የለቅሶና የቀብር ስርዓት

3ኛ. የዕድሜ ባለፀጎች የለቅሶና የቀብር ሥርዓት

4ኛ. የሕፃናት የለቅሶና የቀብር ሥርዓት በማለት ከፋፍለው ያከብሩታል።

አራቱ የለቅሶና የቀብር ሥርዓት አይነቶች ኩንዲሳ(1988) እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል። የማህበረሰቡ የለቅሶና የቀብር ሥርዓት የሚፈፀመው ሟቹ በማህበረሰቡ ዘንድ ካለው ቦታ አንፃር ስለሆነ ለሁሉም ሰው ተመሳሳይ የሆነ ዝግጅት አይደረግለትም። ምክንያቱም

አንድ ባለቃልቻና ሀብት ንብረት ያለው ሰው ሲሞት ከበሮ እየተመታ ከሶስት እስከ 30 ቀን ሊጨፈር ይችላል፡፡ ህፃናት ሲሞቱ ደግሞ ምንም ዓይነት የጭፈራ ስርዓት አይደረግም፡፡

በማህበረሰቡ አንድ ባለቃልቻ ሲሞት ወዲያውኑ እንደሞተ የቅርብ አገልጋይ የሆኑት ሰዎች ተሰብስበው ከቤት እየወጡ እና እየገቡ ይዘፍናሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉበትን ምክንያት አቶ ሻንቆ ጋኪናስ እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡ "በዚህ ሰዓት የሚዘፈነው የእምነቱ ተከታዮች ባለቃልቻው መሞቱን አስቀድመው እንዲያውቁና ተተኪ ሊሆን የሚችለውን ከባለቃልቻው ልጆች እንዲመርጡ ነው፡፡" (አማን፣ ሚያዝያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም) በተራ ቁጥር 3 እና 4 በተዘረዘሩት የለቅሶ ስርዓቶች ጊዜ የሚዘፈንበትን ምክንያት ደግሞ አቶ ገዛኸኝ አባተ እንዲህ በማለት ገልጸውልኛል፡፡ "እነዚህ ሰዎች ሲሞቱ የሚዘፈነው ሀዘንተኞችን ለማፅናናት እና ለሞተው ሰው ጊዜያችንን በደስታ አሳልፈናል የሚለውን ለመግለፅ ነው፡፡" (ሚዛን፣ ሚያዝያ 26 ቀን 2003 ዓ.ም) በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ ሀዘኑና ደስታውን የሚገልፀው የተለያዩ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን በመከወን ነው፡፡ እነዚህ ትውን ጥበባት ከላይ በተዘረዘሩት ማህበረ-ባህላዊ እሴቶች ይከወናሉ፡፡

## 3.9 ባህላዊ እምነት

የቤንች ማህበረሰብ ቀደም ካሉት ዘመናት ጀምሮ እስካለንበት ዘመን ድረስ የተለያዩ እምነቶች ያሉት ሲሆን የማህበረሰቡ አባላት ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በአብዛኛው የሚያምነው በሙት ነፍስ (በሚያንጌ) ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ደግሞ አብዛኛው የማህበረሰብ ክፍል በቃልቻ ያምናል፡፡ ይህ መንፈሳዊ ህይወቱ አንድም ከራሱ የመነጨ ወይም በልዩ ልዩ የታሪክ፣ የባህልና የማህበራዊ ኑሮ ግንኙነት የተነሳ ከተለያዩ ማህበረሰቦች የተወረሰ ነው ሲል ማንያለው (1999) የተለያዩ አጥኚዎችን (Cerulli (1986)፣ Tippetit (1970)) በመጥቀስ ገልፆታል፡፡ እንዲሁም ኩንዲሳ (1988 ዓ.ም) እና ግርማይ (1993 ዓ.ም) ይህንን ሀሳብ በጥናታቸው ውስጥ በሰፊው አብራርተውታል፡፡

### 3.9.1 የሚያንጌ እምነት

የቤንች ማህበረሰብ ባህላዊ እምነቶች ከሆኑት አንዱ ሚያንጌ ነው። ሚያንጌ ማለት የሙት ነፍስ ማለት ነው። ይህም የሚሆነው አባታቸው ሲሞት ነፍሱ በልጁ ላይ ሲያድር ማለት ነው። እነዚህ የሙት ነፍስ ያደረባቸው ሰዎች ቦክትያት፣ ዣዥቲያት፣ ሜርቲያት፣ ቶምቲያት፣ ሼኤቲያት. . .ወዘተ በመባል ይጠራሉ። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ቲያቶች ማህበረሰቡን የመግዛት፣ የማስተዳደር እና የማስገበር ስልጣን አላቸው።

የእምነቱ ተከታዮች ሚያንጌን የሁሉ ነገር ፈጣሪ አድርገው ይቆጥሩታል። ይህን ሀሳብ በተመለከተ ማንያለው (1999) መረጃ ሰጪውን ቄስ ተገኝ ማሪኩን ጠቅሶ እንዲህ ሲል ያብራራዋል።

> እግዚአብሔር በዚህ አለም ላይ የሚገኙትን ነገሮች በሙሉ ፈጠረ። እነዚህ የየሮ (ፈጣሪ) ፍጥረቶች በምድር፣ በሰማይ፣ በውሃ፣ ወዘተ ብቻ የሚኖሩ ሳይሆኑ የሰው ልጅ በዐይኑ ሊመለከታቸው የማይችለውን መንፈሶች (spirits) ጭምር ነው። እነዚህን ሁሉ የፈጠረው የሮ ፍጡራኖቹን በመንፈስ እንዲመራና እንዲገስጽ የበላይነቱን ለሚያንጌ ሰጠው። ስለዚህ በሰውና በየሮ መካከል ያለው አገናኝ ሚያንጌ ነው። (ማንያለው፣ 1999፡ 25)

ይህ የሚያንጌ እምነት በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ቦታ ያለው ነው። ይህም እንደእምነቱ ተከታዮች አስተሳሰብ ሰው መግደል፣ ማዳን፣ ዝናብ ማዝነብ፣ ፀሃይን ማስወጣትና ማስገባት ይችላል። ኩንዲሳ (1988) የሚያንጌ እምነት መንፈሳዊ አሰራር እንዴትነትንና የአምልኮት ስርዓቱን በሰፊው አብራርተውታል።

በአጠቃላይ የሚያንጌ እምነት በማህበረሰቡ ዘንድ የፍቅር፣ የሠላም፣ የብልፅግና አምላክ እንደ ነበር ማንያለው (1999፡26) እና ኩንዲሳ (1988፡28) የገለፁት ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ግን በማህበረሰቡ ዘንድ የፕሮቴስታንት ሀይማኖትና የቃልቻ እንጂ የሚያንጌ እምነት እየተዳከመ መሆኑን በመስክ ቆይታዬ ተርጓሚዬ ከድር ሽባ አረጋግጠውልኛል። ይህን ያልኩበት ምክንያት ባለሚያንጌው የት ነው ብዬ ስጠይቅ ተደጋጋሚ የማገኛቸው የማህበረሰቡ ተወላጆች አሁን የለም አይገኝም የሚል ምላሽ ስለሰጡኝና አቶ ኩንዲሳ ፈርኪ ሀሳቡን ስላረጋገጡልኝ ነው። (ቂጤ፣ ሚያዝያ 25ቀን *2003 ዓ.ም*)

### 3.9.2 የቃልቻ እምነት

ቃልቻ ማለት መንፈስ ያደረበት ሠው ማለት ነው። የቃልቻ እምነት የቤንች ማህበረሰብ የቆየ እምነት ሳይሆን ከከፋ ማህበረሰቦች የተወረሰ መሆኑን ማንያለው አባተ (1999) እና ኩንዲሳ (1988) የገለፁት ቢሆንም በመስክ ቆይታዬ አቶ ሻንቆ ጋኪናስንና አቶ ኩንዲሳ ፈርኪን በጋራ አግኝቼ ባነጋገርሁበት ወቅት ይህን ሀሳብ አረጋግጠውልኛል። ነገር ግን የባላባት (የቃልቻ) እምነት መሰረቱ የመንፈስ ባለቤትነት ነው። መንፈሱ በማንኛውም ሰው ላይ ሊያድር ይችላል የሚል ሀሳብ ማንያለው (1999፡27) አስቀምጧል። መረጃ ሰጭዎች (ኮጁ መንግስቴ እና ሻንቆ ጋኪናስ) የነገሩኝ ግን መንፈሱ በማንኛውም ሠው ላይ አያርፍም። የሚያርፈው በፊት የቃልቻ መንፈስ ያለበት ሠው አባት ወይም አያት ካለው እነርሱ ላይ ነው። እነሱም ብዙ ጊዜ ባለአባቶች ናቸው ሲሉ አብራርተውልኛል። እንዲሁም ባለቃልቻው አቶ ኮጁ መንግስቴ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል። "እኔ ባለቃልቻ ነኝ የባለአባት ልጅ ነኝ በአባቴ ቃልቻ ነበረበት ከዚያ እኔ ላይ አረፈ። እኔ ላይ ያረፈበት ምክንያት የአባቴ የበኩር ልጅ ስለሆንኩ ነው" ሲሉ አረጋግጠውልኛል። (ኮብ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም)

የቃልቻ እምነት ክብረ በዓላት የሚከበሩት በአመት ሶስት ጊዜ በመስከረም፣ በህዳር እና በሚያዝያ ወራት ነው። በእነዚህ ወራት በዓሉ የሚከብረው በባለቃልቻው ቤት ሲሆን የእምነቱ ተከታዮች ለባለቃልቻው የተለያዩ ስጦታዎችን ይዘው ይመጣሉ። ስጦታውን የሚያቀርቡት ስለት ተስለው ስለታቸው ከደረሰ ነው። ስልቱን የሚቀርቡት በገንዘብ ወይም በጭፈራ መልክ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በክብረ በዓላቱ ወቅት ማንኛውም የእምነቱ ተከታይ በዝግጅቱ ላይ ተገኝቶ የግድ መጨፈር አለበት። ጭፈራውን የሚያስጀምሩት ወይዘሶች (የባለቃልቻው የቅርብ አገልጋዮች[2]) ናቸው። የእምነቱ ተከታዮች በክብረ በዓሉ ወቅት ተገኝተው ለባለቃልቻው ይህን ካላደረጉ ግን እንታመማለን፣ እንሞታለን ወይም እንደኸያለን ብለው ያስባሉ።

---

[2] "ወይዘስ" ማለት በማህበረሰቡ ቋንቋ "የባለቃልቻው የቅርብ አገልጋይ" ማለት ስለሆነ እኔም በማህበረሰቡ አገላለጽ መሰረት በጥናቱ ውስጥ "ወይዘስ" የሚለውን ቃል ተጠቅሜያለሁ።

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች አማካኝነት በሚፈጠሩ አጋጣሚዎች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባቱን ሲከውኑ ይስተዋላሉ፡፡ ይህም በምዕራፍ አራት እንደሚከወኑበት አጋጣሚ ተከፋፍሎ ቀርቧል፡፡

## 4. የቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት አውዳዊ ክዋኔ ገለፃ

የቤንች ማህበረሰቦች እንደ ሌሎች ማህበረሰቦች የራሳቸው የሆኑ ማህበረ-ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ እሴቶች አሏቸው፡፡ የማህበረሰቡ አባላት በእነዚህ ማህበረ-ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ እሴቶች አማካይነት በሚፈጠሩ አጋጣሚዎች በመጠቀም የራሳቸውን ታሪክና ባህል ይገልፁባቸዋል፡፡ ከእነዚህ የመግለጫ መንገዶች መካከል የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት አይነት የሆኑት ሀገረሰባዊ ሙዚቃና ሀገረሰባዊ ዳንስ ናቸው። እነዚህ ትውን ጥበባት በማህበረሰቡ ዘንድ የሚከወኑት የራሳቸው በሆኑ የመከወኛ አጋጣሚዎችና የክዋኔ ስርዓቶች ነው። በእነዚህ አጋጣሚዎች በሚደረጉ የክዋኔ ስርዓቶች እና በወቅቱ በሚጠቀሙባቸው የመከወኛ ቁሶች አማካይነት ማህበረሰቡ የራሱን ስሜት እና ፍላጎት ይገልፅባቸዋል፡፡

ቫንሲና (1985፣ 39) እንደገለፁት አንድ የትውን ጥበብ የሚከወነው በዘፈቀደ ሳይሆን የራሱ የሆነ የመከወኛ አጋጣሚውን በመጠቀም ነው፡፡ የቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትም ቲወሪው እንደሚለው የሚከውኑበት የራሳቸው የሆኑ የተለያዩ ማህበረ-ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ሰበቦች አሏቸው፡፡ እነዚህ ማህበረ-ባህላዊ ሰበቦች ወርደት (ሰርግ)፣ የብ (ለቅሶ) እና ቃይጥ (ስራ) ናቸው፡፡ ከሃይማኖታዊ ሰበቦች መካከል ደግሞ አንዱ እምነት ሲሆን በማህበረሰቡ አጠራር ቃልቻ በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ ጥናት የማህበረሰቡ አባላት በነዚህ አጋጣሚዎች የሚከውኗቸውን የትውን ጥበባት ዓይነቶችና በትውን ጥበባቱ ወቅት የሚጠቀሙባቸውን ቁሶች ትኩረት ሰጥቶ ይመረምራል፡፡ ትውን ጥበባቱ የሚከወኑበት አጋጣሚዎች ማህበረ-ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ አውዶች ተብለው በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች እና በንዑስ ርዕስ ተከፋፍለው እንደሚከተለው ተገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ዓይነት የሆኑት ሀገረሰባዊ ዳንስና ሀገረሰባዊ ሙዚቃ የሚከወኑበትን አጋጣሚ መሰረት በማድረግ በንዑስ ርዕሶች ተከፋፍለው ቀርበዋል፡፡

## 4.1 የቤንች ሀገረሰባዊ ሙዚቃ (ዱብ[3])

ከቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት መካከል አንዱ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ ሲሆን በማህበረሰቡ አጠራር ዱብ በመባል ይታወቃል፡፡ ዱብ የሚከወነው ከማህበረሰቡ መሀል ያውቃሉ[4] ተብለው በተመረጡ ሰዎች አማካይነት በባህላዊ የዱብ መሳሪያዎች በመታጀብ ነው። የሚከወነውም በዘፈቀደ ሳይሆን በተለያዩ አጋጣሚዎች ለተለያዩ አላማዎች ነው።

Largey (1990፤96) እንደሚገፁት አንድ ሙዚቃ በማህበረሰቡ ዘንድ በአንድ አጋጣሚ በሚከወንበት ጊዜ የማህበረሰቡን ስሜት፣ ፍላጎት፣ ደስታ እና ሀዘን ይገልፃል፡፡ እንደ ምሁሩ ሀሳብ የቤንች ዱቦች በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚከወኑበት ሰዓት የማህበረሰቡን ደስታ፣ ሀዘንና ስሜት በመግለፅ በኩል ከፍተኛ የሆነ ተግባር አላቸው። እነዚህ ዱቦች የሚከወኑት የማህበረሰቡ አባላት በሆኑና በልምድ ሙያውን ባገኙት ሰዎች ነው፡፡ አንዳንድ ከዋኞች ከሙያቸው በተጓዳኝ የሚሰሩ (non-specialists) እና ባለሙያ (specialists) ተብለው የሚመደቡ ናቸው (Finnegan, 1970፡171-215) ብለው ገልፀውታል፡፡ እንደ እሳቸው ሀሳብ ሁሉ የቤንች ዱቦች የሚከወኑት በባለሙያዎች ሳይሆን ከስራቸው በተጨማሪ ጎን ለጎን በሚሰሩ ሰዎች ነው፡፡

በቤንች ማህበረሰብ ዱቦች የሚከውኑት በማህበረ-ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ አጋጣሚዎች ወቅት ነው፡፡ በእነዚህ ወቅቶች የሚከወኑት ዱቦች የተለያየ መልዕክት እና ጭብጥ አላቸው። ይህ የመነጨው ከሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች የተነሳ ነው፡፡ እነዚህ ዱቦች የሚከወኑበትን አጋጣሚ መሰረት በማድረግ ማህበረ-ባህላዊ

---

[3] "ሙዚቃ" ማለት በማህበረሰቡ አጠራር "ዱብ" ማለት ስለሆነ እኔም ለአጠቃቀም እንዲመቸኝ በማሰብ "ዱብ" የሚለውን ቃል ተጠቅሚያለሁ፡፡

[4] "ያውቃሉ" የተባሉት በሙዚቃው ዘርፍ የሰለጠኑ ሳይሆኑ በተለምዶ በማህበረሰቡ ተሰጦ አላቸው ተብለው የተመረጡ ሰዎች ናቸው፡፡

(የወርደት[5]፣ የየብና[6] የቃይጥ[7]) እና ሃይማኖታዊ (የቃልቻ) በማለት በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለው ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 4.1.1 ማህበረ- ባህላዊ አውድ

የአንድ ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ሲጠኑ በማህበረ- ባህላዊ አውድ መከፋፈል አለባቸው፡፡ ነገር ግን እነዚህን ማህበረ-ባህላዊ አውዶች አንዱን ከአንዱ ነጥሎ ማየት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ማህበራዊ አውዱ የትውን ጥበባቱን ባለቤቶች የያዘ ሲሆን ባህላዊ አውዱ ደግሞ የማህበረሰቡን እምነትና አመለካከት የያዘ ነው፡፡ ስለዚህ ማህበረሰቡ ሲነሳ ባህሉ ስለሚነሳ ሁለቱም ተያያዥነት አላቸው ብለው (ቦርላንድ፣1990፡ 93) ገልፀውታል፡፡ ልክ እንደ ምሁሩ አገላለፅ ሁሉ የቤንች ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እንደ ማንኛውም ማህበረሰብ የሚከወኑበት የራሳቸው የሆኑ ማህበረ-ባህላዊ አጋጣሚዎች አሏቸው፡፡ በእነዚህ አጋጣሚዎች የማህበረሰቡ አባላት በሚከውኗቸው ትውን ጥበባት አማካይነት የራሳቸውን እምነት፣ አመለካከትና ፍላጎት ይገልፁባቸዋል፡፡ እነዚህ ትውን ጥበባት የሚከወኑባቸው ማህበረ-ባህላዊ አውዶች ወርደት፣ የብ እና ቃይጥ በመባል በማህበረሰቡ አገላለጽ ተመድበዋል፡፡

#### 4.1.1.1 የወርደት ዱብ (የሰርግ ሙዚቃ)

የቤንች ማህበረሰቦች አራት ዓይነት የጋብቻ ሥርዓቶች ያሏቸው መሆኑን ቀደም ብሎ በጥናቱ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ላይ ተገልጿል፡፡ ከነዚህ መካከል ግን የወርደት ሥርዓት የሚከወነው በሶስቱ የጋብቻ ዓይነቶች ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የማህበረሰቡ አባላት ዱቦችን ከሚከውኑባቸው መንገዶች አንዱ በሶስቱ የጋብቻ ዓይነቶች በሚከወኑ የወርደት ክዋኔዎች ነው፡፡ በእነዚህ የወርደት ስርዓቶች ጊዜያት የተለያየ ዜማ ያላቸው ዱቦች በባህላዊ የዱብ መሳሪያዎች እና በተለያዩ ቁሶች በመታጀብ ይከወናሉ፡፡ እነዚህን

---

[5] "ወርደት" ማለት በማህበረሰቡ ቋንቋ "ሰርግ" ማለት ስለሆነ ከአሁን በኋላ ለአገላለፅ ይመቸኝ ዘንድ "ወርደት" የሚለውን ቃል ተጠቅሜያለሁ፡፡

[6] "የብ" ማለት በማህበረሰቡ አጠራር "ለቅሶ" ማለት ስለሆነ ከአሁን በኋላ ለአገላለፅ ይመቸኝ ዘንድ "የብ" የሚለውን ቃል ተጠቅሜያለሁ፡፡

[7] "ቃይጥ" ማለት በማህበረሰቡ አጠራር "ስራ" ማለት ስለሆነ በዚህ የጥናት ወረቀትም "ቃይጥ" የሚለውን ቃል ተጠቅሜያለሁ፡፡

የወርደት ዱቦች የሚያዜሟቸው የማህበረሰቡ አባል የሆኑና በማህበረሰቡ ዘንድ ችሎታ አላቸው ተብለው የሚታወቁ ሰዎች ናቸው። የወርደት ዱቦች እንደሚከወኑበት ጊዜ እና ቦታ የተለያዩ ተግባራት ይኑራቸው እንጅ የሚያስተላልፉት መልዕክት ግን በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው።

የወርደት ዱቦች በሚከወኑበት ወቅት የራሳቸው የሆነ አላማና የአቀራረብ ስልት እንዲሁም የራሳቸው የሆነ ከዋኝና ታዳሚ አላቸው። እነዚህ ዱቦች የሚከወኑበትን አላማ እና ከዋኝ መሰረት በማድረግ በአምስት ክፍሎች ተከፍለው ከዚህ በታች ቀርበዋል።

**ሀ. ሱቱይ፡-** ስቱይ ማለት በወርደት ጊዜ ከሚዜሙ ዱቦች መካከል አንዱ ነው። ይህ ዱብ የሚከወነው ወርደቱ በተጀመረ በመጀመሪያው ቀን ሲሆን የሚዜመውም በሁለቱም ሙሽሮች ቤት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ እንደሆነ ተመልክቻለሁ። ይህ ዱብ በዚህ ሰዓት የሚዜምበት ምክንያት ወርደቱን ረስተው ሳይመጡ የቀሩ ሰዎችን ወርደት እንዳለ ለማስታወስ እና እንዲመጡ ለማድረግ ነው። ይህን ሀሳብ በተመለከተ ባደረግሁላቸው ቃለመጠይቅ መሰረት አዳሙ ሀንቲያብ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል።

> በባህላችን ይህ ዘፈን (ዱብ) በዚህ ስዓት የሚዘፈነው በሁለቱም ቤት የተለያየ መልዕክት ለማስተላለፍ ነው። በሙሽራው ቤተሰቦች ቤት የሚዘፈነው ወደ አማቱ ቤት ሊሄድ ስለሆነ እንሸኘው፤ በሰላም አምላኩ እንዲመልሰው ለማለት ነው። በሙሽሪት ቤት ደግሞ በዚህ ስዓት የሚዘፈነው ወርደቱን ረስተው ያልመጡና የተኙ ሰዎች ካሉ ለማስታወስ እና እንዲመጡ ለማድረግ ነው። (ጊሊት ቀበሌ፣ ግንቦት 6 ቀን 2003ዓ.ም)።

ይህ ዱብ ከወርደት በተጨማሪ በየብ ወቅት ማታ ከሞተው ሰው ቤት የሚሰበሰቡት ሰዎች የሚያዜሙት ሲሆን በማህበረሰቡ ዘንድ በተደጋጋሚ ሲዜም ሰምቻለሁ። (ስለ የብ ዱቦች ወደፊት በሰፊው ተብራርቷል።) ዱቡ በተደጋጋሚ የሚያዜምበትን ምክንያት ወጣት ሰለሞን ፈጠነ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል። "ይህ ዱብ በባህላችን ዘንድ በጣም ተወዳጅ ነው። ምክንያቱም ዜማው በጣም ማራኪ ስለሆነ የየብ ጊዜ ሲዘፈን የሞተውን ሰው መንፈስ ደስ ይለዋል።[8] በወርደት ጊዜ ሲዘፈን ደግሞ የተኛው ሰው ሳይቀር ተነስቶ

---

[8] ደስ ይለዋል የተባለው የሞተው ሰው ሳይሆን የሙት መንፈሱ ነው። ይህም ማለት በሌሊት በሞተው ሰው ቤት ከተዘፈነ የሙት መንፈሱ አይከፋም ብለው ስለሚያምኑ ነው።

ይዘፍናል።" (አዲስ ዓለም፣ ግንቦት 5 ቀን 2003ዓ.ም)። ዱቡን የሚያዜሙት በሁለቱ ሙሽሮች ቤት የተሰበሰቡት ወንዶች እና ሴቶች በህብረት በመሆን ነው። ዱቡ በሚዜምበት ጊዜ በጭብጨባና ቶሪ (ቃጭል[9]) ከሴቶች እግር ላይ በሚታሰር የዱብ መሳሪያ እንደሚታጀብ ተመልክቻለሁ።

**ለ. ቦተር፡-** ቦተር ማለት በዱብ ወቅት በሙሽሪት ቤት ከሚዜሙት ዱቦች መካከል አንዱ ነው። በመስክ ቆይታዬ እንደሰማሁት ይህ ዱብ የሚዜመው በሙሽሪት ቤተሰቦች ቤት ብቻ ነው። ዱቡም የሚዜመው ከሌሊቱ አራት ሰዓት ሲሆን የሙሽራው አጃቢዎች እና ሙሽራው ከሙሽሪት ቤት ሲደርሱ ነው። የሚያዜሙትም የሙሽሪት ሴት ዘመዶች በቶሪ የዱብ መሳሪያ በመታጀብ ነው። ቶሪውን የሚያስሩት የሙሽሪት ዘመዶች ሲሆኑ "ጪጪ" የሚል ድምፅ እያሰሙ ሙዚቃውን ያጅቡበታል። በዚህ ዱብ የሙሽሪትን ጎሳ፣ የዘር ሀረግ፣ ቤተሰቦቿንና ሙያዋ ይሞገስበታል። ምክንያቱም ሙሽራው ገና እየመጣ ስለሆነ የሚያገባትን ሴት የጎሳ እና የቤተሰብ ሁኔታ ለእሱ እና ለአጃቢዎቹ ለማስተዋወቅ ነው። ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ በላይ አዲሱ እንዲህ ሲሉ አጠናክረውልኛል። "ይህ ዱብ የሚዘፈነው ሙሽራውን አጅበው ለመጡት ሰዎችና ለሙሽራው ነው። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ሙሽሪት የዚህ ጎሳ ዘር ናት የሚለውን ለመግለፅ እና የቤተሰቦቿን ማንነት ለማሳወቅ ነው።" (ሚያህ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም)።

**ሐ. ጎይሴ (ሾተስ)፡-** ይህ ዱብ ከቦተር ዱብ በአከዋወኑም ሆነ በዜማው ብዙም ልዩነት አይታይበትም። ነገር ግን ዱቡ ሙሉ በሙሉ አንድ እንዳይሆን የሚያደርገው ሙሽራውን አጅበው በመጡት ሰዎች መዜሙና በሴቶች ጭብጨባና ወንዶች በሚይዙት ጦር (ማይት[10]) መታጀቡ ነው።

---

[9] "ቃጭል" ማለት በማህበረሰቡ አጠራር "ቶሪ" ማለት ስለሆነ በዚህ የጥናት ወረቀትም "ቶሪ" የሚለውን ቃል ተጠቅሜያለሁ።

[10] "ጦር" ማለት በማህበረሰቡ አጠራር "ማይት" ማለት ስለሆነ በዚህ የጥናት ወረቀት ውስጥ "ማይት" የሚለውን ቃል ተጠቅሜያሉ።

**መ. በዲ፡-** በዲ ማለት አንዱ የወርደት ዱብ ነው። ይህ ዱብ የሚከወነው ከጎይሴ ቀጥሎ ሲሆን የሚከውኑት ሙሽራውን አጅበው የመጡት ሰዎች እና የሙሽሪት ዘመዶች በህብረት በመሆን እየተቀባበሉ እንደሆነ አስተውያለሁ። በዚህ ጊዜ የሚያዜሙት ዱብ በጎይሴ ጊዜ እንደሚያዜሙት ሁሉ የሙሽሪትን ዘመዶች የሚያሞግሱ እና ሙሽሪት እንድትጫወት የሚገፋፉ ናቸው። ሙሽራውን አጅበው የመጡት ሰዎች እና የሙሽሪት ዘመዶች በህብረት በመሆን አብረው የሚዘፍኑበት ምክንያት በጋብቻ አንድ መሆናቸውንና ጋብቻው መጽናቱን ለመግለጽ ነው። ይህን ሀሳብ በተመለከተ ሀብታሙ ኮምትኪት እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል። "እነዚህ ሰዎች አብረው እየተቀባበሉ የሚዘፍኑት ከአሁን በኋላ አንድ ነን፣ ተጋብተናል የሚለውን ሀሳብ ለመግለጽ ነው።" (ሚዛን፣ ግንቦት 6 ቀን 2003 ዓ.ም)

**ሠ. ኪርኪም፡-** ይህ ዱብ ዓይነት የሚከውነው በሁለቱ ሙሽሮች ቤተሰቦች ቤት ከሌሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ነው። በሁለቱ ቤት የሚከወነው በተመሳሳይ ሰዓት ቢሆንም ዱብን የሚያዜሙት ሰዎች እና የሚዜምበት አላማ ግን የተለያየ ነው። በሙሽሪት ቤት የሚያዜሙት ሙሽራውን አጅበው የመጡት ሰዎች ናቸው። የሚያዜሙበት ምክንያት ደግሞ ሙሽሪትን አዘጋጁና ስጡን ስንጫወት አድረናል ስለዚህ በቃን ልንሄድ ነው የሚለውን ለመግለፅ ነው። በሙሽራው ቤት የሚያዜሙት ደግሞ የሙሽራው ቤተሰቦች ሲሆኑ የሚያዜሙበት ምክንያት ሙሽሪትን ይዞ እየመጣ ስለሆነ ተሰብስበው ለመቀበል ሌሎች ሰዎች እንዲዘጋጁ ለማድረግ ነው። ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ አበሽ ቱዩ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል።

> ኪርኪም የሚባለው ዱብ ከሌሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ላይ በሙሽሪት ወላጆች ቤት ከቀረበ የሙሽሪት ቤተሰቦች ሙሽሪትን አዘጋጅተው እንዲሰጧቸው ለመጠየቅ ነው። በሙሽራው ወላጆች ቤት የተዘፈነ ደግሞ ሙሽራው ሊመጣ ስለሆነ ተነሱ እንቀበለው ለማለት ነው። (ሚያህ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም)

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ የወርደት ዱቦች እንደሚከወኑበት መቼት እና እንደ ከዋኞች ማንነት ይለያዩ እንጂ በአቀራረባቸው እና በመልዕክታቸው በአብዛኛው ተመሳሳይ ናቸው። ሁሉም የወርደት ዱቦች የሚከወኑት ከዋኙ ሲከውን ሌሎች ደግሞ ተሳታፊ ተመልካች በመሆን እየተቀባበሉ ነው። እንዲሁም የዱቡ ከዋኞች ክዋኔውን የሚያገኙት ከአባቢያቸው ማህበረሰብ በልምድ እንደሆነ በመስክ ቆይታዬ ለማረጋገጥ

ችያለሁ። እነዚህ ከዋኞች በዱቡ የሚያስተላልፉት መልዕክት በአብዛኛው ሙሽሪትንና የሙሽሪትን ቤተሰቦች የሚያሞግስ ነው። ለአብነት ያህል ከዚህ በታች ያለውን ግጥም ማየት ይቻላል።

## ግጥሙ በመገኛ ቋንቋ

| አውራጅ (አቀንቃኝ) | ተቀባይ |
|---|---|
| Fababa balus babe | wow-wow |
| Baynu bab | wow-wow |
| Ha wore wogashno | wow-wow |
| Ha wose woxsa shino | wow-wow |
| Seto shna befo | wow-wow |
| Sherashido nibab dube | wow-wow |
| Bay gashe | wow-wow |
| Bakha shido | wow-wow |
| No nale nola befo | wow-wow |
| Wo nase nam befane | wow-wow |
| Wo kaso | wow-wow |
| Wornya kalo | wow-wow |
| Setenta bego? | wow-wow |
| Wo dape wor nato? | wow-wow |
| Wo angaso has nkaso? | wow-wow |

**የግጥሙ ትርጉም በአማርኛ**

| አውራጅ (አቀንቃኝ) | ተቀባይ |
|---|---|
| አባታችን ባለ ሚሊኒየሙ | ዎው-ዎው |
| ባኑ የምትባል ላም አለችው | ዎው-ዎው |
| ሙሽራይቱ አትቀመጪ | ዎው-ዎው |
| ከዘመድ ጋር ተጫወቺ | ዎው-ዎው |
| ይህችን ላም እንድትሰጪ | ዎው-ዎው |
| ወጣቱ አንጎራጉር እንጂ | ዎው-ዎው |
| አትፍራ የአባታችን ዘፈን ነው | ዎው-ዎው |
| የእናታችን ባህል ነው | ዎው-ዎው |
| ጨዋታ ነው ተጫወቱ | ዎው-ዎው |
| አንተ ሰው ሙሽሪትን አይተህ ተጫወት | ዎው-ዎው |
| የሙሽራ ዘመድ አይደለህም ወይ? | ዎው-ዎው |
| ልትጫወት የመጣህ? | ዎው-ዎው |
| ለምን ዝም ትላለህ? | ዎው-ዎው |

ተርጓሚ፦ሀብታሙ ኮምትኪት

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ዱቦች አንድን ወርደት ከማድመቂያነት በተጨማሪ ለማህበረሰቡ የስሜት መግለጫና መግባቢያ በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የማህበረሰቡን አመለካከት፣ መልካም ምኞት እና መስተጋብር በመግለጽ በኩል ከፍተኛ የሆነ ድርሻ አላቸው፡፡

## 4.1.1.2 የየብ ዱብ (የለቅሶ ሙዚቃ)

ቀደም ብሎ በጥናቱ ማህበረ-ባህላዊ ዳራው ላይ እንደተገለፀው የቤንች ማህበረሰብ በየብ ሥርዓቱ ላይ ከሚጠቀምባቸው ትውን ጥበባት መካከል አንዱ ባህላዊ ጭፈራ ነው፡፡ በዚህ ጭፈራ ወቅት ሀገረሰባዊ ዳንሶች[11] (ዶሮች) እና ዱብ እጅ እና ጓንት ሆነው

---

[11] "ዳንስ" ማለት በማህበረሰቡ ቋንቋ "ዶር" ማለት ስለሆነ እኔም ለአገላለፅ እንዲመች በማሰብ "ዶር" የሚለውን ቃል ተጠቅሜያለሁ፡፡

ይከወናሉ። በማህበረሰቡ ዘንድ ዶሮች እና ዱቦች በየብ ወቅት የሚከወኑበት ዋናው ምክንያት የሚቹን መንፈስ ለማስደሰት እና ሀዘንተኞችን ለማፅናናት ታስቦ ነው።

የቤንች ማህበረሰብ ዱብ በየብ ወቅት የሚከወነው ለማንኛውም ሰው ሳይሆን ባለቃልቻ እና ሀብት ንብረት ያላቸው ሰዎች ሲሞቱ እንደሆነ አስተውያለሁ። ለእነዚህ ሰዎች ብቻ ዱቡ የሚከወንበት ምክንያት ዱቡን የሚያዜሙት ሰዎች የግድ የሚበሉትና የሚጠጡት ነገር የሚዘጋጅላቸው የሞተው ሰው ድርሻ ከሌሎች ቤተሰቦች ተከፍሎ ነው[12]። እነዚህ በየብ ወቅት የሚዜሙት ዱቦች ከሚከወኑበት መቼት እና ከከዋኞች አንጻር በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለው ከዚህ በታች ቀርበዋል።

1 **ጎዝ፦** በየብ ወቅት ከሚዜሙት ዱቦች መካከል አንዱ ነው። በመስክ ቆይታዬ እንዳስተዋልሁት ዱቡን የሚያዜሙት የእድሜ ባለጸጎች በህብረት አንድ ላይ በመሆን ነው። ዱቡን የእድሜ ባለፀጎች አንድ ላይ በመሆን ያዜሙት እንጂ የሚያስጀምረው ግን የቤተሰቡ የበኩር ልጅ ወይም አባወራ ነው። እሱ የሚስጀምርበትን ምክንያት አቶ በላይ አዲሱ እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል። "በባህላችን የበኩር ልጅ እያለ ዱቡን እሱ ካላስጀመረው የሙት ነፍስ በቀላሉ መንግስተ ሰማይ አትገባም ተብሎ ይታመናል።" (ሚያህ፣ ሚያዝያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም)።

ጎዝ ዱብ በሚያዜምበት ወቅት በቲያርብ (ከበሮ[13])፣ በቶሪ፣ በማይትና በጦር (ጃስ[14]) ይታጀባል። በዚህ ጊዜ የሚጠቀሙባቸው ቲያርቦች ሶስት ዓይነት ሲሆኑ የሚመቷቸው ደግሞ ለየብ ከመጡት ሰዎች መካከል የመምታት ችሎታ ያላቸው ሰዎች ናቸው። ቶሪውን ደግሞ ሀዘንተኛ የሆኑት ሴቶች በእግራቸው ላይ በማሰር እየተንቀሳቀሱ የዱቡ ምት እንዲጠብቅ ያደርጉታል። ቶሪ በእግራቸው ያሰሩት ሀዘንተኛ ሴቶች ዜማውን ማለት ባይችሉም ከወንዶች መሀል በመሆን አብረው

---

12 የሞተው ሰው ሀብት እና ንብረት ተከፍሎ እየተበላ እና እየተጠጣ የሚጨፈረውም ሟቹ ሀብትና ንብረት እያለው የእሱ ድርሻ ከሌሎች ቤተሰቦቹ ተከፍሎ ካልተጨፈረለት የሙት መንፈስ ይቆጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው።

13 "ከበሮ" ማለት በማህበረሰቡ ቋንቋ "ቲያርብ" ማለት ስለሆነ በዚህ ጥናት ውስጥ ለአገላለጽ ይመቸኝ ዘንድ የማህበረሰቡን ቋንቋ ተጠቅሜያለሁ።

14 "ጋሻ" ማለት በማህበረሰቡ አጠራር "ጃስ" ማለት ስለሆነ እኔም ለአገላለጽ ይመቸኝ ዘንድ በጥናት ወረቀቱ "ጃስ" የሚለውን ቃል ተጠቅሜያለሁ።

| ግጥሙ በመገኛ ቋንቋው | ትርጉም በአማርኛ |
|---|---|
| Hasis sis boya (4x) | ሀሲስ ሲስ ቦያ (4x) |
| Kaska kasasa boya | ተጫውተህ/ሽአጫወትኸን/ሽን ቦያ |
| Qayxsa qaysasaboya | ሰርተህ/ሽ አሰራኸን/ሽን ቦያ |
| Yeka yesasa boya | አልቅሰህ/ሽ አስለቀስኸን/ሽን ቦያ |
| Dyasa dyasasa boya | ወልደህ/ሽ አሳድገህል/ሻል ቦያ |

ተርጓሚ፡- አዳሙ ሀንትያብ

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ የየብ ዱብ በህብረት የሚዜም ሲሆን የሚዜምበት ዋና አላማ የሞተውን ሰው ጥሩ ስነ-ምግባር፣ ማንነት እና ታሪክ ለመግለጽ፣ ሀዘንተኞችን ለማጽናናት፣ የሞተውን ሰው መንፈስ ለማስደሰት እና በምድር ሆነው የመሰከሩለት ነገር በቀላሉ መንግስተ ሰማያት ያስገባል ብለው ስለሚያስቡ ያንን መልካም ምኞት ለመግለጽ ነው፡፡

### 4.1.1.3 የቃይጥ ዱብ (የስራ ሙዚቃ)

በቤንች ማህበረሰብ ዘንድ የቃይጥ ዱቦች የሚዜሙት በአብዛኛው የማህበረሰቡ አባላት በህብረት (በደቦ) በመሆን የግብርና ስራ በሚሰሩበት ወቅት ነው፡፡ በዚህ የቃይጥ ደቦ የሚሳተፉት ባለቃልቻ ያልሆኑና በማህበረሰቡ ዘንድ መካከለኛ ገቢ አላቸው የሚባሉት ሰዎች ናቸው፡፡ በቃይጥ ወቅት የሚዜሙትን ዱቦች የሚያዜሟቸው ሁሉም በቃይጡ ላይ የተገኙት የማህበረሰቡ አባላት ናቸው፡፡ በቃይጥ ወቅት የሚዜመው ዱብ 'woye' (ወዬ) የሚል ስያሜ አለው፡፡ ይህን ስያሜ ያገኘው ከዋኞች በህብረት እየተቀባበሉ ሲያዜሙ ከሚያሰሙት "ወይዮ" የሚል ድምፅ እንደሆነ አዳሙ ሀንትያብ እና ሰለሞን ፈጠነ አረጋግጠውልኛል፡፡

በቃይጥ ጊዜ ዱቡን የሚያዜሙት እንደቃይጥ ቦታው የመሬት አቀማመጥ (ከላይ ያሉት በአንድ ህብረት ከታች ያሉት በአንድ ህብረት) በመከፋፈል አውራጅ (ከዋኝ) እና ተቀባይ (ተሳታፊ ታዳሚ) ሆነው ነው፡፡ ይህ ዱብ ሲዜም በፊርግን የዱብ መሳሪያ ይታጀባል፡፡ በደቦ ቃይጥ ወቅት ዱብ የሚዜምበት ዋናው አላማ ጠንክረው ስራውን ለመስራት ነው፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ ሰለሞን ፈጠነ እንዲህ ሲሉ አብራርተውልኛል፡፡ "በባህላችን በቃይጥ ጊዜ ዱብ የሚዜመው የደከመውን በሞራል

| ግጥሙ በመገኛ ቋንቋው | ትርጉም በአማርኛ |
| --- | --- |
| Hasis sis boya (4x) | ሀሲስ ሲስ ቦያ (4x) |
| Kaska kasasa boya | ተጫውተህ/ሽአጫወትኸን/ሽን ቦያ |
| Qayxsa qaysasaboya | ስርተህ/ሽ አሰራኸን/ሽን ቦያ |
| Yeka yesasa boya | አልቅሰህ/ሽ አስለቀስኸን/ሽን ቦያ |
| Dyasa dyasasa boya | ወልደህ/ሽ አሳድገህል/ሻል ቦያ |

ተርጓሚ፡- አዳሙ ሀንትያብ

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ የየብ ዱብ በህብረት የሚዜም ሲሆን የሚዜምበት ዋና አላማ የሞተውን ሰው ጥሩ ስነ-ምግባር፣ ማንነት እና ታሪክ ለመግለጽ፣ ሀዘንተኞችን ለማጽናናት፣ የሞተውን ሰው መንፈስ ለማስደሰት እና በምድር ሆነው የመሰከሩለት ነገር በቀላሉ መንግስተ ሰማያት ያስገባል ብለው ስለሚያስቡ ያንን መልካም ምኞት ለመግለጽ ነው፡፡

### 4.1.1.3 የቃይጥ ዱብ (የስራ ሙዚቃ)

በቤንች ማህበረሰብ ዘንድ የቃይጥ ዱቦች የሚዜሙት በአብዛኛው የማህበረሰቡ አባላት በህብረት (በደቦ) በመሆን የግብርና ስራ በሚሰሩበት ወቅት ነው፡፡ በዚህ የቃይጥ ደቦ የሚሳተፉት ባለቃልቻ ያልሆኑና በማህበረሰቡ ዘንድ መካከለኛ ገቢ አላቸው የሚባሉት ሰዎች ናቸው፡፡ በቃይጥ ወቅት የሚዜሙትን ዱቦች የሚያዜሟቸው ሁሉም በቃይጡ ላይ የተገኙት የማህበረሰቡ አባላት ናቸው፡፡ በቃይጥ ወቅት የሚዜመው ዱብ ‘woye’ (ወዬ) የሚል ስያሜ አለው፡፡ ይህን ስያሜ ያገኘው ከዋኞች በህብረት እየተቀባበሉ ሲያዜሙ ከሚያሰሙት “ወይዮ” የሚል ድምፅ እንደሆነ አዳሙ ሀንትያብ እና ሰለሞን ፈጠነ አረጋግጠውልኛል፡፡

በቃይጥ ጊዜ ዱቡን የሚያዜሙት እንደቃይጥ ቦታው የመሬት አቀማመጥ (ከላይ ያሉት በአንድ ህብረት ከታች ያሉት በአንድ ህብረት) በመከፋፈል አውራጅ (ከዋኝ) እና ተቀባይ (ተሳታፊ ታዳሚ) ሆነው ነው፡፡ ይህ ዱብ ሲዜም በፊርግን የዱብ መሳሪያ ይታጀባል፡፡ በደቦ ቃይጥ ወቅት ዱብ የሚዜምበት ዋናው አላማ ጠንክረው ስራውን ለመስራት ነው፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ ሰለሞን ፈጠነ እንዲህ ሲሉ አብራርተውልኛል፡፡ “በባህላችን በቃይጥ ጊዜ ዱብ የሚዜመው የደከመውን በሞራል

ለማገዝ ሲሆን ብርቱውን ደግሞ ለማሞካሸትና ስራውን ለማቀላጠፍ ነው፡፡" (አዲስ አለም ቀበሌ፣ ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡

በዚህ ዱብ ጠንካራ የሆነው ሰራተኛ ብርታት፣ የመስራት ችሎታው፣ ታታሪነቱ እና ሰውየው የሚይዘው ገጀራ ስለታማነት ይሞገስበታል፡፡ እንዲሁም ቃይጡ የሚሰራለት ሰው በሬና ማረሻ መቆፈሪያው እና ዘር አዘራር ይደነቅበታል፡፡ የሚሰራው ስራ የትጋ ወደ ኋላ እንደቀረ ይጠቁሙበታል፡፡ ለአብነት ያህል ከዚህ በታች ያለውን ግጥም ማየት ይቻላል፡፡

**<u>ግጥሙ በመገኛ ቋንቋው</u>**

| <u>አውራጅ (አቀንቃኝ)</u> | <u>ተቀባይ</u> |
|---|---|
| Woyo yi! Ye yi yo | wow woyiyo wo shasha |
| Shashntete nayuo | wow woyiyo wo shasha |
| Zoyisa fayxso | wow woyiyo wo shasha |
| Qayxsa miuo | wow woyiyo wo shasha |
| Wotorsa tore | wow woyiyo wo shasha |
| Wo denta geshidow | wow woyiyo wo shasha |
| No qerm zayxs zolo | wow woyiyo wo shasha |

**<u>ትርጉሙ በአማርኛ</u>**

| <u>አውራጅ (አቀንቃኝ)</u> | <u>ተቀባይ</u> |
|---|---|
| ወይዬ ዪ!ይ ዪ ዮ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| የሻንቲቲት ልጆች | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| ጠንካራ ነህ ስራ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| በለስለታም ገጀራ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| የንጉስ ልጅ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| ታችኛው ነው የቀረህ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| ላይኛው ነው የቀረህ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| ከመሀል ነው የቀረህ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |

ተርጓሚ፡-ሀብታሙ ኮምትኪት

### 4.1.2 ሃይማኖታዊ አውድ

የቤንች ማህበረሰብ እንደሌሎች ማህበረሰቦች የራሳቸው የሆኑ ሃይማኖቶች አሏቸው፡፡ በጥናቱ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ላይ እንደተገለፀው እነዚህ ሃይማኖቶች የማህበረሰቡ አባላት በልምድ የወረሷቸው እና በባህላዊ መንገድ ይሆንልናል (ይደረግልናል) ብለው የሚያምኑባቸው ናቸው፡፡ በአሁኑ ሰዓት የማህበረሰቡ አባላት በሰፊው ከሚያምኑባቸው ሃይማኖቶች መካከል አንዱና ዋነኛው የቃልቻ እምነት ነው፡፡

#### 4.1.2.1 የቃልቻ ዱብ (የቃልቻ ሙዚቃ)

የቤንች ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ባህላዊ እምነት ያለው መሆኑን ቀደም ብሎ በማህበረ-ባህላዊ ዳራው ስር የተገለፀ ሲሆን ከእነዚህ መካከል የቃልቻ እምነት አንዱ ነው፡፡ ይህ የቃልቻ እምነት የራሱ የሆነ ክብረ በዓልና ንግስ አለው፡፡ በዚህ ክብረ በዓልና ንግስ ጊዜ የእምነቱ ተከታዮች የተለያዩ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን ይከውናሉ፡፡ ከሚከውኗቸው የትውን ጥበባት ቅርጾች መካከል አንዱ ዱብ ነው፡፡ ይህን ዱብ የሚከውኑት በክብረ በዓሉ ላይ የተገኙት የእምነቱ ተከታዮች በሙሉ ናቸው፡፡ ነገር ግን ዱቡን በመጀመሪያ የሚያስጀምሩት ወይዘሮች ናቸው፡፡ ከዚያ በኋላ የእምነቱ ተከታዮች በሙሉ በህብረት በመሆን አብረው ያዜሙታል፡፡ ይህ ዱብ በሚዜምበት ወቅት በወሸ፣ በክራር እና ጃስ ሲታጀብ ተመልክቻለሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ክራሩን የሚመቱና ወሹን የሚነፉት ወይዘሮች ናቸው፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች እንኳ ወይዘሮች ከሌሉ ክራሩን እራሱ ባለቃልቻው ይመታዋል እንጅ ማንኛውም የእምነቱ ተከታይ የሆኑት ሰዎች አይመቱትም፡፡ ሌሎች ሰዎች ክራሩን የማይመቱበት ምክንያት ባለቃልቻው የማይፈቅደውን ምግብ እና መጠጥ (ጎመን፣ የጤፍ እንጀራ እና ቦርዴ[15]) ከበሉና ከጠጡ መንፈሱ ይረክሳል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

በነዚህ ወቅት የሚዜሙት ዱቦች ባለቃልቻውን የሚያሞግሱና በዜማቸው ተመሳሳይ የሆኑ ናቸው፡፡ ዱብ ባለቃልቻው ከየት እንደመጣ፣ የማን የዘር ሀረግ እንደሆነ፣ ባለቃልቻ የሆነው ከዘር ሀረጎቹ ወርሶ እንደሆነ፣ ለጋስነት እና ጥሩ ስነ-ምግባሩ እስከ

---

[15] ቦርዴ ማለት ከበቆሎ ባህላዊ መጠጥ ነው፡፡

ምን ደረጃ እንደሚደርስ ይገልጹበታል። ለምሳሌ ያህል ከዚህ በታች ያለውን ግጥም ማየት ይቻላል።

| ግጥሙ በመገኛ ቋንቋው | ትርጉም በአማርኛ |
|---|---|
| Shasha-gakitnasa | ሻሻ የጋኪት ልጅ |
| Qaznisi yarsargusa | አውጥቶ የማይመልስ |
| Utsni etargusa | ሰጥቶ የማይወስድ |
| Soteti sovxn skosagus | የባለአባት ልጅ እሱም ባለአባት |
| Usasi borsi tosxn barsagus | በህል ለውጦ ብር የሚለግስ |
| Balababa wumbaba | ድሀ የሚታደግ |
| Menis kuchmaxn woxagus | ምስኪን የሚያሳድግ |
| Dodab harkus | ደግ የደግ ልጅ |

ተርጓሚ፡- አዳሙ ሀንታያብ

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ ዱቦች በማንኛውም አጋጣሚዎች የሚከወኑት ከዋኞች እና ታዳሚዎች የጋራ ቅብብሎሽ እና ውዝዋዜ በማድረግ ነው። የዱብ ክዋኔ ሁል ጊዜ ማለት ይቻላል የሚከወነው በመቅዳት እና በማስመሰል ነው። እንዲሁም አንድ ማህበረሰብ በሚከውነው ሙዚቃ አማካኝነት የራሱን ልምድና መልዕክት ይለዋወጥበታል ብለው Turner and McArthur (1990 :85) እንደገለጹት ሁሉ የቤንች ማህበረሰብ አባላት በሚያዜሟቸው ዱቦች አማካኝነት የራሳቸውን መስተጋብር፣ ታሪካዊ አመጣጥ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ስሜት እና ፍላጎት ይገልጹባቸዋል። እንዲሁም እርስበርሳቸው በቀላሉ መልዕክት ይለዋወጡባቸዋል።

## 4.2 የቤንች ሀገረሰባዊ ዳንስ (ዶር)

የቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ከሆኑት መካከል አንዱ ሀገረሰባዊ ዳንስ ነው። አንድ ዳንስ የሚከወንበት የራሱ የሆነ የመከወኛ አጋጣሚ፣ ቦታ እና ጊዜ አለው ብለው Matthews (1990 :102) ገልፀውታል። እንደ ምሁሩ ገለፃ ሁሉ የቤንች ማህበረሰብ ዶር የራሱ የሆነ የመከወኛ አጋጣሚ፣ ቦታ እና ጊዜ አለው። እነዚህ አጋጣሚዎች ማህበረ-ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ አውድ ተብለው ተመድበዋል። በእነዚህ አጋጣሚዎች

የሚከወኑት ዶሮች በአብዛኛው የማህበረሰቡን ፍላጎት፣ እምነት እና አመለካከት በመግለጽ በኩል ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

### 4.2.1 ማህበረ- ባህላዊ አውድ

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የቤንች ማህበረሰብ ትውን ጥበባትን የሚከውኑባቸው የራሳቸው የሆኑ ማህበረ-ባህላዊ አውዶች አሏቸው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ በማህበረ-ባህላዊ አውዶች ስር የተመደቡት ወርደት እና የብ ናቸው፡፡ በእነዚህ አውዶች በሚከሰቱ ሁነቶች አማካኝነት የማህበረሰቡ አባላት የተለያዩ ዱሮችን ይከውናሉ፡፡

#### 4.2.1.1 የወርደት ዶር (የሰርግ ዳንስ)

የቤንች ማህበረሰብ ዶሮች ከሚከወኑባቸው አጋጣሚዎች መካከል አንዱ ወርደት ሲሆን በዚህ ወቅት የተለያዩ የዶር ዓይነቶች ሲከወኑ በመስክ ቆይታዬ ተመልክቻለሁ፡፡ ከጥናቱ ማህበረ-ባህላዊ ዳራው ላይ እንደተገለፀው የቤንች ማህበረሰቦች አራት ዓይነት የጋብቻ ሥርዓቶች ያሏቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን በማህበረሰቡ ዘንድ የወርደት ሥርዓት ክዋኔዎች የሚከወኑት በሶስቱ የጋብቻ ዓይነቶች ብቻ ነው፡፡ በእነዚህ የወርደት ስርዓት ማህበረሰቡ የተለያዩ ዝግጅቶችን (ምግብ፣ መጠጥ፣ የተለያዩ ለሙሽራውና ለሙሽሪት መጊያጌጫ የሚሆኑ ነገሮች) ካዘጋጁ በኋላ እየበሉና እየጠጡ በሙሽራውና በሙሽሪት ቤት በዘመዶቻቸው አማካኝነት የተለያዩ ዶሮች ይከወናሉ፡፡ ዶሮቹ የሚከውኑት በሶስቱ የጋብቻ ዓይነቶች (በማባበል ጋብቻ፣ በጠለፋ ጋብቻ እና በቤተሰብ ስምምነት በሚፈፀም ጋብቻ) ነው፡፡ በእነዚህ የጋብቻ ዓይነቶች ዶሩ የሚጀመረው የሁለቱ ተጋቢዎች ቤተሰብ የወርደቱን ቀን ቆርጠው ከተለያዩበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ በነዚህ ጊዜያት የሚከወኑት ዶሮች በእንቅስቃሴያቸው እና በሚያስተላልፉት መልዕክት የተለያዩ ናቸው፡፡ በወርደት ወቅት የሚከወኑት ዶሮች በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ተከፍለው ከዚህ በታች በምስላዊ ገለጻ በመደገፍ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **ዳሶዬ ዶር፡-** ይህ የዶር ዓይነት በወርደት ጊዜ ከሚከወኑ ዶሮች መካከል አንዱ ሲሆን የሚከወነውም ·በሙሽራው እና በሙሽሪት ቤት መካከል በሚገኝ ወንዝ ዳር ነው፡፡ የዚህ ዶር ከዋኖች በአብዛኛው ያላገቡ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ከዋኞች ቁጥራቸው አራት ሲሆኑ በሚደንሱበት ወቅት አራቱ ሰዎች በአንድ ላይ በመሆን ሁለቱ ወደ ፊት ሲሄዱ ሁለቱ ደግሞ ወደ ኂላ እያሉ በመተላለፍ ይጨፍራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሌሎች አራት ሰዎች ደግሞ ተራ እስከሚደርሳቸው ከዳር በመሆን ማይት በእጃቸው ይዘው እየተንቀሳሱ ሲያጅቡ ተመልክቻለሁ፡፡ ከዚህ በታች ካለው ምስል መመልከት እንደሚቻለው እድሜያቸው ለትዳር ያልደረሱ ህፃናት እና ባለትዳር የሆኑት ደግሞ ራቅ ብለው በመቆም ወይም በመቀመጥ ይመለከታሉ፡፡

በዚህ ዶር የሚሳተፉ ከዋኞች የአንድ ጎሳ አባል ያልሆኑና ምንም ዓይነት የስጋ ዝምድና የሌላቸው ናቸው፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ሁለቱ ወጣቶች ለትዳር የሚፈላለጉበት ጭፈራ ስለሆነ ነው፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ዘንድ የአንድ ጎሳ አባል የሆኑ እና የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች መጋባት ስለማይችሉ ነው፡፡ አንድ ወንድ የጎሳው አባል ከሆነች ሴት ጋር አብሯት ከጨፈረ ደግሞ “ሊያገባት ነው እንጅ እንዴት ወርደት ላይ አብረው ይጨፍራሉ?” ተብሎ በማህበረሰቡ ስለሚከለከል ነው፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ የማህበረሰቡ አባል የሆነው ከድር ሸባ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡ “በባህላችን ሁለት የስጋ ዝምድና ያላቸው ወንዶች እና ሴቶች በዳሶዬ ዶር ላይ አብረው አይጨፍሩም ነውር ነው ምክንያቱም ይህ ጭፈራ የመተጫጫ ጭፈራ ነው፡፡” (ደብረወርቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡



ምስል 4.1. ዳሶዬ ሲጨፍሩ

በአጠቃላይ ይህ ዶር እኔ እንደተመለከትሁት በሁለት ወጣት ወንዶችና ሴቶች ከወንዝ ዳር የሚጨፈር ነው፡፡ ከወንዝ ዳር የሚጨፈረውም የሙሽሪት ቤተሰቦች ወንዙን ተሻግረው ከሂዱ የጎሳ ግጭት ስለሚነሳ ያንን በመፍራት ነው፡፡ ዶሩ መጨፈሩ ወርደቱን ከማድመቂያነት ባለፈ በማህበረሰቡ አባላት መካከል የትስስር መንፈስን በመፍጠር በኩል ሰፊ ድርሻ አለው፡፡

**2. ባባ ዶር፡-** ይህ የዶር ዓይነት የሚከወነው ከዳሶዬ ዶር ቀጥሎ ሲሆን የሚከወነውም በሙሽራው እና በሙሽሪት ቤት መካከል በሚገኝ ወንዝ ዳር ወይም ከሙሽሪት ቤት ነው፡፡ የዶሩ ከዋኞች የማንኛውም ማህበረሰብ አባል የሆኑና በወርደቱ ቦታ የተገኙ ሰዎች ናቸው፡፡ ሚያዚያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም በቦታው ተገኝቼ እንደተመለከትሁት ዶሩን የሚከውኑት ወንዶች እና ሴቶች በህብረት ሆነው ክብ በመስራት እየተሽከረከሩ ነው፡፡ ከዋኞች ክብ ሰርተው የሚከውኑበትን ምክንያት ታደሰ ከተማራሽ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡ "በባህላችን አንድ ዶር ሲጨፈር ከዋኞች ክብ ሰርተው የሚሽከረከሩ ከሆነ ሌሎች ተመልካቾችን ኑ እንጫወት ቦታው ክፍት ነው ለማለት ነው፡፡"

(ደብረወርቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡ ሌሎች ሰዎች ደግሞ በዚህ ጊዜ ፍዝ ተመልካች ይሆናሉ፡፡ ዶሩ በሚከወንበት ወቅት በማይት፣ በጠብመንጃ፣ በክራር እና በቶሪ የዱብ መሳሪያ ይታጀባል፡፡



ምስል 4.2 ባባ ሲጨፍሩ

ይህ ዶር ክብ ተሰርቶ መከወኑ የከዋኞችን አመለካከት ከመግለፅ ባለፈ ከቤት አሰራራቸው ጋር ግንኙነት አለው፡፡ ምክንያቱም የማህበረሰቡ ቤት የሚሰራው ክብ በሆነ ቅርፅ ነው፡፡

**3. ናሪ ዶር፡-** ይህ ዶር የሚከወነው ከሙሽሪት ቤት ብቻ ነው፡፡ የዱሩ ከዋኞች ሁለት ወጣት ያላገቡ ሴቶች እና ወንዶች ናቸው፡፡ እነዚህ ከሁለት ምንም ዝምድና ከሌላቸው ጎሳ የመጡና ዳሶዬ ሲጨፍሩ ለጋብቻ የተመራረጡ ወጣቶች ናቸው:: ሁለቱ ጥንድ ከዋኞች በተመሳሳይ አቅጣጫ ወደ ፊት እና ወደ ኋላ እየተያዩ ለተወሰነ ደቂቃ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ከዚያም ፊርግን የተባለው የዱብ መሳሪያ ሲነፋ እሷ ከፊት እሱ ከኋላ በመሆን እየተሽከረከሩና ወንዱ እና ሴቷ ማይት በመቀባበል ሲጨፍሩ ተመለከትሁ፡፡

ማይት የሚቀባበሉበትን ምክንያት አቶ ኩጁ መንግስቴ በጠየቅኂቸው መሰረት እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል።

> ይህ ጭፈራ በሚጨፈርበት ጊዜ ማይቱን የሚቀባበሉት በጣሊያን ጦርነት ጊዜ ወንዶች ጦርነት ሲሄዱ ሴቶች ደግሞ የጣሊያንን ጦርነት ሳይፈሩ ናሪ የሚባል ዘፈን እየዘፈኑ ለወንዶች ስንቅ ያቀብሉ ስለነበረ። ይህ የሚያመለክተው ደግሞ እነሱም ጀግና መሆናቸውን ነው። (ኮብ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም)።

"ይህ ዶር የሚያገለግለው ከዚህ ጎሳ ይችን ልጅ ላገባት መርጫለሁ እና የእኔ ስለሆነች ማንም እንዳይነካብኝ የሚለውን መልዕክት ማስተላለፊያ ስለሆነ የግድ አንድ ወንድ ለትዳር ያጫት ልጃገረድ ካለች አብሯት መጨፈር አለበት።" (ደብረወርቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም)። ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ይህ ዶር መጨፈሩ የማህበረሰቡን ጀግንነት ከመግለጽ ባለፈ አንድ ወንድ ለጋብቻ የመረጣትን ሴት ለሱ መሆኗን ለሌሎች ሰዎች የሚገለጽበት አጋጣሚ ጭምር መሆኑን ነው።



ምስል 4.3 ናሪ ሲጨፍሩ

4. **ቶናስ ዶር**፡- ይህ ዶር ስያሜውን ያገኘው ቶህ ከሚባለው የዱብ መሳሪያ ነው። የሚከወነውም ልክ እንደ ናሪ ከሙሽሪት ቤት ብቻ ነው። ዶሩ የሚከወነው ለየብ፣ ለወርደት እና ለቃልቻ ነው። በእነዚህ ሶስት የመከወኛ አጋጣሚ በሚከወንበት ወቅት ቶህ በሚባለው ባህላዊ የትንፋሽ የዱብ መሳሪያ ይታጀባል።

ከምስል 4.4 ማየት እንደሚቻለው ቶናስ ዶርን የሚከውኑት ሴቶች እና ወንዶች በህብረት በመሆን ሲሆን በሶስቱ አጋጣሚ የሚከወነው ክብ በመሆን እና በመዞር ነው። ክቡም እንደሚከወንበት አጋጣሚ የተለያየ መልዕክት አለው። ከላይ እንደተገለፀው በወርደት ጊዜ ክብ ሰርተው የሚጨፍሩ ከሆነ ተመልካቾችን ኑ እንጫወት ቦታው ክፍት ነው ማለት ሲሆን በየብ ጊዜ ደግሞ ክብ የሚሰሩት ሟቹ ከነሱ መካከል እንደነበር ለማስታወስ ነው። ነገር ግን ለወርደት ሲጨፍሩ የሚጠቀሙበት ዱብ እና ለሌሎች አጋጣሚዎች ሲጨፍሩ የሚጠቀሙበት ዱብ የተለያየ እንደሆነ ተመልክቻለሁ። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ዶሩ እንደሚከወንበት ቦታ እና ጊዜ የተለያየ መልዕክት ስለሚያስተላልፍ ነው።



ምስል 4.4 ቶናስ ሲጨፍሩ

በአጠቃላይ በወርደት ወቅት የሚከወኑት የቤንች ዶሮች በአብዛኛው የሚከወኑት በወጣት ከዋኞች ነው። እነዚህ ከዋኞች ሙያውን የሚለምዱት በአካባቢያቸው ካለው ማህበረሰብ ነው። ዶር የሚለምዱበት ዋናው ምክንያት የማህበረሰቡ አባላት በአብዛኛው የትዳር አጋር የሚመራረጡት በዚህ የወርደት ጭፈራ ወቅት ስለሆነ ነው። በዚህ ምክንያት

የግድ አንድ ልጃገረድ ለመታጨት ስትል በወርደት ጭፈራ ወቅት ብትችልም ባትችልም መጨፈር አለባት፡፡

#### 4.2.1.2 የየብ ዶር (የለቅሶ ዳንስ)

የቤንች ማህበረሰቦች እንደ ሌሎች ማህረሰቦች የራሳቸው የሆኑ የየብ ስርዓቶች እንዳሏቸው ቀደም ብሎ በማህበረ-ባህላዊ ዳራው ላይ ተገልጿል፡፡ እነዚህ ስርዓቶች እንደ ሟቹ እድሜ እና የማህበራዊ ደረጃ የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህም ማለት ባለቃልቻ ሲሞት ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ ወይዘሶች እየወጡ እና እየገቡ የተለያዩ ዱቦችን እያዜሙ የባለቃልቻውን መሞት ለእምነቱ ተከታዮች ያበስራሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት የእምነቱ ተከታዮች ባለቃልቻው መሞቱን ተረድተው ወደ ፊት ቃልቻው አርፎበት ሊያመልኩበት የሚችሉትን ሰው ከባለቃልቻው ልጆች እንዲመርጡ ለማድረግ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የእምነቱ ተከታዮች ይህን ዱብ ሰምተው ወደ ፊት ቃልቻው የሚያርፍበት ሰው ከባለቃልቻው ልጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች ካልመረጡለት እና እዚያ ሰው ላይ ቃልቻው ካላረፈ አስከሬኑን መቅበር አይችሉም፡፡ ምናልባት ቢቀብሩት እንኳን ቀብረነዋል ብለው አያወሩም፡፡ ይህ የሚሆነው ቃልቻው ሌላ ሰው ላይ ሳያርፍ ከተቀበረ የእምነቱ ተከታዮች ሰላም ሊያጡ ስለሚችሉ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ኩጁ መንግስቴ እንዲህ ሲሉ አብራርተውልኛል፡፡ “በእምነታችን ቃልቻው ሌላ ሰው ላይ ሳያርፍ ባለቃልቻውን ከቀበርነው መንፈሱ ይቆጣና ጤናችንን፣ ሀብት ንብረታችንን አልፎ ተርፎ የወለድናቸውን ልጆች ሊያሳጣን ይችላል፡፡” (ኮብ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡

የማህበረሰቡ አባላት በየብ ጊዜ የሚጨፍሩት ለባለቃልቻ ብቻ ሳይሆን ሀብትና ንብረት ላላቸው ሰዎች ጭምር ነው፡፡ ሀብትና ንብረት ለሌላቸው ሰዎች እና ለህፃናት ግን ሲሞቱ አይጨፈርም፡፡ በመስክ ቆይታዬ እንዳረጋገጥሁት ለነዚህ ሰዎች የማይጨፈርበት ምክንያት በየቡ ላይ ለሚከውኑት ሰዎች የግድ የሚበላ እና የሚጠጣ ነገር የሚዘጋጅላቸው የሟቹ ድርሻ ከሌሎች የቤተሰብ አባላት ተከፍሎ ስለሆነ ነው፡፡ ይህ የሚደረግበትን ነገር ሰለሞን ፈጠነ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡

> የሟቹ ሀብት እና ንብረት ተከፍሎ ለሚጨፍሩት ሰዎች የሚዘጋጀው የሱ ድርሻ ስለሆነ ጦሱን ይዞ ይሄድ በማለት ነው፡፡ እንዲሁም ሀብትና ንብረት እያለው በየቡ ላይ ቲያርብ እየተመታ ካልተጨፈረለት የሟቹ መንፈስ ይቆጣል ተብሎ

ስለሚያስብ ነው፡፡ ለህፃናት ደግሞ የማይጨፈረው በልዩ ልዩ ምክንያቶች በባህላችን ስለማይፈቀድ ነው[16]፡፡ (አዲስ አለም፣ ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም)

ከላይ እንደተገለፀው የቤንች ማህበረሰብ በየብ ጊዜ ከሚያከናውኗቸው ስርዓቶች መካከል አንዱ ዶር ሲሆን በየብ ጊዜ የሚከወኑት ዶርች እንደሚከወኑበት አጋጣሚዎች እና ከዋኞች የተለያዩ ተግባራት አሏቸው፡፡ ይሁን እንጂ ዶሩ የሚጀመረው ወዲያውኑ ሟቹ እንደ ሞተ ሳይሆን የተለያዩ ዝግጅቶች ከተደረገ በኋላ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የሞተው ሰው ባለቃልቻ ከሆነ የቅርብ ተከታዮች ግቢውን እያፀዱ፣ እየወጡ እና እየገቡ መሞቱን ለእምነቱ ተከታዮች በዱብ ካበሰሩ በኋላ ነው፡፡ የሞተው ሰው ደግሞ ባለቃልቻ ካልሆነ ወዲያውኑ እንደ ሞተ ለዘመዶቹ መልዕክት ተልኮ ከመጡ በኋላ ወደ ቀብር ቦታው ሲሄድ ጀምሮ ይጨፈራል፡፡

በየብ ላይ የሚከወኑት ዶሮች እንደሚከወኑበት ጊዜ እና ቦታ ይለያዩ እንጅ ለማንኛውም ሰው (ለባለቃልቻ እና ሀብት ንብረት ላላቸው ሰዎች) በአከዋወናቸውም ሆነ በመከወኛ ቁሶች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ዘንድ ባለቃልቻ እና ሀብት ንብረት ያላቸው ሰዎች ሲሞት የእምነቱ ተከታዮች ከማልቀስ ይልቅ የሙት መንፈሱን ለማስደሰት ሲባል በቲያርብ፣ በፊርግንና በቶህ የዱብ መሳሪያዎች፣ በጃስና በማይት በመታጀብ ይከውናሉ፡፡ የየብ ዶሮችን ከዋኞችንና የክዋኔውን እንቅስቃሴ መሰረት በማድረግ በአራት ክፍሎች ተከፍለው ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. **የሮ (ይህ) ዶር**፡- ይህ ዶር የሚከወነው ሟቹ በሞተ በመጀመሪያው ቀን ወደ ቀብር ከመሄዱ በፊት እና ከቀብር በኋላ ነው፡፡ ከዚህ በታች ካለው ምስል መመልከት እንደሚቻለው የየሮ ዶር ከዋኞች የእድሜ ባለፀጋ ወንዶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች የሚከውኑት "ይህ ይህ" የሚል ድምፅ እያሰሙ፣ ማይታቸውን እየሰበቁ፣ እየዘለሉ እና እየተሽከረከሩ ነው፡፡ ከእነሱ መካከል ቲያርብ መምታት የሚችሉት ቲያርቦችን እየመቱ ከመሀል በመሆን ሲንቀሳቀሱ ሴቶች ደግሞ ከሟቹ ቤት በር አፍ ላይ በመሆን "እልል" እያሉ በድምፃቸው ሲያጅቧቸው ተመልክቻለሁ፡፡

[16] በባህሉ የማይፈቀድበት ምክንያትም አሁን ለሞተው ህፃናት ከተጨፈረ እናቱ ደግማ ሌላ ልጅ አትወልድም ተብሎ በብሔረሰቡ ዘንድ ስለሚታመን ነው፡፡



ምስል 4.5 የሮ (ይህ) ሲጨፍሩ

ይህን ዶር የእድሜ ባለፀጋ የሆኑት ወንዶች ብቻ የሚከውኑበት ምክንያት የሞተውን ሰው ከአምላኩ ጋር በዚህ ጭፈራ እናማልደዋለን ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ በዚህ ዶር ሴቶች የማይሳተፉበት ምክንያት ደግሞ በባህላቸው ሴት ልጅ ጨፍራ ከአምላክ ጋር የሙት መንፈስ አታገናኝም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ ኩጁ መንግስቴና ሌሎች ሰዎች አረጋግጠውልኛል (ኮብ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡ Matthews (1990፡ 102) ዳንስ ከፍተኛ የሆነ ጉልበትና እንቅስቃሴ የሚጠይቅ ነው ብለው እንደገለጹት፡፡ የቤንች ማህበረሰብ ሴቶች በዚህ ዶር የማይሳተፉበት ምክንያት ሲከወን ከፍተኛ የሆነ ጉልበት ስለሚጠይቅና በማህበረሰቡ አባላት ደግሞ ሴቶች በተፈጥሯቸው ጉልበት የላቸውም ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡

2 **ሲሶ ዶር፡-** ይህን የዶር ዓይነት የሚከወኑት ወንዶች ናቸው፡፡ በክዋኔው ወቅት እንደተመለከትሁት የሚከውኑት የሞተውን ሰው ቀብረው እንደመጡ በተዘጋጀው ድንኳን አጠገብ በመሆን "ሲሶ ኦኦ" የሚል ድምፅ እያሰሙ በመስመር ሆነው ወደ ፊት እና ወደ ኋላ በመንቀሳቀስ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ቲያርቦችን የመምታት ችሎታ ያላቸው ከመሀል ሆነው እየመቱ ሲዞሩ ሴቶች ደግሞ ከኋላ በመሆን "እልል" እያሉ እጃቸውን ወደ ላይ በማንሳት እና በድምጻቸው ሲያጅቧቸው ተመልክቻለሁ፡፡ ይህ

የሚሆንበትን ምክንያት አቶ በላይ አዲሱ በጠየቅኋቸው መሰረት እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡ “በባህላችን የሞተውን ሰው ቀብረን እንደመጣን የምንጨፍርበት ምክንያት እሱን ለመቅበር ስንሄድ ያጠፋነውን ጊዜ እንደማይጎዳንና አምላኩ በሰላም መንፈሱን እንዲቀበለው ለመለመን ነው፡፡” (ሚያህ፣ ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም)፡



ምስል 4.6 ሲሶ ሲጨፍሩ

3 **ቶናስ ዶር**፡- ይህ የዶር ዓይነት ከላይ በወርደት ዶሮች ላይ እንደተገለፀው ቶናስ የሚለውን ስያሜ ያገኘው ቶህ ከሚባለው የዱብ መሳሪያ ነው፡፡ የዶሩ ከዋኞች ሁሉም በየቡ ላይ የተገኙ ወንዶች እና ሴቶች ናቸው፡፡ ሲከወን እንደተመለከትሁት ይህ ዶር የሚጨፈረው ክብ በመስራት እግራቸውን ወደፊትና ወደኋላ በማንቀሳቀስ እና በመዞር ነው፡፡ በየብ ጊዜ ክብ ሰርተው የሚከውኑበትን ምክንያት ሀብታሙ ኮምትኬት እንዲህ ሲል ገልፆልኛል፡፡ “በባህላችን በየብ ጊዜ ክብ ተሰርቶ የሚጨፈረው ሟቹ ከእኛ መሀል እንደ ነበረ ለማስታወስ ነው” (ሚዛን፣ ግንቦት 6 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡ ይህ ዶር በወርደት ጊዜ ከሚከውነው ዶር በአከዋወኑ እና ለማጀቢያነት በሚጠቀሙባቸው የመከወኛ ቁሶች ተመሳሳይ ይሁን እንጂ በመልዕክት ግን የተለያዩ ናቸው፡፡

4. **ጌያሶ (አስ) ዶር**፡- ይህ ዶር የሚከወነው ሟቹ በሞተ በአራተኛ ቀን አስ የሚባል የመብል እና የመጠጥ ዝግጅት ከሞተው ሰው ቤት ተዘጋጅቶ እየተበላና እየተጠጣ ነው፡፡ ዶሩን የሚከው‌ኑት ወንዶች ብቻ ሲሆኑ ከሟቹ ቤት ፊት ለፊት መስመር ሰርተው ወደ ፊት እና ወደ ኋላ እየተንቀሳቀሱ፣ ጃስ እየመቱና ማይት እየሰበቁ ነው፡፡ ጃሱን የሚመታው የልጅ ባል ካለ የልጅ ባል ከሌለ ደግሞ የቅርብ ዘመድ ነው እንጂ የስጋ ዝምድና የሌለው ሰው አይመታም፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ በደንብ መጨፈር እና ጃስ መምታት ያለበት ከሟቹ ቤት በተደጋጋሚ ጥሩ ምግብ የበላ ነው ተብሎ በማህበረሰቡ ስለሚታመን ነው፡፡

ከላይ እንደተገለጸውና ከዚህ በታች ካለው ምስል ማየት እንደሚቻለው አስ ዶር የሚከወነው በተዘጋጀው ድንኳን አጠገብ በመሆን ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ዶሩን የሚከውኑት ሰዎች መስመር ሰርተው ወደ ፊት እና ወደ ኋላ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ጃሱን የሚመታው የልጅ ባል ከመሀል በመሆን የፊት እግሩ እስከሚደማ ድረስ ሲደበድብ ተመለከትሁት፡፡ በዚህ ጊዜ ለምን እግሩ እስከሚደማ እንደሚደበድብ በጠየቅኋቸው መሰረት አቶ ሻንቆ ጋኪናስ እንዲህ ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡

> በየብ ጊዜ አንድ ሰው ጋሻ ሲመታ የፊት እግሩ ጣት ከደማ ለሟቹ በደንብ አዝኗል ማለት ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ የፊት እግሩ ጣት ካልደማ በደንብ አላዘነም ተብሎ ይነወራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሟቹ መንፈስ ሰላም አይሰጠውም[17] ተብሎ ይታሰባል፡፡ (ደብረወርቅ፣ ሚያዝያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡

በአጠቃላይ ይህ የዶር አይነት በማህበረሰቡ ዘንድ የሞተው ሰው ለማን ጥሩ አብልቶና አጠጥቶ በደንብ እንደጨፈረለት መለያ በመሆን ያገለግላል፡፡

---

[17] የሙት መንፈሱ ሲተኛ እየመጣ ይቆጣዋል፡፡



ምስል 4.7 አስ ሲጨፍሩ

## 4.2.2.ሃይማኖታዊ አውድ

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የቤንች ማህበረሰብ ከሚያምኑባቸው ባህላዊ እምነቶች መካከል አንዱ የቃልቻ እምነት ነው፡፡ ይህ የቃልቻ እምነት የማህበረሰቡ አባላት ዶሮች ከሚከውኑባቸው አጋጣሚዎች አንዱ ነው፡፡

### 4.2.2.1 የቃልቻ ዶር (የቃልቻ ዳንስ)

የማህበረሰቡ ዶር የሚከወነው የቃልቻው በዓል በሚከበርበት፣ የስልጣን ሽግግር በሚያደርግበት (በሚነግስበት) እና አዲስ ዘመን[18] በሚቆጥርበት ወቅት ነው፡፡ በነዚህ ጊዜያት የእምነቱ ተከታዮች በዓሉ በሚከበርበት ስፍራ በመገኘት የተዘጋጀውን ምግብ እና መጠጥ እየበሉ እና እየጠጡ የግድ መከወን አለባቸው፡፡ ያለበለዚያ ግን እንሞታለን፣ እንታመማለን፣ አዝመራው አይበረክትም ብለው ያስባሉ፡፡ ለቃልቻ የሚጨፈሩት ዶሮች

---

[18] በቃልቻው ህግ መሰረት ህዳር ላይ የሚደረገው የዘመን አቆጣጠር ማለት ነው፡፡

በዓይነታቸው በአብዛኛው ተመሳሳይ ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1.ቡብ

2.ቶናስ

3.ዳሶይ

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ዶሮች የሚከወኑት በመጀመሪያ ቃልቻው ያረፈበት ሰው ከሞተበት ቀን አንስቶ በሌላ ሰው እስከሚያርፍ ደረስ ነው፡፡ ቃልቻው በሌላ ሰው ላይ ማረፉን የእምነቱ ተከታዮች የሚያረጋግጡት ከባለቃልቻው ልጆች አንዱ የቃልቻው ማረፊያ ተብላ ከተዘጋጀች ትንሽ የሳር ጎጆ ቤት ዘሎ ገብቶ ከተንፈራገጠ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ ሰለሞን ፈጠነ እንዲህ ሲሉ አረጋግጠውልኛል፡፡ "ቃልቻው በሌላ ሰው ላይ ማረፉን የምናረጋግጠው ቃልቻው ያረፈበት ሰው ለቃልቻው ማረፊያ ተብላ ከተሰራች አነስተኛ የሳር ጎጆ ቤት ዘሎ ገብቶ እየተንፈራገጠ ከጮኸ ነው፡፡" (አዲስ አለም ቀበሌ፣ ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም) ነገር ግን በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ ይህ ምልክት ከሞተው ሰው ልጆች በአንዱ ካልታየ ቃልቻው አልተሸጋገረም ተብሎ ስለሚታመን የእምነቱ ተከታዮች ክብ በመስራት ከቃልቻው ቤት ፊት ለፊት "እሆ" የሚል የመለማመኛ ድምፅ እያሰሙ ምልክቱ እስከሚታይ ድረስ ይጨፍራሉ፡፡

ሌላው የቃልቻ ዶር የሚከወንበት ወቅት ደግሞ የቃልቻው ክብረ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ነው፡፡ በጥናቱ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ላይ እንደተገለጸው የቃልቻ በዓል የሚከበረው በማህበረሰቡ ዘንድ በዓመት ሶስት ጊዜ ሲሆን ይኸውም በመስከረም፣ በህዳር እና በሚያዝያ ወራት ነው፡፡[19] ነገር ግን በሁሉም በዓላት የእምነቱ ተከታዮች የተለያዩ ስጦታዎችን (ለምሳሌ፡- ፍየል፣ ከብት እና ገንዘብ) ይዘው ከባለቃልቻው ቤት በመምጣት የተዘጋጀላቸውን ምግብና መጠጥ በመብላት እና በመጠጣት ቡብ፣ ዳሶይ እና ቶናስ ዶሮችን እስከ ሶስት ቀን ይጨፈራሉ፡፡ በክወኔው ወቅት እንደተመለከትሁት ዶሩ በክራር፣ በእጨጭ፣ በአሞራ ክንፍ እና በቶሪ ይታጀባል፡፡

---

[19] በእነዚህ ወራቶችም የሚከበሩት የተለያዩ ክብረ በዓላት ናቸው፡፡ ማለትም በህዳር የቃልቻው የዘመን መለወጫ፣ በመስከረም ቃልቻው ለመጀመሪያ ጊዜ የእምነት ተከታዮችን ያፈራበት ወቅት መሆኑ፣ በሚያዝያ ደግሞ የቃልቻው መንፈስ ከግራዋ አበባ ጋር ተከትሎ የእምነቱን ተከታዮች ሊባርክ የሚመጣበት ወር ስለሆነ ነው፡፡

የቃልቻ በዓል ሲከበር የእምነቱ ተከታዮች ዶሩን የሚከውኑበት ዋናው ምክንያት የጎደለባቸውን ነገር ቃልቻው ከሞላላቸው እና ወደፊት በሰላም ከብቶቻቸውን፣ ልጆቻቸውን እና አዝመራቸውን እንዲጠብቅላቸው በማሰብ ነው። ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ሻንቆ ጋኪናስ እንዲህ ሲሉ አብራርተውልኛል። "አባቴ ባለቃልቻ ነው እና የቃልቻው የዘመን መቆጠሪያ ክብረ በዓል በሚከበርበት ወቅት የእምነቱ ተከታዮች ከቤታችን መጥተው የሚከውኑት ለሚቀጥለው ዓመት በሰላም እንዲያደርሳቸው[20] በማሰብ ነው።" (ደብረወርቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም)




ምስል 4.8 ለባለአባት ሲጨፍሩ

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ ዶር በሚከወኑበት ወቅት የማህበረሰቡን ማንነት፣ አመለካከት፣ እምነት፣ ማህበራዊ ግንኙነት እና ማህበራዊ ደረጃ ይገልጻሉ። በመስክ

[20] ሰብስቦ እንዲያደርሳቸው የተባለው ቃልቻው ነው።

ቆይታዬ እንደተመለከትሁት ብዙውን ጊዜ የቤንች ዶሮች በጋራ የሚከወኑና የመከወኛ አጋጣሚ የሚፈልጉ ሲሆኑ ሁሉም የዶር ዓይነቶች በባህላዊ የዱብ መሳሪያ የሚታጀቡ ናቸው፡፡

## 4.3 የቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት የመከወኛ ቁሶች

ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሚከወኑበት ወቅት የራሳቸው የሆነ የመዋቢያና የማድመቂያ ቁሶች እንዲሁም ለማድመቂያነት የሚውሉ የሙዚቃ መሣሪያዎች እና አልባሳት አጀብ ያስፈልጉታል፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ ፈቃደ እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል፡፡ "…የሀገረሰብ ልብሶች ተለብሶ፣ በሀገረሰብ የሙዚቃ መሣሪያዎች ታጅቦ፣ አስፈላጊው መጊያጌጥ ከተከናወነ በኋላ እንደየሀገረሰቡ ልማድ አስፈላጊው ዝግጅት በሙሉ ከተደረገ በኋላ የሚከወነውን ነው ሙያው የሚያጠናው፡፡" (ፈቃደ፣ 1991፡11)

አንዳንድ ቁሶች ከመዋቢያና ከማድመቂያነት ባለፈ ተበታትኖ በሰፈረው ማህበረሰብ ውስጥ በመልዕክት መለዋወጫነት ሲያገለግሉ ይታያሉ፡፡ ይህን ሀሳብ ቫንሲና እንዲህ ሲሉ አብራርተውታል፡፡

> In various parts of Africa south of the Sahara and in New Guinea, where the languages are tonal, drum rhythms are used to transmit information. In some West African kingdoms drum slogans and poems recorded historical information. (Vansina,1985፡ 46-47)

እንደዚህ ሀሳብ ሁሉ የቤንች ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሚከውኑበት ወቅት ለማድመቂያነት የሚውሉ ባህላዊ ቁሶችን ይዘውና ባህላዊ ልብሶችን ለብሰው ይከውናሉ፡፡ እነዚህ የመከወኛ ቁሶች በሚያወጡት የተለያየ ድምጽ አማካኝነት የማህበረሰቡ አባላት መልዕክት ይለዋወጣሉ፡፡ ለምሳሌ:- ቲያርብ ከተመታ ትልቅ ሰው በአካባቢው መሞቱን የማህበረሰቡ አባላት ይረዳሉ፡፡ በመሆኑም የአንድ ማህበረሰብ መገለጫ የሆኑት ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ክዋኔዎች በሚጠኑበት ወቅት የመከወኛ ቁሶችን ማጥናት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የቤንች ማህበረሰቦች ትውን ጥበባትን በሚከውኑበት ወቅት የሚጠቀሙባቸውን የመከወኛ ቁሶች በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ተመድበው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 4.3.1 የዱብ መሣሪያ (የሙዚቃ መሳሪያ)

የአንድ ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሚከወኑበት ወቅት የተመልካች ተሳትፎንና የዱብ መሳሪያዎችን አጀብ ይሻሉ። እነዚህን የዱብ መሣሪያዎች የሚሰሯቸው ደግሞ በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ የዝቅተኛ ጎሳ አባል (ማኖ) በመባል የሚታወቁ ሰዎች ነው። እነዚህ ቁሶች በነዚህ ጎሳ አባላት ይሰሩ እንጂ ማንኛውም የማህበረሰቡ አባላት በደስታውም ሆነ በሀዘኑ ወቅት በመከወኛነት ይጠቀምባቸዋል። እነዚህ የዱብ መሳሪያዎች የማህበረሰቡን ታሪካዊ ማንነት፣ እምነት እና አመለካከት በመግለፅ በኩል ሰፊ ሚና አላቸው።

የቤንች ማህበረሰብ ትውን ጥበባትን በሚከውኑበት ወቅት የሚጠቀሙባቸው የዱብ መሳሪያዎች በእጅ የሚመቱ፣ በትንፋሽ የሚነፉ እና በእግር ላይ የሚታሰሩ ናቸው። እነዚህ የዱብ መሣሪያዎች በአጠቃቀማቸው መሰረት የእጅ፣ የእግር እና የትንፋሽ የዱብ መሳሪዎች ተብለው ከዚህ በታች እንደሚከተለው ተገልፀዋል።

#### 4.3.1.1 የእጅ የዱብ መሳሪያ

ከላይ እንደተገለጸው የአንድ ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሚከወኑበት ወቅት በራሳቸው ባህላዊ ቁሶች የሚታጀቡ ናቸው። የቤንች ማህበረሰብ ዶሮችን እና ዱቦችን በሚከውኑበት ወቅት በማጀቢያነት የሚጠቀሙባቸው የራሳቸው የሆኑ የዱብ መሳሪያዎች አሏቸው። ከነዚህ መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

ሀ. **ክራር፡-** ክራር የሚዘጋጀው ከደረቀ የዋንዛ እንጨት እና ከቆዳ ውጤት በሚገኙ ቀጫጭን ክር መሠል ፈትል ጅማቶች ነው። ይህ ክራር "ቪ" ቅርጽ ያለው ነው። ይህን ቁስ የሚሰሩት በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ የዝቅተኛ ጎሳ አባል ተደርገው የሚታሰቡ የማኖ ጎሣ አባል የሆኑ ሠዎች ናቸው። በማህበረ-ባህላዊ ዳራው ላይ እንደተለገፀው የእነዚህ ጎሣ አባል ሰዎች የሚተዳደሩት ቆዳ በመፋቅ እና የሸመና ሥራ በመስራት ነው።

የቤንች ማህበረሰብ ክራርን የሚጠቀሙበት የተለያዩ ትውን ጥበባትን በሚከውኑበት ወቅት እንደሆነ ተመልክቻለሁ። ከእነዚህ መካከል የወርደት፣ የቃልቻ ጭፈራ እና

የቃይጥ ወቅቶች ይጠቀሳሉ፡፡ በክዋኔው ላይ እንዳስተዋልሁት በቃልቻ ጭፈራ ወቅት ክራሩን የሚመቱት ባለቃልቻው ወይም ወይዘሶች ብቻ ናቸው፤ እንጅ ማንኛውም የእምነቱ ተከታይ የሆነ ሰው የቃልቻውን ክራር መምታትም ሆነ መንካት አይችልም፡፡ በወርዶት እና በየብ ወቅት ግን ማንኛውም የመጫወት ችሎታ ያለው ሰው ሁሉ መምታት ይችላል፡፡

በማህረሰቡ ዘንድ ክራር በሶስቱ የጭፈራ ወቅቶች የሚመታበት ምክንያት ከማድመቂያነቱ ባለፈ የማህበረሰቡን አባላት ድሮ ይጠቀሙበት የነበረውን ታሪካዊ የዱብ መሳሪያ ለማስታወስ ነው፡፡ እንዲሁም የማህበረሰቡ አባላት በአብዛኛው በዶር ወቅት የሚያንቀሳቅሱት የሰውነት ክፍል እግራቸው ነው፡፡ ይህም የመጣው ከክራር የዱብ መሳሪያ ድምጽ ስለሆነ የዶሩን እንቅስቃሴ ለማስጠበቅ ጭምር ነው፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ ከበደ አበሽ እንዲህ ሲል ተርኮልኛል፡፡ "ድሮ አባቶቻችን ይጠቀሙበት የነበረው የዱር መሳሪያ ክራር ነበር ከዚያ አንድ ሰው ቁጭ ብሎ እየመታ ሲጫወት እግሩንም አብሮ ከድምጹ ጋር እያንቀሳቀሰ ይጫወት ስለነበር የአሁኑ የእግራችን እንቅስቃሴ ከዚያ የመጣ ነው፡፡" (ደብረ ወርቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡ ስለዚህ የማህበረሰቡ አባላት ያለፈ ታሪኩን የሚገለፀው በዚህ የዱብ መሳሪያ ነው፡፡





ክራር　　　　　　　　　　ክራር ሲመታ

ምስል 4.9 ክራር የዱብ መሳሪያ

**ለ. ቲያርብ (ከበሮ)፡-** ይህ የዱብ መሣሪያ የሚሰራው ከደረቀ የዋንዛ እንጨት እና ከከብት ቆዳ ሲሆን የሚሰሩት ልክ እንደ ክራር ማኖ የሚባሉት የጎሣ አባላት ናቸው፡፡ ቲያርብ የሚሰሩት በሶስት አይነት መጠን ማለትም ትልቅ (ኢዝ)፣ መካከለኛ (ዲንታርስ) እና ትንሽ (ቲያርብ) በማድረግ ነው፡፡ እነዚህ ሦስት ቲያርቦች በአንድ አቅጣጫ ሰፊ የሆነ ክብ ቅርፅ ያላቸው ሲሆኑ በአንድ አቅጣጫ ደግሞ ጠባብ ሆኖ ክብ ቅርፅ አላቸው፡፡ ከምስል 4.10 ላይ መመልከት እንደሚቻለው ቲያርቦች ከመጠናቸው በተጨማሪ በቀለማቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ ማለትም ትንሿ እና መካከለኛው ቡኒ ቀለም ባለው ቆዳ የተሰሩ ሲሆን ትልቁ ደግሞ ነጭና ጥቁር ቀለም ባላቸው ቆዳዎች የተሠራ ነው፡፡

ቲያርቦች በዱብ መሣሪያነት የሚያገለግሉት ደግሞ በየብ ወቅት ብቻ እንደሆነ በመስክ ቆይታዬ ተመልክቻለሁ፡፡ ቀደም ብሎ በየብ ዶር ላይ እንደተገለፀው እነዚህ ቲያርቦች የሚመቱት ለሁሉም የማህበረሠብ አባል ሣይሆን ባለቃልቻ እና ሀብት ንብረት ያላቸው ሠዎች ሲሞት ነው፡፡ በየብ ወቅት ቲያርቦች የሚመቱበት ምክንያት ለሌሎች ሰዎች እዚያ አካባቢ ባለቃልቻ ወይም ሀብትና ንብረት ያለው ሠው መሞቱን እንዲያውቁ ለማድረግ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቲያርብ እየተመታ ሲጨፈር የሞተው ሰው መንፈስ ደስ ይለዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ ከድር ሸባ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡

> በባህላችን አንድ ባለቃልቻ ሞቶ ቲያርብ እየተመታ ካልተጨፈረ የወለዱት ልጅም ሆነ ዘመዶቹ በደንብ አልተለቀሠለትም ብለው ይከፋቸዋል፡፡[21] ከዚህ በተጨማሪ ቲያርብ የሚመታው የአካባቢው ሠዎች ትልቅ ሠው መሞቱን በቀላሉ ተረድተው ለማልቀስ እንዲመጡ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የመጡት ሠዎች ቲያርብ እየመቱ ካልጨፈሩ ለሞተው ሰው ከልባቸው አላዘኑም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ (ደብረ ወርቅ፣ ሚያዚያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም)

በየብ ወቅት ሶስቱ ቲያርቦች የሚመቱት በተመሣሣይ ጊዜ ቢሆንም በመጀመሪያ ጊዜ ግን የሚመታው ትልቁ ወይም መካከለኛው ነው፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ትንሿ ከዚያ መካከለኛው እያሉ ሲመቱ አስተውያለሁ፡፡ በሁለቱ ቲያርቦች መሀል ትንሿ ቲያርብ የምትመታው የሁለቱን ቲያርቦች ድምጽ ለማስማማት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እነዚህ ቲያርቦች ሲመቱ በሚያወጡት ድምጽ አማካኝነት የሚያስተላልፉት የራሳቸው የሆነ መልዕክት አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ትልቁ ቲያርብ በመጀመሪያ ከተመታ የማህበረሰቡ አባላት በአካባቢው ባለቃልቻ መሞቱን ይረዳሉ፡፡ መካከለኛው ቲያርብ በመጀመሪያ ከተመታ ደግሞ ሀብትና ንብረት ያለው ሰው መሞቱን በቀላሉ ይረዱበታል፡፡ ይህን ሀሳብ ከድር ሸባ እና ሌሎች ሰዎች አረጋገጠውልኛል (ደብረወርቅ፣ ሚያዝያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡ ቲያርቦች የሚመቷቸው ለየብ የመጡና የመምታት ችሎታ ያላቸው ሠዎች ናቸው፡፡

---

[21] የሚከፋቸውም ሀብትና ንብረት እያለው ከበሮ እየተመታ ካልተለቀሰ የሙት መንፈስ ይከፋል፡፡ ስለዚህ የእሱ ድርሻ ተሽጦ በከበሮ መጨፈርና ጦሱን ይዞ መሄድ አለበት ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡





በየብ ጊዜ ብቻ የሚመቱ ሶስቱ ቲያርቦዎች        ሶስቱ ቲያርቦች ሲመቱ

ምስል 4.10 ሶስቱ ቲያርቦች

### 4.3.1.2 የትንፋሽ የዱብ መሳሪያ

የቤንች ማህበረሰቦች በትውን ጥበባት ክዋኔ ወቅት ከሚጠቀሙባቸው የዱብ መሳሪያዎች መካከል የተወሰኑት የትንፋሽ የዱብ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የትንፋሽ የዱብ መሳሪያዎች በርከት ያሉ ሲሆኑ ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ሀ.ቶህ፡-** ይህ የዱብ መሣሪያ የሚዘጋጀው ከደረቀ የዋንዛ እንጨት ውስጡ በመቦርቦር ነው፡፡ ቁመቱም ከአንድ ስንዝር ከአንድ አጥቅ እስከ አንድ ክንድ ይሆናል፡፡ ቶሁን የሚሰሩትም ከኮምት ጎሳ አባል ውጭ የሆኑና የመስራት ችሎታ ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ የዚህ ጎሳ አባል የሆኑ ሰዎች ቶህ የማይሰሩበት ምክንያት የባለአባት (የባለቃልቻ) ጎሳ አባል ስለሆኑ መስራታቸው በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ እንደነውር ስለሚቆጠር ነው፡፡ የማህበረሰቡ አባላት ይህን የዱብ መሣሪያ የሚጠቀሙበት ለወርደት፣ ለየብ እና ለቃልቻ በሚጨፈርበት ወቅት እነደሆነ በክዋኔው ወቅት ተመልክቻለሁ፡፡ መሳሪያውን የሚነፉት ደግሞ ከማህበረሰቡ ውስጥ ተመርጠው በልምድ ችሎታ ያላቸው ወጣት ወንዶች ናቸው፡፡ ወጣት ወንዶች የሚነፉበት ምክንያት ቶሁ በሚነፋበት ወቅት ከፍተኛ የሆነ ትንፋሽ ስለሚያስፈልገው ነው፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ሻንቆ ጋኪናስ እንዲህ ሲሉ ነግረውኛል፡፡ “እኔ ድሮ

ወጣት እያለሁ ቶህ እነፋ ነበር አሁን ግን ትቻለሁ ምክንያቱም ሲነፋ ብዙ ትንፋሽ ስለሚጠይቅ እሱን ለመንፋት አቅም እና ጉልበት የለኝም በዚህ የተነሳ ትቼዋለሁ፡፡" (ደብረወርቅ፣ ግንቦት 5 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡ ከዚህ የምንረዳው በማህበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ጉልበት ያላቸው ወንዶች ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ መሳሪያዎችን እነሱ እንዲነፉ መደረጉን ነው፡፡

"በባህላችን በወርደት እና በየብ ወቅት ሁለት ቶሆች በአንድ ጊዜ ሲነፉ የተለያየ ድምፅ ያወጣሉ በዚህ ጊዜ ድምጹን በመለየት እነማን እዚያ ቦታ ላይ እንዳሉ በቀላሉ ማወቅ ይቻላል፡፡" አዳሙ ሀንቲያብ (ጊሊት ቀበሌ፣ ግንቦት 6 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡ ከዚህ ሀሳብ መረዳት እንደምንችለው የማህበረሰቡ አባላት በወርደት እና በየብ ወቅት በሚጠቀሙባቸው የመከወኛ ቁሶች አማካይነት መልዕክት እንደሚለዋወጡባቸው ነው፡፡



ምስል 4.11 ቶህ ሲነፋ

**ለ. ወሽ፡-** ይህ የዱብ ማሪያ የሚዘጋጀው ቀርቅሀ ከሚባል ሸንበቆ መሣይ እንጨት ሲሆን የሚያዘጋጁት የባለቃልቻው ወይዘሮች ናቸው፡፡ ቁመቱም ከአንድ ክንድ እስከ አንድ ክንድ ከስንዝር እንደሚሆን አቶ ሻንቆ ጋኪናስ (አማን፣ ሚያዚያ 25 ቀን 2003

ዓ.ም) ገልፀውልኛል። ይህን የዱብ መሳሪያ የሚጠቀሙበት አንድ ባለቃልቻ ሞቶ ሌላ ባለቃልቻ በሚተካበት ወይም በሚነግስበት ወቅት ነው። በክብረ በዓሉ ወቅት ወሹን የሚነፉት ወይዘሶች ቃልቻው የማይፈልገውን ምግብ የማይበሉና ንፁህ[22] የሆኑት ተመርጠው ነው። መስክ በነበርሁበት ወቅት ወሽ የሚባለውን የዱብ መሳሪያ ማየትም ሆነ ፎቶ ግራፍ ማንሳት አልቻልሁም። ምክንያቱም የእምነቱ ተከታይ ያልሆነ ሰው ወሹን ከአየው እምነታችን ይረክሳል ብለው ስለሚያስቡ አልተፈቀደልኝም።

**ሐ. ፊርግን፡-** ይህ የትንፋሽ የዱብ መሣሪያ የሚዘጋጅው ከሸንበቆ ሲሆን ቁመቱ ከአንድ ስንዝር እስከ አንድ ክንድ ይሆናል። የሚያዘጋጁትም የማንኛውም የጎሳ አባል የሆኑና በአብዛኛው ወጣት ወንዶች ናቸው።

በትውን ጥበባቱ ክዋኔ እንደተመለከትሁት የማህበረሰቡ አባላት ይህን የዱብ መሣሪያ የሚጠቀሙበት በወርደት፣ በየብ እና በቃይጥ ወቅት ነው። በእነዚህ ወቅቶች በአንድ ጊዜ ከአንድ እስከ ሰባት የሆኑ ፊርግኖች ሊነፉ ይችላሉ። በአንድ ጊዜ ሰባቱን በሚነፉበት ወቅት ሰባት ሰዎች እንደ ፊርግኑ የቁመት መጠን ሠዎችም በቁመት ተከፋፍለው እየተቀባበሉ ሊነፉት ይችላሉ ወይም አንድ ሠው ሰባቱን በአንድ ላይ አስሮ ሊነፋው ይችላል።



**ምስል 4.12 ፊርግን**

---

[22] ንፁህ ማለት በህብረተሰቡ ዘንድ ቦርዴ የሚባል መጠጥ አለ ያንን መጠጥ ያልጠጡ፣ የበግ ሥጋና ጎመን ያልበሉ ማለት ነው።

#### 4.3.1.3 የእግር የዱብ መሳሪያ

የቤንች ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሚከውኑበት ወቅት ከሚጠቀሙባቸው የዱብ መሳሪያዎች መካከል አንዱ በእግር የሚታሰር ሲሆን ይህም ከላይ እንደተገለፀው በማህበረሰቡ ቋንቋ ቶሪ በመባል ይታወቃል፡፡ ቶሪ የሚዘጋጀው ከቆርቆሮ ወይም ከቀለህ እና ከወፍራም ክር ነው፡፡ የሚሰሩትም የማኖ ጎሳ አባል የሆኑት ሰዎች ናቸው፡፡ ከዚህ በፊት እንደተገለጸው እነዚህ ሰዎች ዋና መተዳደሪያቸው ቆዳ በመፋቅ እና የሸመና ስራ በመስራት ቢሆንም የሚተዳደሩት ጎን ለጎን ግን እነዚህን የዱብ መሳሪያዎች ይሰራሉ፡፡

የማህበረሰቡ አባላት ቶሪ የሚጠቀሙት በወርደት፣ በየብና በቃልቻ ጭፈራ ወቅት ነው፡፡ ይህን የዱብ መሣሪያ በእግራቸው ላይ የሚያስሩት በቃልቻ እና በወርደት ጭፈራ ወቅት የባለአባት ጎሣ አባል የሆኑና ወጣት ያላገቡ ሴቶች ናቸው፡፡ ወጣት እና ያላገቡ ሴቶች ብቻ የሚያስሩበትን ምክንያት ከድር ሸባ እንዲህ ሲል አስረድቶኛል፡፡ "በባህላችን ቶሪ በእግራቸው ላይ የሚያስሩት የባለአባት ጎሳ አባል የሆኑና ያላገቡ ወጣት ሴቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱም በአብዛኛው በጭፈራ ወቅት የሚሳተፉት እነሱ ስለሆኑ የማን ጎሳ አባል መሆናቸው እንዲታወቅና ያላገቡ መሆናቸውን ለሌሎች ሰዎች ለመግለጽ ነው፡፡" (ደብረ ወርቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡ በየብ ወቅት ደግሞ ማንኛውም የማህበረሰቡ አባላት የሆኑና ሀዘንተኛ ሴቶች እንደሚያስሩት ተመልክቻለሁ፡፡ እነሱ የሚያስሩበት ምክንያት ሀዘንተኛ መሆናቸውን ለሌሎች ለመግለፅ ነው፡፡

ይህን የዱብን መሳሪያ በእግራቸው ላይ አስረው በሚጨፍሩበት ወቅት ‹‹ጪጪ›› የሚል ድምጽ እያሰሙ በማድመቂያነት ይጠቀሙበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሚጨፍሩበት ወቅት ዱቡና ዶሩ አብረው እንዲሄዱ በማድረግ ይገለገሉበታል፡፡




ምስል 4.13 ቶሪ (ቃጭል)

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰቦች ትውን ጥበባት በሚከውኑበት ወቅት በሚጠቀሙባቸው የዱብ መሳሪያዎች አማካይነት ከማድመቂያነታቸው ባለፈ የማህበረሰቡን ማህበራዊ ደረጃ፣ ታሪካዊ አመጣጥ፣ እምነት፣ ፍላጎት፣ አመለካከትና እሴት ይገልጹባቸዋል፤ መልዕክት ይለዋወጡባቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ የአንዱን ጎሳ አባል ከሌላው ለመለያነት ይጠቀሙባቸዋል።

## 4.3.2. ለማድመቂያነት የሚውሉ ቁሶች

የቤንች ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በሚከውኑበት ወቅት ከዋኞች በርከት ያሉ ቁሶችን በእጃቸው ይዘው፣ በወገባቸው አስረውና ከወገብ በላይ ለብሰው ይከውናሉ። እነዚህ ቁሶች እንደ ሌሎች የዱብ መሳሪያዎች ድምጽ አይኑራቸው እንጂ ዱቡን እና ዶሩን በማድመቅ በኩል ከፍተኛ የሆነ ድርሻ አላቸው። ከዚህ በተጨማሪ ቁሶቹ የማህበረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥና ማህበራዊ ደረጃን በመግለጽ በኩል ሰፊ ድርሻ አላቸው።

ይህ ጥናት የቤንችን ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት ክዋኔዎች በሚያጠናበት ወቅት እግረ መንገዱን የሚጠቀሙበትን ቁስ ቢመለከትም ሙሉ በሙሉ ግን ሁሉንም የማህበረሰቡን

አልባሳት አይመለከትም፡፡ ማለትም የሚመለከታቸው የማህበረሰቡ አባላት ትውን ጥበባቱን በሚከውኑበት ወቅት ብቻ የሚጠቀሙበትን ቁሶች ብቻ ነው የሚያካትተው፡፡ እንጂ በማንኛውም ቀን የሚለብሱትንና የሚጠቀሙበትን አያካትትም፡፡ በትውን ጥበባት ክዋኔ ወቅቶች የማህበረሰቡ አባላት ለማድመቂያነት ከሚጠቀሙባቸው ቁሶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ሀ. ማይት (ጦር)፡-** ማይት የሚሰራው ከደረቀ ጥቁር እንጨትና ጫፉ ከሾለ ብረት ነው፡፡ ይህን የሚሰሩትም ማንኛውም የማህበረሰቡ አባላት የሆኑ ወጣት ወንዶች ናቸው፡፡ የማህበረሰቡ አባላት የሆኑት ወንዶች ማይትን በማንኛውም ወቅት ከእጃቸው የማይለዩት ቢሆንም ይበልጥ ግን የሚጠቀሙበት በየብና በወርደት ወቅት ነው፡፡ በየብ ክዋኔ ወቅት እንደተመለከትሁት በአብዛኛው የሚይዙት የእድሜ ባለፀጎች ናቸው፡፡ በዚህ ወቅት ጦሩን የሚይዙት ከማድመቂያነቱ በተጨማሪ የሟቹን እና የእነሱን ጀግንነት ለመግለጽ ነው፡፡ ይህን ሀሳብ አቶ ኩጁ መንግስቴ እንዲህ በማለት ገልፀውልኛል፡፡

> በባህላችን ዘንድ አንድ ሰው ሲሞትና ወደ የብ ቤት ስንሄድ ማይት ይዘን ነው የምንሄደው፡፡ አሁን[23] ማይት የምንይዝበት ምክንያት ጣሊያንን ድል ያደረግነው በጦር ተዋግተን ስለሆነ ያንን ጀግንነት ለማስታወስ ጭምር ነው፡፡ እንጂ ድሮም[24] በአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግስት ጀምሮ በየብ ጊዜ ስንጨፍር የራሳችንና የሟቹን ጀግንነት ለመግለፅ እንይዝ ነበር፡፡ (ኩብ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም)

የማህበረሰቡ አባላት ወደ የብ ሲሄዱ ከያዙት የማይት ጫፉ ላይ እርጥብ ሳር አስረው ሲሄዱ ተመልክቻለሁ፡፡ ይህን ሳር የሚያስሩበት ምክንያት መንገድ ላይ የሚያገኛቸው ማንኛውም የማህበረሰቡ አስተዳዳሪ በሰላም ወደ የብ ቤት መሄዳቸውን ተረድቶ ምንም ዓይነት ጥያቄ እንዳይጠይቃቸው ነው፡፡ ሳር በማህበረሰቡ አባላት ዘንድ የሰላም ተምሳሌት ተደርጎ እንደሚወሰድ አቶ ሻንቆ ጋኪናስ እና ሌሎች ሰዎች አረጋግጠውልኛል (አማን፣ ሚያዝያ 25 ቀን 2003ዓ.ም)፡፡

---

[23] አሁን የተባለው ከጣልያን ጦርነት በኋላ ያለውን ነው፡፡
[24] ድሮም የተባለው ከጣልያን ጦርነት በፊት ለማለት ነው፡፡

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የማህበረሰቡ አባላት በወርደት ጊዜ በሚጨፍሩበት ወቅት ማይት በመያዝ ጥንድ ጥንድ ሆነው ወጣት ሴቶችና ወንዶች ይጨፍራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ ወንድ የሚወዳት ሴት በሚጨፈርበት አካባቢ ካለች የእሱ መሆኗን ለመግለጽ ማይቱን እየሰጠ አብራው እንድትጨፍር ያደርጋታል፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ ከድር ሽባ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡

> በባህላችን በወርደት ጭፈራ ጊዜ ወጣት ወንዶች ማይት የሚይዙበት ምክንያት አንደኛ በጭፈራ ወቅት የጎሳዎች ግጭት ስላለ እራሳቸውን ከጠላት ለመከላከል፤ ሁለተኛው በጭፈራ ወቅት የሚወዷትን ልጃገረድ መርጠው ጦር እየሰጡ አብረዋት ለመጨፈር እና ልጅቷ የእነሱ መሆኗን ለሌሎች ሰዎች ለመግለጽ ነው፡፡ (ደብረ ወርቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም)

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ በተለያዩ የጭፈራ ወቅቶች ማይት የሚይዙበት ምክንያት ከማድመቂያነቱ ባለፈ የራሳቸውን ጀግንነት እና ፍላጎት ለሌሎች ሰዎች ለመግለፅ ወይም ለማሳወቅ ነው፡፡

**ለ. ጃስ (ጋሻ)፡-** ይህ ቁስ በየብ ጭፈራ ክዋኔ ወቅት እንደተመለከትሁት የቤንች ማህበረሰብ ለማድመቂያነት ከሚጠቀሙባቸው ቁሶች አንዱ ነው፡፡ ይህ ቁስ የሚቹን ጀግንነት እና ማንነት በመግለጽ በኩል ሰፊ ድርሻ አለው፡፡የማህበረሰቡ አባላት አንድ ባለቃልቻ ወይም ባለሀብት ሰው ሲሞት ሞቅ ያለ ጭፈራ ጃስ እየተመታ ይጨፈራል፡፡ ጃሱን የሚመታው የልጅ ባል ካለ እሱ ከሌለ ደግሞ የቅርብ ዘመድ ነው፡፡ መስክ በነበርሁበት ወቅት ግን በየቡ ላይ የሞተው ሰው የልጅ ባል እግሩ እስኪደማ እየመታ ከጨፋሪዎች መሐል ሲሽከረከር አይቸዋለሁ፡፡ "እግሩ እስከሚደማ የሚደበድበውም የሞተውን ሰው ጀግንነት እና ጨፋሪው የራሱን ማንነት ለመግለጽ ነው፡፡" በላይ አዲሱ ገልፀውልኛል፡፡ (ሚያህ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡



**ምስል 4.14 ጻስ**

በቤንች ማህበረሰብ በአንድ ሰው የብ ላይ ጻስ እየተመታና ካልተጨፈረ የሞተው ሰው ጀግና አልነበረም ወይም የልጅ ባልና ዘመዶቹ አይወዱትም ማለት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

ሐ. **ጠብመንጃ፡-** የቤንች ማህበረሰብ በወርደት ወቅት ለመከወኛ ከሚጠቀሙባቸው ቁሶች መካከል አንዱ ጠብመንጃ ሲሆን በወርደት ወቅት ይህን ቁስ የሚጠቀሙት የሙሽሪት ዘመዶች ናቸው፡፡ ነገር ግን የማህበረሰቡ አባላት ሙሽሪት ዘመዳቸው ስለሆነች ብቻ በወርደቱ ላይ ተገኝተው በራሳቸው ፈቃድ መተኮስ አይችሉም፡፡ በመጀመሪያ ወደ ወርደቱ ከመሄዳቸው አስቀድመው ከባለቃልቻው ከዘመዳቸው ቤት ወርደት እንዳለ እና ምን ያህል ጥይት መተኮስ እንደሚፈልጉ ያስፈቅዳሉ፡፡ ምክንያቱም በጥናቱ ማህበረ-ባህላዊ ዳራ ላይ እንደተገለፀው በአብዛኛው ማህበረሰቡ የሚተዳደረው በቃልቻው ህግ መሰረት ነው፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው ሳይፈቀድለት ጥይት ከተኮሰ በህጉ መሰረት እስከ ሞት ድረስ ሊቀጣ ይችላል፡፡

አንድ የሙሽሪት ዘመድ በወርደቱ ላይ ተገኝቶ ከሁለት እስከ አምስት ጥይት ሲተኮስ አስተውያለሁ፡፡ ይህ ያህል ጥይት የሚተኩስበት ምክንያት ወርደቱን ከማድመቂያነት በተጨማሪ ለማህበረሰቡ የሚፈጥረው የትስስር መንፈስ እንዳለ ከድር ሸባ እንዲህ ሲሉ አብራርተውልኛል፡፡

> የአንዲት ሙሽራ ዘመድ በወርደቷ ላይ ተገኝቶ ጥይት ካልተኮሰላት ዘመዴ ጥይት ያልተኮሰልኝ እኮ ስለማይወደኝ ነው ብላ ታስባለች ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች የሚያገቡት ልጃገረዶች በእሷ ወርደት ላይ በብዛት ጥይት የተኮሰውን ሰው ጎሣ በመለየት ከእነሱ ጎሳ ነው የምናገባው፡፡ ምክንያቱም በዘመዳቸው ወርደት እንኳን መጥተው ብዙ ጥይት የተኮሱ እነሱ ናቸው፡፡ ስለዚህ እርስ በርሳቸው ይዋደዳሉ ማለት ነው ብለው እንዲወስኑ ያደርጋቸዋል፡፡ (ደብረ ወርቅ፣ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም)

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ ጠብመንጃን በወርደት ወቅት የሚጠቀመው የራሱን የትብብር መንፈስ ለማበረታታትን እና ለመፍጠር ነው፡፡

### 4.3.3 አልባሳት

ሀ. **እጨጭ**፡- ይህ ልብስ ለባለቃልቻ በሚጨፈርበት ወቅት ጭፈራውን ለማድመቂያነት ከሚውሉት ቁሶች መካከል አንዱ እንደሆነ ተመልክቻለሁ፡፡ ልብሱ የሚዘጋጀው ከዱር ውስጥ ከሚቆረጥ ሀረግ ነው፡፡ ከምስል 4.8 መመልከት እንደሚቻለው ይህ ሀረግ የሚለበሰው ከወገብ በላይ ባለው የኂለኛው የሰውነት ክፍል ሲሆን የሚለብሱት የእምነቱ ተከታይ የሆኑ ወንዶች ናቸው፡፡ በዚህ ወቅት ይህን ሀረግ የሚለብሱበትን ምክንያት ከበደ አበሽ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡ "እጨጭ በቃልቻ ጭፈራ ወቅት የሚለበሰው ጨፋሪዎች በጣም ጎበዝ ጨፋሪ ነኝ ለማለት እና እራሳቸውን ከሌላ ነገር ይጠብቀናል[25] ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡" (ደብረወርቅ፣ ሚያዝያ 24 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡

በመሆኑም ይህ ልብስ የከዋኞችን ጀግንነትና ችሎታ የማህበረሰቡን ታሪካዊ የአለባበስ ሥርዓት ይገልፃል፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ኩጁ መንግስቴ እንዲህ ሲሉ አብራርተውልኛል፡፡

> በማህበረሰባችን ድሮ ኮት የሚባል ነገር የለም ነበር፡፡ ከወገባችን በታች የምንለብሰው ቀይ የኮባ ቅጠል ወይም የከብት ቆዳ ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ የእምነቱ

---

[25] ይጠብቀናል የሚሉት ጎበዝ ጨፋሪ ከሆኑ ቡዳ (ቃምጨት) እንዳይበላቸው ነው፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ ዘንድ ጎበዝ የሆነ ጨፋሪ ሲጨፍር ቃምጨት ካየው ይበላዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ ይህ ልብስ መለበሱ ሲጨፍሩ እየተንቀሳቀሰ የቃምጨቱን አይን ይከልላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አረንጓዴ ቀለም ያለው ነገር ሁሉ ስለሚያምር የቃምጨቱ ዓይን ከእጨጭ ላይ ያርፋል በማለት ነው፡፡ ቃምጨት ማለት ክፉ መንፈስ ያደረባቸው እና በቀላሉ አይተው በሰዎች ላይ ህመም ይፈጥራሉ የሚባሉ ሰዎች ናቸው፡፡

> ተከታዮች ለቃልቻው መስዋዕት በሚቀርቡበት ወቅት ለጭፈራ ሲመጡ ይህን እጨጭ ይለብሱ ነበር አሁንም ያንን ለማስታወስ ይለበሳል፡፡ (ኮብ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 18 ቀን 2003 ዓ.ም)

**ለ. ማይዱሽ፡-** ይህ ልብስ በወርደት ጭፈራ ወቅት ለማድመቂያነት ከሚውሉት ቁሶች መካከል አንዱ ሲሆን የሚሰራው ከሣር ወይም ከእርጥብ የኮባ ቅጠል በቀጭኑ በመተልተል ነው፡፡ ይህን ልብስ የሚለብሱት በማህበረሰቡ ዘንድ የዝቅተኛ ጎሳ አባል በመባል የሚታወቁ ወንዶች ናቸው፡፡ ከዚህ በታች ካለው ምስል እንደሚታየው እነዚህ ወንዶች ይህን ልብስ የሚለብሱት በጂላቸው በኩል ከትክሻቸው ጀምረው እስከ ወገባቸው ድረስ ነው፡፡ ይህ ልብስ በማህበረሰቡ ዘንድ ልክ እንደ እጨጭ ተመሳሳይ የሆነ መልዕክት አለው፡፡ ይህን ሀሳብ በተመለከተ አቶ ኩንዲሳ ፈርኪ እንዲህ ሲሉ ገልፀውልኛል፡፡

> በባህላችን ማይዱሽ የሚለበሰው በወርደት ጭፈራ ወቅት ነው፡፡ ይህን ልብስ የሚለብሱትም ከዝቅተኛ ጎሳ አባል የሚመጡ ወንዶች ናቸው፡፡ እነዚህ ወንዶች በድሮ ጊዜ ልብስ በሌለበት ዝናብ ሲመጣ ከእነ ኮፍያው ይህን ማይዱሽ ስለሚሞቃቸው ይለብሱት ነበር፡፡ (ቂጤ፣ ሚያዝያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም)




ምስል 4.15 ማይትና ማይዱሽ

ከላይ እንደተገለጸው የማህበረሰቡ አባላት በወርደት ወቅት ማይዱሽ የሚለብሱት ከማድመቂያነት ባለፈ ያለፈ ታሪካቸውን እንደ ባህል በመቁጠር ለመግለጽ ነው፡፡ ከዚህ

በተጨማሪም አንድ ሰው በወርደት ወቅት ማይዱሽ ለብሶ ለመጨፈር ከመጣ የማህበረሰቡ አባላት ይህ ሰው ጎበዝ ጨፋሪ መሆኑን ለሌሎች ሰዎች ለመግለጽ ነው፡፡

**ሐ. የአሞራ ክንፍ፡-** ይህ ልብስ የቤንች ማህበረሰብ በቃልቻ ጭፈራ ወቅት ለማድመቂያነት ከሚጠቀሙባቸው ቁሶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህን የአሞራ ክንፍ በቃልቻ ጭፈራ ወቅት የሚለብሱት የእምነቱ ተከታይ የሆኑ ወጣት ወንዶች ናቸው፡፡ ከዚህ በታች ካለው ምስል ማየት እንደሚቻለው አለባበሱ ልክ እንደ ኮፍያ ከራሳቸው ላይ በመድፋትና እግሩን ደግሞ ወደ ታች በአንገታቸው በማውረድ ነው፡፡ እንዲህ አድርገው የሚያዘጋጁት አሞራውን ወዲያው እንደገደሉት ምንም ቆዳውን ሳይነኩ ከሆዱ ውስጥ ያለውን ነገር በሙሉ በአንገቱ በኩል በማውጣት እና የኮፍያ ቅርጽ አስይዘው በማደረቅ ነው፡፡ የቃልቻ እምነት ተከታዮች ይህን የሚለብሱበት ምክንያት እምነታቸው ምን ያህል እረድቷቸው የሚበር አሞራ ከሰማይ እንዳወረዱ ለመግለፅ ነው፡፡ አቶ አበሽ ቱዮ እና ሌሎች ሰዎች ይህን ሀሳብ እንዲህ ሲሉ አረጋግጠውልኛል፡፡ "በቃልቻ ጭፈራ ወቅት የአሞራ ክንፍ የሚያደርገው ሰው የራሱን ጀግንነት ለመግለፅና እምነቱን ለመስበክ ነው፡፡" (ሚያህ ቀበሌ፣ ሚያዝያ 19 ቀን 2003 ዓ.ም)፡፡




**ምስል 4.16 እጨጭና የአሞራ ክንፍ**

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባትን በሚከውኑባቸው አጋጣሚዎች የሚጠቀሙባቸው የመከወኛ ቁሶች ከማድመቂያነታቸው በተጨማሪ

የማህበረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥ፣ ማንነት፣ አመለካከት እና እምነት በመግለፅ በኩል ከፍተኛ የሆነ ድርሻ እንዳላቸው ጥናቱ አረጋግጧል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት በቤንች ማህበረሰብ ውስጥ በአብዛኛው የሚታዩ የትውን ጥበባት ክዋኔዎች ከማህበረ-ባህላዊ እና ከሃማኖታዊ አውዶች ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ እነዚህ ትውን ጥበባት እንደሚከወኑበት አጋጣሚዎች ከዋኞች በእድሜና በጾታ የተከፋፈሉ መሆናቸውን ጥናታዊ ፅሑፉ ያስረዳል፡፡

ጥናቱ በማህበረሰቡ ዘንድ በወርደት፣ በየብና በቃይጥ ከሚከወኑት ትውን ጥበባት መካከል በማህበረሰቡ ቋንቋ ዶርና ዱብ ላይ ያተኮረ ሲሆን በእነዚህ ትውን ጥበባት ቅርጾች አማካይነት የማህበረሰቡ አባላት ስሜታቸውን፣ እምነታቸውን፣ ፍላጎታቸውንና አመለካከታቸውን እንደሚገልፁ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡ እንዲሁም እነዚህ ትውን ጥበባት መከወናቸው በማህበረሰቡ ዘንድ የትስስር መንፈስን በመፍጠር በኩል ሰፊ ድርሻ እንዳላቸው ጥናቱ ያስረዳል፡፡ ለምሳሌ፡- በወርደት ወቅት ዶር መከወኑ በማህበረሰቡ ዘንድ የትዳር አጋር ማግኛ በመሆን ያገለግላል፡፡ በየብ ወቅት በሚከወኑ ዶሮች ማህበረሰቡ ሀዘኑን እንደሚረሳበት፣ የሙት መንፈስ እንደሚረጋጋበት፣ በቃልቻ ክብረ በዓል በሚከወኑ ዶሮች አማካይነት የእምነቱ ተከታዮች አምልኮታቸውን እንደሚፈፅሙበት፣ በቃይጥ ወቅት በሚዜሙት ዱቦች ደግሞ የማህበረሰቡ አባላት የአንድነት መንፈሳቸውን እንደሚያጠናክሩበት በጥናቱ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል በትውን ጥበባቱ ክዋኔዎች ወቅት የሚጠቀሙባቸው የመከወኛ ቁሶች ክዋኔዎችን እንደሚያደምቁና ከዚያ በተጨማሪ የማህበረሰቡን ታሪካዊ አልባሳትና የዱብ መሳሪያዎች እንደሚገልጹ በጥናት ወረቀቱ ውስጥ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ይሁንና እንደ እጨጭ እና ማይዱሽ የመሳሰሉት አልባሳት የማህበረሰቡን ጥንታዊ አልባሳት የሚገልፁ ፤ጃስና ማይት የከዋኙን እና የሚቹን ጀግንነትና የመጨፈር ችሎታ የሚገልጹ ሲሆኑ ክራር እና ቶሪ የመሳሰሉት የዱብ መሳሪያዎች ደግሞ የማህበረሰቡን ጥንታዊ የዱብ መሳሪያዎች በመግለፅ በኩል ሰፊ የሆነ ድርሻ እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በጥናቱ ውስጥ ያሉትን የዱብ ግጥሞች ስንመለከት ደግሞ የማህበረሰቡን እምነት፣ አመለካከት እና ጎሳ ከማሞገስ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የትውን ጥበባቱ ከዋኞችም ከወቅቱ ጋር አያይዘው የሚያዜሙት ዱብ እምነታቸውን የሚለምኑበት፣ ሙሽሪትን

የሚያሞጋግሱበት፣ በቃይጥ ወቅት የደቦ ሰራተኞችን የሚያበረታታቱበትና የትስስር መንፈስን የሚፈጥሩበት መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

ከዋኞች በእድሜ፣ በፆታ እና በሀይማኖት የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ከዋኞች ሙያውን የሚለምዱት ከአካባቢያቸው እንደሆነ ጥናቱ ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ የቤንች ማህበረሰብ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እንደሚከወኑባቸው አውዶች የተለያዩ ከዋኞችና ታዳሚዎች እንዳሏቸው፤ትውን ጥበባቱ በመከወናቸው በማህበረሠቡ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ትስስር እንደሚፈጥሩና ማህበረሰቡ ታሪኩን፣ እምነቱንና እሴቱን እንደሚገልፅባቸው በጥናት ወረቀቱ ውስጥ ተገልጿል፡፡

## ጥቅስማ (Reference)


Bauman, Richard. *Genre in Folklore, Cultural Performance and Popular Entertainment.* A communication centered handbook. Oxford: Oxford University Press. 1991.

Bauman, Richard. *"verbal Art as performance".* American anthropologist, New Series, vol.77, no.2. (jun., 1975) PP. 290-311. 1975. Publisher Contact information may be obtained at http://www Jstor.org/journals/stable url/anthro.html.

Ben-Amos ,Dan,. *"Context" in Context. Western Folklore.* 1993. Retrieved on Wed Apr 11 2011 from http://www.jstor.org., Vol. 52, No. 2/4.

Borland, Katherine. "Documenting the Fieldwork Project." *The Emergence of Folklore Everyday life.* George H.Schoemaker. *(ed.)* Indiana University; Trickster press,1990.

Bruno, Nettl. *"Folk Music."* Microsoft® Encarta®. 2009. Redmond, WA: Microsoft Corporation, 2008.

Buckland ,Theresa. "Definitions *of Folk Dance".* Journal of the Folklore Institute Vol. 15, No. 3 (Sep. - Dec., 1978) pp. 263-265. 1983. English Folk Dance + Song Society Retrieved jun 18, 2011 from http://www.jstor.org/stable/4522127.

Dorson, R. (Ed). *Folklore and Folk Life: An Introduction.* Chicago: The University of Chicago Press. 1972.

Dundes, Alan. *"Folkloristic in the Twenty-First Century:* (AFS Invited Presidential Plenary Address, 2004)". 2005. Journal of American Folklore,118

Ezra, Abate. *Ethiopian Folklore Text Book.* Yared Music School,1996

Finnegan, Ruth. Oral poetry ;Its nature, significance and social context. Cambridge: Cambridge University Press, 1977.

---------------- *Oraltrature in Africa.* Oxford; clarenden press,1970.

----------------*Oral traditions and the verbal arts.* USA and Canada; Routledge is an International Thomson Publishing Company, 1992

*Folk-dance. Dictionary Definition.* 2011. Retrieved May 26, 2011 from http://encarta.msn.com/dictionary_1861690592/folk_dance.html

*Folk -dance.* The Free Dictionary, Farlex, Inc. 2011. Retrieved May 21, 2011, from http://www.thefreedictionary.com/folk+dance

*Folk -music. Macmillan Dictionary.* 2009-2011.Macmillan Publishers Limited. Retrieved May 21, 2011, from http://www.macmillandictionary.com/dictionary/british/folk-music.

Kim Ruehl. *Folk Music.* About.Com Guide. 2011. Retrieved May 25, 2011 from http://folkmusic.about.com/od/glossary/g/FolkMusic.html

Largey, Michael. "Ethnomusicology and Musical Collecting Techniques." *The Emergence of Folklore Everyday life.* George H.Schoemaker. (*ed.).* Indiana University: Trickster Press, 1990.

Matthews, Gail. "Movement and Dance." *The Emergence of Folklore Everyday life. H.Schoemaker. (ed) Indiana* University: Trickster Press,1990.

Martin, Gyorgy. *"Dance Types in Ethiopia".* Journal of the International Folk Music Council.vol.19 PP. 23-27. 1967. International council for traditional music, http://www Jstor.org/stable/ 942181.

Redmond, *"Performing Arts."* Microsoft® Encarta®. 2009. WA: Microsoft Corporation, 2008.

Rosenberg, Neil V. *Folklore an Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art.* Thomas A. Green. (Ed) United States of America; California, 1997.

Sims, Martha and, Martine, Stephens. *Living folklore: An Introduction to the Study of People and Their Traditions.* United States of America; Utah State University Press. 1963.

Suzanne,Youngerman. *Folk Dance.* Microsoft® Encarta®. 2009. Redmond, WA: Microsoft Corporation, 2008.

Timkehet Teffera. *Control, Influence and violence through music: The role of political songs during the Ethiopian revolution (1974-1991).* 2009. ICTIM meeting in Hamburg.

*Tripod.* PageInsider.com, 2009-2011. 1994. Retrieved April 13, 2011 from http://mfolkie.tripod.com

Turner, Rory & Phillip H. McArthur. "Cultural Performance; Public Display Events and Festival." *The Emergence of Folklore Everyday life. edited by George H.Schoemaker. Indiana* University: Trickster Press,1990.

Vadasy, Tibor. *"Ethiopia Folkdance".* Journal of Ethiopian study. 1970. Addis Ababa university, V. 8 n.1, P. 119-146.

___________. *"Ethiopian folk dance II Tiger and Gurage."* Journal of Ethiopian study. 1971. Addis Ababa University, V. 9 n.2, P. 191-217.

___________. *"Ethiopia folk dance III Wollo and Gala."* Journal of Ethiopia study. 1973. Addis Ababa University, V. 11 n.1, P. 213-131.

ማንያለው አባተ፣ "የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሑፍ ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ 1999 ።

ማቴዎስ ከበደ፣ "የሸዋ ኦሮሞ ጥቂት የባህል ሙዚቃና የሙዚቃ መሣሪያዎቻቸው"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ያሬድ ት/ቤት፣1994።

ሰለሞን ስህሌ፣ "ትውፊታዊ ድራማ በሸካቾ ብሔረሰብ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በትያትር ጥበባት ክፍል ለባችለር አርት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣1980።

ሳሮን ጌትየ፣ "ጌይ ኢሱዑ" የአደሬ ባህላዊ ሙዚቃ"። አ.አ.ዩ፣ ያሬድ ት/ቤት፣ 1994።

ነፃነት ሙሉ ጌታ፣ "የአማራ ባህላዊ ውዝዋዜ ጥንትና ዛሬ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ያሬድ ት/ቤት፣ 1994።

አሸናፊ ሙሉጌታ፣ "በጅጅጋ አካባቢ የሚኖሩ የሱማሌ ብሔረሰብ ባህላዊ አናናራቸውናሙዚቃቸው"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ያሬድ ት/ቤት፣ 1994።

አበበ ኃይሉ፣ "የወዳጃ ትውፊት በሐረርጌ ኦሮሞ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለትያትር ጥበባት ክፍል ለባችለር አርት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሁፍ፣1980።

ኩንዲሳ ፊርኢ፣ "የቤንች ብሔረሰብ ታሪክ እና ባህል ጥናት" ሚዛን ተፈሪ፣ በቤንች ማጂ ዞን ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ የተዘጋጀ፣ ያልታተመ፣1988።

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦችና ፕሮፋይል፣የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦችና ቋንቋና ታሪክ ቅርስ ጥናት ተቋም፣ ሀዋሳ፣ ፍቅረሰላም ማተሚያ ቤት፣ 2001።

ይርጋሸዋ ደብሬ፣ "የአላባ ብሔረሰብ ባህላዊ አናናራቸውና ሙዚቃቸው"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ያሬድት/ቤት፣ 1994።

ገዛኸን አሠፋ፣ "የከምባታ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሑፍ ክፍለ ትምህርት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፣ 1999።

ፈቃደ አዘዘ፣ የሥነ ቃል መምሪያ:: አዲስ አበባ፣ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጉልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፣ 1991::

# አባሪዎች

# አባሪ አንድ

## የቤንች ማህበረሰብ በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚከውኗቸው ዶቦች በመገኛ ቋንቋቸው እና በአማረኛ ትርጉማቸው

### 1.የወርደት ዱብ

### ግጥሙ በመገኛ ቋንቋው

| አውራጅ (አቀንቃኝ) | ተቀባይ |
|---|---|
| Ababe balus babe | wow-wow |
| Baynu bab | wow-wow |
| Ha wore wogashno | wow-wow |
| Ha wose woxsa shino | wow-wow |
| Seto shna befo | wow-wow |
| Sherashido nibab dube | wow-wow |
| Bay gashe | wow-wow |
| Bakha shido | wow-wow |
| No nale nola befo | wow-wow |
| Wo nase nam befane | wow-wow |
| Wo kaso | wow-wow |
| Wornya kalo | wow-wow |
| Setenta bego | wow-wow |
| Wo dape wor nato | wow-wow |
| Wo angaso has nkaso | wow-wow |
| Wobabe bubedate | wow-wow |
| Wosise siskabefo | wow-wow |
| Kaya Kaya kaygue | wow-wow |
| Kaso kastam haqo | wow-wow |
| Wora wubesa | wow-wow |
| Wos kaoo | wow-wow |

## የግጥሙ ትርጉም በአማርኛ

| አውራጅ (አቀንቃኝ) | ተቀባይ |
|---|---|
| አባታችን ባለ ሚሊኒየሙ | ምው-ምው |
| ባኑ የምትባል ላም አለችው | ምው-ምው |
| ሙሽራይቱ አትቀመጪ | ምው-ምው |
| ከዘመድ ጋር ተጫወቺ | ምው-ምው |
| ይህችን ላም እንድትሰጪ | ምው-ምው |
| ወጣቱ አንጎራጉር እንጂ | ምው-ምው |
| አትፍራ የአባታችን ዘፈን ነው | ምው-ምው |
| የእናታችን ባህል ነው | ምው-ምው |
| ጨዋታ ነው ተጫወቱ | ምው-ምው |
| አንተ ሰው ሙሽሪትን አይተህ ተጫወት | ምው-ምው |
| የሙሽራ ዘመድ አይደለህም ወይ? | ምው-ምው |
| ልትጫወት የመጣህ? | ምው-ምው |
| ለምን ዝም ትላለህ? | ምው-ምው |

ተርጓሚ፡-ህብታሙ ኮምትኪት

## 2.የየብ ዱብ

| ግጥሙ በመገኛ ቋንቋው | ትርጉም በአማርኛ ቋንቋ |
|---|---|
| Kuy yiyi | ኩይ ይ!ይ!ይ! |
| Yare yare yeye (2x) | ያሬ ያሬ (2x) |
| Wo siso wo siso | ምሲሶ ምሲሶ |
| Woow! Woow | ዋው! ዋው |
| Yiyi yiyiyo | የቤንች ንጉስ ልጅ ይኸው |
| Benctetonantso yiyii | የሜር ንጉስ ልጅ ይኸው |
| Shetetnantso yiyiyio | የሳቸው ልጅ ነኝ እኔ |
| Wowoo | ጅንን ኩራ ወገኔ |
| Yiyi yio mettetnantso | የሳቸው በመሆኔ |
| Gatitnassado ---- | እኮራለሁ ገና እኔ |

ተርጓሚ፡-ህብታሙ ኮምትኪት

Hasis sis boya (4x)
Kaska kasasa boya
Qayxsa qaysasaboya
Yeka yesasa boya
Dyasa dyasasa boya

ሀሲስ ሲስ ቦያ (4x)
ተጫውተህ/ሽአጫወትኸን/ሽን ቦያ
ሰርተህ/ሽ አሰራኸን/ሽን ቦያ
አልቅሰህ/ሽ አስለቀስኸን/ሽን ቦያ
ወልደህ/ሽ አሳድገህል/ሻል ቦያ

ተርጓሚ፡- አዳሙ ሀንትያብ

## 3.የባለቃልቻ ዱብ

**ግጥሙ በመገኛ ቋንቋው**

Shasha-gakitnasa
Qaznisi yarsargusa
Utsni etargusa
Soteti sovxn skosagus
Usasi borsi tosxn barsagus
Balababa wumbaba
Menis kuchmaxn woxagus
Dodab harkus

**ትርጉም በአማርኛ**

ሻሻ የጋኪት ልጅ
አውጥቶ የማይመልስ
ሰጥቶ የማይወስድ
የባለአባት ልጅ እሱም ባለአባት
በህል ለውጦ ብር የሚለግስ
ድሀ የሚታደግ
ምስኪን የሚያሳድግ
ደግ የደግ ልጅ

ተርጓሚ፡- አዳሙ ሀንትያብ

## 4.የቃይጥ ዱብ

**ግጥሙ በመገኛ ቋንቋው**

**አውራጅ (አቀንቃኝ)**

Woyo yi! Ye yi yo
Shashntete nayuo
Zoyisa fayxso
Qayxsa miuo
Wotorsa tore

**ተቀባይ**

wow woyiyo wo shasha
wow woyiyo wo shasha
wow woyiyo wo shasha
wow woyiyo wo shasha
wow woyiyo wo shasha

| | |
|---|---|
| Wo denta geshidow | wow woyiyo wo shasha |
| No qerm zayxs zolo | wow woyiyo wo shasha |

## ትርጉሙ በአማርኛ

| አውራጅ (አቀንቃኝ) | ተቀባይ |
|---|---|
| ወይዬ ዩ!ይ ዩ ዮ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| የሻንቲቲት ልጆች | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| ጠንካራ ነህ ስራ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| በለስለታም ገጀራ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| የንጉስ ልጅ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| ታችኛው ነው የቀረህ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| ላይኛው ነው የቀረህ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |
| ከመሀል ነው የቀረህ | ዎ ወይዬ ወ ሻሻ |

ተርጓሚ፡-ሀብታሙ ኮምትኪት

## አባሪ ሁለት

### 1.የቁልፍ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | የአቀባይ ስም | እድሜ | ፆታ | ሙያ | ቀበሌ | መረጃው የተሰበሰበበት ቀን | መረጃው የተሰበሰበበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከድር ሸባ | 28 | ወ | የባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ምክትል ጸሀፊ | ደብረወርቅ | 24/08/2003 | ቢሮ |
| 2 | ኩንዲሳ ፊርኪ | 62 | ወ | የቡና ነጋዴ | ቂጤ | 25/08/2003 | ካፍቴሪያ |
| 3 | ሰለሞን ፈጠነ | 30 | ወ | የመገናኛ ብዙሀን ሰራተኛ | አዲስ አለም | 05/09/2003 | ካፍቴሪያ |
| 4 | ሀብታሙ ኮምትኪት | 29 | ወ | የመገናኛ ብዙሀን ሰራተኛ | ሚዛን ከተማ | 06/09/2003 | ካፍቴሪያ |
| 5 | ሻንቆ ጋኪናስ | 55 | ወ | አስታራቂ ሽማግሌ | አማን | 25/08/2003 | ቤትና ካፍቴሪያ |
| 6 | አበሽ ቱዮ | 58 | ወ | አርሶ አደር | ሚያህ | 19/08/2003 | መኖሪያ ቤት |

## 2.የንዑሣን መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

| ተ.ቁ | የአቀባይ ስም | እድሜ | ፆታ | ሙያ | ቀበሌ | መረጃው የተሰበሰበበት ቀን | መረጃው የተሰበሰበበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በላይ አዲሱ | 45 | ወ | አርሶ አደር | ሚያህ | 19/08/2003 | በቤት ውስጥ |
| 2 | አዳሙ ሀንትያብ | 32 | ወ | የመገናኛ ብዙሀን ሰራተኛ | ጊሊት | 06/09/2003 | በቢሮ ውስጥ |
| 3 | ቦጁ ቶዩ | 58 | ወ | አርሶ አደር | ሚያህ | 19/08/2003 | በቤት ውስጥ |
| 4 | ገዛኸኝ አባተ | 38 | ወ | የዞኑ አስተዳደር ዋና ጸሀፊ | ሚዛን | 26/08/2003 | በቢሮ ውስጥ |
| 5 | በርናባስ በኮምታት | 31 | ወ | | ሚዛን | 27/08/2003 | ካፍቴሪያ |
| 6 | ከበደ አበሽ | 32 | ወ | አርሶ አደር | ደብረወርቅ | 24/08/2003 | ካፍቴሪያ |
| 7 | ካማ አዲሱ | 39 | ወ | የደቡብ ቤንች ወረዳ አስተዳደር | አማን | 25/08/2003 | በቢሮ ውስጥ |
| 8 | ኩጁ መንግስቴ | 72 | ወ | ባለአባት(ባለቃልቻ) | ኮብ | 18/08/2003 | በቤት ውስጥ |
| 9 | ታደሰ ከተማራሽ | 29 | ወ | የባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ዋና ሃላፊ | ደብረወርቅ | 24/08/2003 | በቢሮ ውስጥ |